# ዘምዘም መፅሔት



በነፃ የሚከፋፈል ነው ::

ح المكتب التعاوني للدعوة والإرشاد وتوعية الجاليات بجنوب مكة, ١٤٣٨ هـ
فهرسة مكتبة الملك فهد الوطنية أثناء النشر
المكتب التعاوني للدعوة والإرشاد وتوعية الجاليات بجنوب مكة
زمزم – باللغة الأمهرية / المكتب التعاوني للدعوة والإرشاد
وتوعية الجاليات بجنوب مكة – مكة المكرمة , ١٤٣٨ هـ
٩٣ ص ؛ ١٧ X ٢٤ سم
ردمك: ٧-٦-٩٠٩٥٧-٦٠٣-٩٧٨
١-العقيدة الإسلامية أ. العنوان
ديوي ٢٤٠ ١٤٣٨/٨٨٠٦

رقم الإيداع: ١٤٣٨/٨٨٠٦
ردمك: ٧-٦-٩٠٩٥٧-٦٠٣-٩٧٨

جمعية الدعوة والإرشاد وتوعية الجاليات بجنوب مكة
ذكرى

ወደ ተከበረው ቤት ወደ መካ ለመጡ ሁሉ

በደቡብ መካ በሚገኘው የደዕዋ ቢሯችን ሁል ጊዜም ብትጎበኙን በጣም ደስ ይለናል፡፡

እኛ ጋር ለመገናኘትና ፕሮግራም ለመያዝ

00966125405537l-00966555264604- 00966534111272

ማሳሰቢያ ፡- ለዳዒዎች፤ ለኸጢቦችና ለኢማሞች የሚሆኑ እውቀት አዘል ስጦታዎች አሉን፡፡


እንኳን ደህና መጣችሁ፡፡

በድህረ ገፃችን አድራሻችንም ዉስጥ በልዩ ልዩ ቋንቋዎች የህትመት ዉጤቶችን ታገኛላችሁ፡፡

zamzam.mk@Gmail.com

በሚለው የፌስቡክ አድራሻችንም ሆነ በ00966534111252 ዋትሳብ ላይ አስተያየታችሁንና የተሰማች ሁን ገንቢ ሐሳባችሁን ብትልኩልን በደስታ ነው የምናስተናግደው፡፡

አላህ የሁላችንንም መልካም ነገር ይቀበልልን፡፡



# ማውጫ


የሁለቱ የምስክር ቃሎች............ 4

የ "ላኢላሀ ኢለሏህ "ቅድመ መስፈርቶች............ 9

የትክክለኛ አምልኮ መስፈርቶች ............ 13

የሽርክ አደገኝነት............ 18

የሶላት ክብደት............ 24

ዱዓ............ 28

ኢስላማዊ ወንድማማችነት ............ 32

የአማና ክብደት በኢስላም ............ 37

የሴቶች ክብር በኢስላም............ 40

መፈተን ............ 45

እምነታዊስህተቶች............ 47

ሱሃቦች የሰማይ ከዋክብት ............ 50

መካ የቅዱሳን ቦታዎች ሁሉ ቅዱስ............ 56

የየልጆች አስተዳደግ በኢስላም ............ 62

ወደ አላህ መጣራት ............ 68

ነነቢዩ ሙሐመድን ﷺ መውደድ ግዴታነት............ 72

ሲሳይእና ማግኛው ምክኒያቶቹ............ 76

بسم الله الرحمن الرحيم

በአላህ ስም እጅግ በጣም ሩህሩህ እና በጣም አዛኝ በሆነው እጀምራለሁ

ለአላህ ብቻ ምስጋና ይገባው፡፡ ሶላትና ሰላም በነቢዩ፤ በቤተሰቦቻቸውና በባልደረቦቻቸው ላይ ይሁን፡፡ በመቀጠል፡-ዉድ አንባቢያን እኛ በዚህ በወህይ መውረጃ፤ በኑብይነት መነሻ በሆነው ፤ በተከበረው በመካና በዙሪያዋ ባሉት ቅዱሳን ቦታዎች ዉስጥ የምንኖር በአላህ ቤት አጠገብ ስንቀበላችሁ የሚሰማንን ወደር የለሽ ደስታችንን ልንገልፅላችሁ እንወዳለን፡፡ አላህ የእኛንም ሆነ የእናንተን መልካም ተግባር እንዲቀበለን እንለምነዋለን፡፡ እናንተም ኸይሩን በሰፊው አፍሳችሁ በሰላም ወደ ሀገራችሁ እዲመልሳችሁ እንለምነዋለን፡፡

جـمـعـيـة الــدعــوة والإرشــاد
وتوعية الجاليات بجنوب مكة
ذكرى

በድቡብ መካ የኢሰላማዊ ጠሪ፤ ምክርና የማህብረሰቦች ግንዛቤ ማሳደጊያ ማስተባበሪያ ቢሮ ማስታወሻ



# የሁለቱ የምስክር ቃሎች፡

ኢስላም በስድስት የእምነት መሰረቶች እና በአምስት ዋና ዋና የኢስላም ማዕዘናት ላይ የተመሰረተ መለኮታዊ ሃይማኖት ነው፡፡ ስድስቱ የእምነት መሰረቶች ‹በአላህ ፤ በመላእክቶች፤ በመነቢያት፤ በመፅሐፍት፤ በትንሳኤ ቀንና ቀድሞውኑ በተወሰኑት የአላህ ውሳኔዎች እና ክስተት ማመን ነው፡፡ አምስቱ የኢስላም መሰረቶች እነሱም የሁለቱ የምስክር ቃላትን ከዉስጡ አምኖ በአንደበቱ መናገር፤ ሶላትን በትክክል መስገድ፤ ዘካን በአግባቡ ለተገቢው መስጠት፤ የረመዷንን ወር መፆምና የሐጅን ፀሎት ማደርግ ናቸው፡፡ ወደ ኢስላም መግቢያ የሆኑትን ሁለቱን የምስክር ቃሎች በአንደበቱ መናገር ከአምስቱ የኢስላም መሠረቶች አንደኛዉና ዋነኛው ነው፡፡ እነሱም «አሽሀዱ አላ ኢላህ ኢለሏህ፤ ወአሽሀዱ አነ ሙሐመድን ረሱሉላህ» የሚሉት ናቸው፡፡ የሁለቱ የምስክር ቃሎች ትርጉምም ከዚህ እንደሚከተለው ነው፡፡

## የ‹ላኢላህ ኢለሏህ› ትርጓሜ

"ላኢላህ ኢለሏህ" የሚለው ቃል ትክክለኛ ትርጉሙ፡-ከአላህ በስተቀር በትክክል ሊገዙት የሚገባው ትክክለኛ አምላክ የለም ማለት ነው፡፡ ምክኒያቱም (ኢላህ) ማለት የቋንቋ ትርጉሙ አምላክ /አምልኮ የሚገባው/ ማለት ሲሆን እንዲሁም በልዕልናው፤ በግርማ ሞገሱ፤ በሀያልነቱ፤ ሁሉን ቻይና ሁሉን አሰገኚነቱ ሰዎችም ሆኑ ሌሎች ፍጠራን ሊገዙት የሚገባው ማለት ነው፡፡ ይህም አላህ በቁርአን "ይህ አላህ እርሱ እውነት ከእርሱም ሌላ የሚገዙት ጣዖታት ሁሉ ውሸት በመሆኑና አላህ የበላይ ታላቅ በመሆኑ ብቻ ነው" በማለት ያስተማረው ነው፡፡ ከአላህ ሌላ አምላክ የለም ማለት፡- ሰዎችም ሆኑ ጋኔኖች ሊገዙት፤ ትዕዛዙን ሊፈጽሙ እና ሊያመልኩት የሚገባ፤ የዓለም ብቸኛ ባለቤትና ገዢ በመሆኑ ከርሱ ውጪ ያለው የርሱን ረድዔት ከጃይ መሆኑን በእርግጠኝነት ማወቅና በአንደበት መመስከር ማለት ነው፡፡ ትክክለኛው አምላክ ከፍጡራን አንዳች ነገርንም የማይፈልግ፤ ፍጡራን ግን በሙሉ ከርሱ ረድዔትን ሁልጊዜም የሚከጅሉት ነው፡፡


## ሙሐመድ ﷺ የአላህ መልዕክተኛ ናቸው ብሎ መመስከር ትርጉም

ነቢዩ ሙህመድ ﷺ ለሰዎችም ሆነ ለጋኒኖች የአላህ መልዕክተኛ ናቸው ብሎ ከልብ አምኖ በአንደበት መመስከር ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳይ አላህ በቁርአን እንዲህ አለ፡ - «መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! እናንተ ሰዎች ሆይ ! እኔ ወደ እናንተ ወደ ሁላችሁም የአላህመልዕክተኛ ነኝ፡፡ ያ ! የሰማያትና የምድር ንግስና ለእርሱ ብቻ የሆነ ነው፡፡ እርሱ እንጂ ሌላ አምላክ የለም፡፡ አላህ ህያው ያደርጋል፡ ፡ ይገድላልም፡፡ በአላህ በዚያም በአላህና በቃላቶቹ በሚያምነው የማይጽፍ የማያነብ በሆነው መልክተኛው እመኑ፡ ፡ ወደ ቅኑ መንገድ ትመሩ ዘንድ ተከተሉት በላቸው» አል-

አዕራፍ 158. እንዲህም አለ (ያ ! ፉርቃንን (እውነትን ከውሸት የሚለየውን ቁርአን) በባሪያው ላይ ለዓለማት አስፈራሪ ይሆን ዘንድ ያወረደው አምላክ ጥራት ይገባው) አል-ፉርቃን 1. ይህ የምስክር ቃል ነቢዩ ሙሐመድﷺ፤

1-ያዘዙትን ሁሉ በአቅም ልክ መታዘዝ፤
2-የከለከሉትን እና ያስጠነቀቁትን መከልከልና መራቅ፤
3-አላህንም በሳቸው አማካኝነት በተደነገገው የሸሪዐ ህግ መሰረት አንጂ አለማምለክ፤
4-የተናገሩትን ሁሉ እውነት ነው ብሎ መቀበል፤
5-እሳቸዉን ከአላህ በመቀጠል ከማንም አስበልጦ መውደድን፤
6-የአምላክነት ስልጣንም ሆነ ዓለምን የማስተናበር አቅም የሌላቸው፤ እንኳንስ ለሌላ ለራሳቸዉም መጉዳትም ሆነ መጥቀም የማይችሉ፤ የነቢያት ሁሉ ማጠቃለያ ነቢይ መሆናቸዉን በትክክል አምኖ መቀበልን ሁሉ ያካትታል፡፡ ነቢዩ ﷺ የአላህ ቅኑ አገላጋይ፤ ያዘዛቸዉን ተከታይ እንጂ ይህን አድረጉልኝ እየተባሉ ሊለመኑ የማይችሉ፤ ገይብ ነገሮችን የማያውቁ፤ ለፈለጉት ኢስላምን ማስያዝ የማይችሉ መሆናቸዉን በተመለከተ አላህ በቁርአን እንዲህ አለ «መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ! የአላህ ግምጃ ቤቶች እኔ ዘንድ ናቸው አልላችሁም፡፡ ሩቅ ሚስጥርንም አላውቅም፡፡ መላዕክት ነኝም አልልም፡፡ ወደ እኔ የሚወርድልኝን መልዕክት እንጂ ሌላን አልከተልም በላቸው፡፡ እውርና የሚያይይስ ተካከላሉን ? አታስተነትኑምን ! በላቸው»አል-አንዓም50. እንዲህም አለ «መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ! ትንሳኤ መቼ እንደምትመጣ ይጠይቁሃል፡፡ እውቀቷ በጌታዬ ዘንድ ብቻ ነው፡፡ መከሰቻዋ ጊዜንም እርሱ እንጂ ሌላ አይገልፅላችሁም፡፡ በሰማያትና በምድር ከበደች፡፡ በድንገት ቢሆን እንጂ አትመጣባችሁም በላቸው፡፡ ስለ እርሷ በደንብ እንደ ተረዳህ አድርገው ይጠይቁሃል፡፡ እውቀቷ ግን አላህ ዘንድ ብቻ ነው፡፡ ግን አብዛኞቹ ሰዎች ይህንን ነገር ጠንቅቀው አያውቁም በላቸው፡፡ መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! አላህ የፈለገዉን በስተቀር ለራሴ ጥቅምንም ሆነ ጉዳት አልችልም፡፡ የሩቅን ሚስጥር የማውቅ በነበርኩ ኖሮ ከመልካም ነገር ሁሉ ባበዛሁና ክፉም ነገር ባልነካኝ ነበር፡፡ እኔ ለሚያምኑ ህዝቦች ሁሉ አስፈራሪና አብሳሪ እንጂ ሌላ አይደለሁም በላቸው»አል-አእራፍ 187-188.

ነብዩ ሙህመድ (ﷺ) የመጨረሻው የአላህ ነብይ እና ታዛዥ ባሪያ መሆናቸውን መመስከር ሁልጊዜም የአላህን አምላክነት ከመመስከር ጋር የሚነጠል ጉዳይ አይደለም፡፡ በእነዚህም ከሁለቱ የምስክር ቃል በመነሳት ነቢዩም ሆኑ ከሳቸው በታች ያለ ሁሉ የማይመለክ መሆኑን፤አምላክነት የአንድ አላህ ብቸኛ ስልጣን መሆኑን ነው በግልፅ የምንማረው፡፡



ተውሒድ ቃሉ የመነጨው ወሐደ ከሚለው የአረበኛ ስርወ ቃል ነው፡፡ ትርጉሙም አንድነትንና ብቸኝነትን አመላካች ቃል ነው፡፡ በሸሪዓው አጠቃቀም መሠረትም ተውሒድ ማለት አላህን በፈጣሪነቱና በአምላክነቱ ብቸኛ ማድረግ፤ የላቁ መልካም ስሞች እና የላቁ ባህሪያት ባለቤት መሆኑን ማመን፡እንዲሁም ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) የእርሱ መልእክተኛና የነብያት መቋጫ መሆናቸውን በመቀበል ያመጡትን ሁሉ መልእክት መከተል ነው፡፡ ስለዚህ ተውሒድ ማለት በቋንቋ የሆነን ነገር አንድ ማድረግ ማለት ሲሆን በኢስላም ሃይማኖትም አላህን በፈጣሪነቱ፤ በተንከባካቢነቱ፤ በአስተናባሪነቱ፤ በአምላክነቱ በስሞቹና በባህሪያቱ አንድ ማድረግ ማለት ነው፡፡

ተውሒድ ማለት የአላህን ፈጣሪነትና አስተናባሪነት (ሩቡብያ) መቀበል ብቻ አይደለም፡፡ በአምልኳችንም ብቸኛ እስካላደረገነው ድረስ ምክኒያቱም ከተውሒድ ጋር ያልተሳሰረ ተግባር ሁሉ ዋጋ የለውምና፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡-«የእነዚያ በጌታቸው የካዱት ሰዎች መልካም ሥራዎቻቸው ምሳሌ በነፋሻ ቀን ነፋስ እንደ በረታችበት አመድ

ነው:: በሠሩት ሥራ በምንም ላይ ሊጠቀሙ አይችሉም ይህ እርሱ ሩቅ ጥፋት ነው»ኢብራሂም› 18.

ተውሒድ፤ ዐቂዳ ፤ኢማን እና ኢስላምም ይባላል:: ወደ ዝርዝር ሲገባ ዐቂዳ የዉስጥ እምነትን የሚያመለክት ሲሆን ከአላህ ሌላን የሚያምንንም ያጠቃልላል:: ኢማን ደግሞ የልቦናን እምነቶችና የምላስንና የአካልን ተግባራት ሁሉ ያካትታል:: እናም ኢማን በመልካም ስራና በኢባዳ ይጨ ምራል:: በወንጀልም ይቀንሳል::

## የተውሒድ ጠቀሜታዎች

ተውሒድ:-የትክክለኛ ሙስሊሞች አስተማማኙና ብቸኛው ምሽግነው::

ተውሒድ:-የአላህ መልእክተኞች ሁሉም በአብይነት ጥሪ ያደረጉበት ዋነኛ ቁም ነገር ነው:: አላህ እንዲህ አለ:-«በየ ሕዝቡ ሁሉ ውስጥ አላህን ተገዙ ጣዖትን ራቁ በማለት የሚያስተምር መልዕክተኛን ልከናል:: ከእነርሱም ውስጥ አላህ ያቀናው ሰው አለ:: ከእነርሱም ውስጥ በእርሱ ላይ ጥመት የተረጋገጠበት ሰው አለ» (አል-ነህል 36) በመሆ ኑም አላህ በብቸኝነት ያለተጋሪ በፍጹም ቅንነትና ታማኝ ነት ይመለክ ዘንድ መልእክተኞችን ሁሉ ላከ:: መጽሐፍ ትንም አወረደ:: እናም የተውሒድን ክልል መጠበቅ የነ ብያትና የመልእክተኞች፣ እንዲሁም እስከ እለተ ቂያማ ድረስ እነርሱን በበጎ ተግባራት የተከተሉ ሰዎች ሁሉ አብይ ተግባር እና ዋነኛ ሃላፊነት ነው:: ሸይኽል ኢሰላም ኢብነ ተይሚያህ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፤-‹መልእክተኞች ሁሉ ያመጡት ተውሒድ በውሰጡ የአላህን ብቸኛ አምላክነት ማጽደቅን ያካተተ ነው:: ይህውም ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለ ይመሰክራሉ:: ከሱ ውጭ ሌላን አያመልኩም:: በርሱ ብቻ ይመካሉ:: ለርሱ እንጅ ለማንንም አይወጓ ኑም:: እርሱን መነሻ አድርገው እንጂ ማንንም አይጠሉም:: ለርሱ እንጂ ለማንም አይሰሩም::

## ተውሒድ በሦስት አይነት የተከፈለ ነው:: የመጀመሪያው የተውሒድ ክፍል:- ተውሂደ ሩቡቢያ ይባላል::

እርሱም የፍጡራን ፈጣሪ፣ ሲሳይን ለጋሻቸው ሕይወት የሚሰጣቸውም የሚገድላቸውም አላህ ብቻ መሆኑን ማመን ነው:: መፍጠር፣ ሲሳይ መለገስ፣ ሕይወት መስጠ ትና መንፈግ የርሱ ስልጣን ብቻ መሆኑን ማጽደቅ ነው:: ይህን የተውሒድ አይነት በአላህ መልእክተኛﷺዘመን የነበሩ ሙሽሪኮች አጽድቀውታል:: አይሁድ፣ ክርስቲያኖ ችና መጁሶችም(እሳት አምላኪዎች) እንከዋን ይቀበሉታል:: የካዱት ደህሪይን በመባል የሚታወቁት የጥንት ቁሳው ያን እና የዚህ ዘመን የኮሚኒሰት አሰተሳሰብ አራማጆች ብቻ ናቸው:: ይህን የተውሒድ ክፍል መቀበል ሰውየ ውን ወደ እስልምና ሐይማኖት አያስገባም:: ደሙን እና ገንዘቡንም የተጠበቀ አያደርገውም:: በመጭው አለምም ከእሳት አያድነውም:: ሙስሊም ለመሰኘት ሌላኛውን የተውሒድ ክፍል መቀበል አለበት:: እርሱም ተውሂደ ኡሉሂያ ይባላል:: ይህ የተውሒድ ክፍል በሰው ልጅ ተፈጥሮ ውስጥ ያለ ነው:: በሐዲስ ይኸው ተመልክቷል:-‹ሁሉም ልጅ በተፈጥሯዊ ሐይማኖት ውስጥ ሆኖ ይወለ ዳል:: ከዚያ በኃላ ወላጆቹ አይሁድ፣ ክርስትያን ወይም መጁስ ያደርጉታል› ይህን የተውሒድ ክፍል የሚመለከቱ የቁርአን መረጃዎች በርካታ ናቸው:: ተከታዩ አንቀጽ ለአ ብነት ይጠቀሳል «ከሰማይና ከምድር ሲሳይን የሚለግሳ ችሁ፤ መሰሚያ ጆሮዎችን፣ መመልከቻ ዓይኖችን የሰጣ ችሁ፤ ሕያውን ከሙት፣ ሙትን ከሕያው የሚያወጣ፣ነገሮ ችን የሚያስተናብርና የሚሰራ ማነው?በላቸው አላህ ነው ይላሉ:: «አትፈሩትምን ?»በላቸው:: «አላህ ይህ ነው:: እውነተኛው ጌታችሁ:: ከእውነት በኋላ ጥመት እንጅ ሌላ ምን ሊኖር ይችላል ? ታዲያ ለምን ከእውነት ትዞራላችሁ::? »(ዩኑስ 31-32).

## ሁለተኛው የተውሒድ ክፍል:- ተውሂደል ኡሉሂያህ ይባላል::

እርሱም አላህን በብቸኝነት ማምለክ ነው:: ማለትም:- ኢባ ዳዎችን ሁሉ ለምሳሌ ዱዓን፤ ስለትን፤ እርድን፤ ተስፋን፤ ፍርሃትን፤ መመካትን፤ መጓጓትን፤መስጋትን፤ በተውባ መመለስን፤ እርዳታ መፈለግን እና መሰል ኢባዳዎችን ሁሉ ለአላህ ብቻ ማድረግ ነው:: ከጥንት ዘመን ጀምሮ ሰዎች

የተወዘገቡበት የተውሒድ አይነት ይህ ክፍል ነው፡፡ መልክተኞችም ወደየህዝቦቻቸው የተላኩበት ተውሒድ ይህ ነው፡፡ መልእክተኞች ሕዝባቸው ድሮውኑ የተቀበለውን ተውሒድ ሩቡብያን ካጸደቁ በኋላ ወደዚህ የተውሒድ ክፍል ማለትም ወደ ተውሒድ ኡሉሂያ ጥሪ አድርገዋል፡፡ አላህ የኑህን ተልእኮ አስመልክቶ ሲናገር እንዲህ ይላል «ኑህን ወደ ወገኖቹ ላክን ፡፡ እኔ ለናንተ ግልጽ አስጠንቃቂያቹ ነኝ*፡፡ (የሚል የጥሪ ድምጹንም አሰማ)፡፡ አላህን እንጂ አታምልኩ፡፡ እኔ የአሰቃቂውን ቀን ቅጣት እፈራላችኋለሁ (አላቸውም)(ሁድ 25-26) እንዲህም ብሏል «አላህን በብቸኝነት አምልኩ፡፡ ከርሱ ጋር አንድንም አካል አታጋሩ »(አል ኒሳእ 36) ይህ ተውሒድ በሰው ልጆች ላይ ግዴታ የሆነ የአላህ መብት ነው፡፡ የዲኑ ትልቁ ትእዛዝም ይሄው ነው፡፡ የስራዎች ሁሉ መሰረትም ነው፡፡ ቁርኣንም አጽድቆታል፡፡ በርሱ ካልሆነ በስተቀር የጀነት ደስታና ከእሳት መዳን እንደማይገኝም በተደጋጋሚ አብራርቷል፡፡

ሶስተኛው የተውሒድ ክፍል፡- ተውሂዱል አስማእ ወሲፋት ይባላል፡፡

ይህ የተውሂደ ክፍል ከአላህ ስሞችና ባህሪያት ጋር የተያያዘ የተውሒድ ክፍል ነው፡፡ ይኸውም አላህ ራሱን የገለጻባቸውን ወይም ነብዩ ሙህመድ ﷺ እርሱን የገለጹበትን ስሞችና ባህሪያት ሳያዛቡና ሳያዛንፉ እንዲሁም ከፍጡራን ጋር ሳያመሳስሉ እንዳሉ መቀበልና ማጽደቅ ነው፡፡

ተውሒድና ሶስቱ የቀብር ጥያቄዎች ጥብቅ ግንኙነት

የአዕምሮ በሽተኛ እብድ የሆነ እና ሕፃን ሲቀር የሞተ ሰው ሁሉ በቀብር ውስጥ ከሶስት ጉዳዮች ይጠየቃል፡፡ እነሱም፡

1-ጌታህ ማነው ?

2-ነብይህስ ማን ነው ?

3-እምነትህ ምንድን ነው ? የሚሉ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ ሁሉንም ከመለስ ነፃ ይወጣል፡፡ ካልመለሰ ግን ይከስራል፡፡ እናም ከነዚህ ጥያቄዎች መካከል፡- አንዱ ነብይህ ማን ነው የሚለው መሆኑን ተመልክተናል፡፡ ይህን ጥያቄ በዱንያ ላይ ሳለ መስፈርቶቹን አሟልቶ የነበረ ሰውና አላህ በቀብር ውስጥ ፅናቱን ሰጥቶት ልጅም ሆነ ገንዘብ በማይጠቅምበት በዚያ ቀን እንድትጠቅመው ያደረገለት ሰው ካልሆነ በስተቀር ለትክክለኛው መልስ ሁሉም ሰው አይታደልም፡፡ እነዚህ መስፈርቶችም ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው፡፡

አንደኛው፡-ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ያዘዙትን ሁሉ በአቅሙ ልክ መታዘዝ ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ አላህ በቁርአን እንዲህ አለ ፡- «መልዕክተኛውን የሚታዘዝ ሰው ሁሉ በርግጥ አላህን ታዘዘ፡፡ ከትዕዛዝም የሸሸሰው (አያሳስብህ) ርሱ ላይ ጠባቂ አድርገን አላክንህምና" የሴቶች ምዕራፍ 80). እንዲህም አለ፡-«መልዕክተኛውም የሰጣችሁን ማንኛውም ነገር ያዙት፡፡ ከእርሱም የከለከላችሁን ነገር ሁሉ ተከልከሉ፡፡ አላህን ፍሩ፡፡ አላህ ቅጣቱ ብርቱ ነውና) አል ሐሽር 7.

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዐልቀማህ እንዳስተላፉት ዐብደላህ ኢብኑ መስዑድ እንዲህ ብለዋል፡- ‹አላህ ንቅሳት የሚነቅሱትንና የሚነቀሱትን፤ የቅንድባቸውን ፀጉር የሚላጩትን፤ ጥርሶቻቸውን ለውበት ሲሉ የሚነቀሱትን፤ የአላህን ተፈጥሮ በራሳቸው የሚቀይሩትን ሴቶች ረግሟቿዋል»አሉ፡፡



ይህ ወሬ ኡሙ የዕቁብ የምትባል ከበኒ አሰድ ጎሳ የሆነች ሴት ይደርሳትና ወደ እርሳቸው መጥታ፡-«አከሌን አከሌን እንደረገምክ በእርግጥ ደርሶኛል» አለቻቸው፡፡ እሳቸውም፡ -«የአላህ መልዕክተኛ ሙሐመድ (ﷺ) የረገማቸውንና በአላህ ቁርኣን ውስጥ የተረገሙትን እንዴት አልረግማቸውም?» አሉ፡፡ ሴትየዋም «በሁለቱ ሎኾች/ማቀፊያውች/ መካከል የተፃፉትን አንብቤያቸዋለሁ ነገር ግን አንተ የምትለውን አላገኘሁም» አለቻቸው፡፡ እሳቸውም «በእርግጥ በትክክል ብታነቢያቸው ኖሮ ታገኚው ነበር፡፡ እንደው «መልዕክተኛውም የሰጣችሁን ማንኛውም ነገር ያዙት፡፡ ከርሱም የከለከላችሁን ነገር ተከልከሉ» አል ሐሽር፡ 7. የሚለው አላነበብሽምን ?» አሏት፡፡ እሷም «እንዴታ! አንብቤዋለሁ እንጂ» አለቻቸው፡፡ እሳቸውም «በእርግጥ እሳቸው ከዚህ ነገር ከልክለዋል» አሏት፡፡ እሷም «ቤተሰቦችህ ይህን ሲፈፅሙ በእርግጥ ተመልክቻቸዋለሁ» አለቻቸው፡፡ እሳቸውም «ሂጂና ተመልከቺያቸው» አሏት፡፡ ሴትየዋም ሄዳ ስትመለከት የምትፈልገውን ነገር ሳትመለከት ቀረች፡፡ እሳቸውም«ሚስቴ አንቺ እንደምታስቢው ሆና በነበር አብሬ አልኖርም ነበር» አሏት፡፡ ቡኻሪ ዘግበውታል.



<u>አንድኛ፡-</u> "ሙሐመድ ሆይ ! አላህን የምትወዱ እንደሆናችሁ እኔን ተከተሉኝ አላህ ይወዳችኋል፡፡ ሀጢአቶቻችሁንም ለናንተ ይምራልና፡፡ አላህ መሀሪና አዛኝ ነው በላቸው" (ኣሊ ዒምራን 31) በማለት እሳቸዉን እንድንከተልና እንድንታዘዝ ስላዘዘን ነው፡፡ ያለምንም ገደብ ጀነት መግባት እሳቸዉን በመታዘዝ የሚገኝ እድል ነው፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ "ህዝቦቼ ሁሉ ጀነት ይገባሉ እንቢ ያለ ሲቀር አሉ፡፡ ሶሃቦችም የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ! ማን ነው እንቢ የሚለው ! ሲሏቸው 'የታዘዘኝ ሰው ሁሉ ጀነት ይገባል፡፡ ያልታዘዘኝ ሁሉ ደግሞ እንቢ አለ "ብለዋል፡፡ ነቢዩን (ﷺ) እወዳለሁ የሚል ሰው ሁሉ እሳቸዉን መታዘዝ ግዴታው ነው፡፡ ምክኒያቱም መታዘዝ የመውደድ ዉጤት ነዉና፡፡ እሳቸዉን ሳይታዘዝና ሳይከተል እወዳቸዋለሁ በማለት የሚሞግት ሰው ሙግቱ የሐሰት ነው፡፡

<u>ሁለተኛ</u>፡- የተናገሩትን ሁሉ እዉነት ነዉ ብሎ ማመን ነው፡፡ ከነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ከተዘገቡ ነገሮች አንድን ነገር በልብ ወለዱ ወይም በስሜቱ ተገፋፍቶ ያስተባበለ ሰው አላህንና መልዕክተኛዉን አስተባብሏል፡፡ ምክኒያቱም ነቢዩ (ﷺ) ከስህተትና ከዉሸት የፀዱ ናቸዉና፡፡ አላህ እንዲህ አለ "ከልብ ወለድ አይናገርም፡፡ እርሱ /ቁርኣን/ ከአላህ የተወረደለት እንጂ ሌላ አይደለም" አን-ነጅም.3-4.

<u>ሶስተኛ፡-እሳቸዉ</u> የከለከሉትንና ያስጠነቀቁትን መራቅ፡፡ ይሄዉም ከወንጀሎች ሁሉ ታላቁ ከተባለው ከሽርክ አንስቶ በታላላቅ ወንጀሎች አልፎ እስከ ጥቃቅን ወንጀሎች ድረስ ያሉትን መራቅ ነው፡፡ ማንኛዉም ሙስሊም ለነቢዩ ባለው ዉዴታ ልክ እምነቱ ይጨምራል፡፡ እምነቱ በጨመረ ልክም አላህ መልካም ስራዎችን ያስወድደዋል፡፡ መጥፎተግባሮችን ያስጠላዋል፡፡

<u>አራተኛ፡-አላህን</u> በርሳቸው አማካኝነት በተደነገገው የሸሪዓ ህግ መሰረት ብቻ እንጂ አለማምለክ ነው፡፡ አምልኮትን በተመለከተ የቅድሚያ መሰረቱ መከልከል ነው፡፡ እናም ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ባስተማሩት መሰረት እንጂ አላህን ማምለክ አይገባም "ትዕዛዛችን የሌለበትን ስራ የሰራ ሰው ሁሉ ስራው ዉድቅ ነው"ብለዋል፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም. በሌላ ዘገባም "ትዕዛዛችን የሌለበትን ስራ የሰራ ሰው ሁሉ ስራው ዉድቅ ነው" ብለዋል፡፡ ሙስሊም. እነዚህን የምስክር ቃሎች ለሰው ዘር ሁሉ የማድረስ ሃላፊነት በሁላችንም ላይ የተጣለ በመሆኑ ሃላፊነታችንን በአግባቡ ለመወጣት ማጠር ይኖርብናል፡፡ አላህ ይርዳን፡፡



# የላኢላህ ኢለሏህ ቅድመ መስፈርቶች

የ"ላኢላህ ኢለላህ " ቅድመ መሰፈርቶች ብዙ ናቸው፡ ፡ ምክኒያቱም በምላሱ ላኢላሃ ኢለላህ ያለ ሁሉ የተው ሒድ ባለቤት ላይሆን ይችላል፡፡ እናም የተውሒድ ባለቤት ለመሆን አሊሞች በዋነኝነት ያወሷቸውን የላኢላህ ኢለላህ ሰባት ቅድመ መሰፈርቶች መጧላታቸው ግድ ነው፡፡ እነሱም፡-

1. የላኢላህ ኢለላህን ትርጉሙን በሚገባ መረዳት ሲሆን፡ - እርሱም በእውነት/በሐቅ/ ለመመለክ የሚገባው ከአላህ ሌላ እንደሌለ ከዉስጥ ማመን፤ በአንድበት መመስከር እና በተግባር ማዋል ነው፡፡ ምክኒያቱም እያንዳንዱ ቃል የራሷ የሆነ ትርጉም አላት፡፡ እናም ያን ትርጉም በትክክል መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ትርጉሟም አምላክነትን ከአላህ ሌላ ከሆነ ሁሉ ስርዞ ለእርሱ ብቻ ብቸኛ አምላክነትን በማ ፅደቅ በእውነት ሊመለክ የሚገባው ከአላህ ሌላ ማንም፤ ምንም የለም ማለት ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳይ አላህ እንዲህ አለ "ከአላህ በስተቀር አምልኮ የሚገባው እንደሌለ እወቅ" ሙሐመድ 19.

እንዲህም አለ፡፡"እነዚያም ከአላህ ሌላ የሚገዟቸው እነሱ ትክክለኛዉን የማያውቁ ሆነው በእውነት ከመስከሩ ክፍሎች በስተቀር ምልጃን አይችሉም" አዙኽሩፍ፡86.

ነቢዩ ሙሐመድም (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ (በት ክክል የሚመለክ ከአላህ ሌላ የሌለ መሆኑን እያወቀ የሞተ ሰው ሁሉ ጀነት ይገባል) ብለዋል፡፡ እንዲህም 'ምንንም ነገር በአላህ ሳያጋራ የሞተ ሰው ጀነት ይገባል" ብለዋል፡ ፡ ሙስሊም.

2.መልዕክቱን በፅኑ ማመንና ከልብ መቀበል ነው፡፡ ይህም ማለት መልዕክቱን በትክክልና ያለምንም ጥርጣሬ መቀበል ነው፡፡አላህ አማኞችን ሲገልፅ "እውነተኞቹ ምዕመናን እነዚያ በአላህና በመልዕክተኛው ያመኑና ከዚያም ያልተ ጠራጠሩ፤ በገንዘቦቻቸውም በአላህ መንገድ ላይ የታገሉ ናቸው፡፡ እነ ዚያ እነርሱ እውነተኞቹ ናቸው"ብሏል፡፡ አል-ሑጁራት 15፡፡ ነቢዩ ሙሐመድም ﷺ "አሽሀዱ አንላ ኢላህ ኢለሏህ ወአነ ሙሐመደን ረሱሉላህ /በሚሉት በሁለቱ ሳይ ጠራጠር ከአላህ ጋር መገናኘት የቻለ ሰው ሁሉ ከጀነት የሚ ጋርደው ማንም የለም»ብለዋል፡፡ሙስሊም.

3. ይህ መልዕት የሚያስከትላቸውን ግዴታዎች በልቡና አምኖ በአንደበትም መቀበልና መመስከር ነው፡፡ ምክኒያ ቱም ላኢላህ ኢለላህን ካወክና ካረጋገጥክ ለዚህ ማረጋገ ጥህ ዉጤት ሊኖርህ ይገባል፡፡ ይኸዉም ይህ የምስክር ቃል ግዴታ አድርጎ የያዘችዉን በልብም ሆነ በምላስ መተ ግበርና መቀበል ነው፡፡ የተውሒድን ጥሪ በትዕቢትም ሆነ በሞገደኝነት ወይም በምቀኝነት የተቃወመና ያልተቀ

በለ ሰው ሁሉ ከሃዲ ነው:: አላህ በትዕቢት የተቃወሙ ትን ሰዎች (እነርሱ ከአላህ ሌላ አምላክ የለም በተባሉ ጊዜ ይኮሩ ነበር» (አሷፋት:35) በማለት ገልጿቸዋል::

4. ይህ ቃል የሚያስከትላቸውን ግዴታዎች መፈፀም:: ይህም የሚረጋገጠው አላህ የደነገገዉን በመተግበርና የከ ለከለዉን በመተው ነው:: አላህ እንዲህ አለ "መልካም ስሪ ሆኖ ፊቱን ለአላህ የሚሰጥ ሰው ሁሉ ጠንካራ ገመድን በእርግጥ ጨበጠ:: የነገሩ ሁሉ ፍፃሜ ወደ አላህ ብቻ ነው"(31:22) . የምስክር ቃሉ ግዴታ አድርጋ የያዘቻዉን በልብም ሆነ በምላስ መተግበርና መቀበል ነው:: አላህ የደነገገዉን በመተግበርና የከለከለዉን በመተው መታዘዝ ነው:: አላህ እንዲህ አለ:-"ሰዎች ሆይ ! ቅጣቱ ወደ እናንተ ከመምጣቱና ከዚያም የማትረዱ ከመሆናችሁ በፊት ወደ ጌታችሁ በመፀፀት ተመለሱ» አዙመር:54.

5.እውነተኛነት እርሱም በአንደበት መናገርና የልቦና እምነት ነው:: ይህም ማለት ሲናገራት እዉነተኛ ሆኖ ዉሸትን ተፃርሮ መሆን አለበት፡ ልቡ እያስተባበለ በምላሱ ብቻ የሚናገራት ሙናፊቅ ይሆናል:: ቁርአን ሙናፊቆችን ሲያወግዝ እንዲህ ይላል ". . . በልቦቻቸው ውስጥ የሌለን ነገር በምላሶቻቸው ይናገራሉ" (አል-ፈትህ:11).

6. ኢኽላስ::ቃሏን ሲናገርም ሆነ በእሷ ሲሰራ ለአላህ ብቻ የማድረግ ስሜት/መኖር ነው:: አላህ እንዲህ አለ:- «ሃይማ ኖትን ለአላህ ብቻ አጥሪዎች፣ ወደ ቀጥተኛ መንገድ የተ ዘነበሉ ሆነው ሊገዙት፣ ሶላትንም አስተካክለው ሊሰግዱ፣ ዘካንም ሊሰጡ እንጂ አልታዘዙም:: ይህም የቀጥተኛይቱ ድንጋጌ ነው"(አል-በይነህ:5). ነቢዩ ሙሐመድም "አላህ የእሱን ዉዴታ ፈልጎ በፍፁምነት ላኢላህ ኢለሏህን የተ ናገረን ሰው እሳት በሱ ላይ እርም አድርጓል"ብለዋል:: ቡኻሪና ሙስሊም.

ከእነዚህ ቅድመ ሁኔታዎችም ጋር እስከ ዕለተ ሞቱ ድረስ በእሷ ላይ መፅናት ያስፈልጋል::

7. መልዕክቷንና የምታስከትላቸውን ኃላፊነቶች መውደድ:: የምስክርነት ቃሏን መልዕክቷንና በሷ የሚሰሩትን ሰዎች ሰዉ ጌታዉን የመውደዱ ምልክት ስሜቱ ከሚወደውና አላህ ከሚወደው የአላህን ዉዴታ ማስቀደም፤ የአላህን ወዳጆች ወዳጁ ማድረግ፤ ጠላቶቹን ጠላቱ ማድረግ፤ ነቢዩ ሙሐመድን መከተል፤ መመሪያቸዉን ማክበር ነው:: አላህን፤ ነብዩን፤ ሙእሚን ወንድሞቹን በመውደድ የእምነት ጣዕም ይገኛል:: ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ «ሶስት ነገሮች በውስጡ ያሉለት በእነሱ የእ ምነትን ጣዕም አግኝቷል:: አላህ እና መልዕክተኛውን ከእነሱ ውጪ ከሆነ ሁሉ አብልጦ መውደድ፤ ሰውን ሲወድ ለአላህ ብቻ ብሎ መውደድ አላህ ከክህደት ነፃ ካዳረገው በኋላ ወደ ክህደት መመለስን ወደ እሳት እንደመወርወር ያህል መጥላት ነው» ብለዋል::

መውደድ ለሶስት ይከፈላል::

ሀ -ያለምንም ጥላቻ በንፁህ መውደድ ሲሆን:-እነሱም ንጹህ አማኞች፤ ነቢያት፤ ፃድቃን ሲሆኑ የእነዚህም ግንባር ቀደም ነቢዩ ሙሐመድ፤ ሚስቶቻቸው፤ ሴት ልጆቻቸ ውና ባልደረቦቻቸው ናቸው::

ለ-ፈፅሞ የማይወደዱና ብሎም ከእነሱ ነፃ መሆን አስፈላጊ የሚሆንበት ነው:: እነሱም ከመፅሐፍ ባለቤቶች መካከል፤ አጋሪዎች፤ ሙናፊቃንና ከሃዲዎች ናቸው::

ሐ-በአንድ በኩል ሲወደድ በሌላ በኩል ደግሞ የሚጠላ አካል አለ:: እሱም በልዩ ልዩ ስህተቶች ዉስጥ የተዘ ፈቁ አማኞች ሲሆኑ ባላቸው መሰረታዊ እምነት መጠን ሲወደዱ በፈፀሙት ስህተት መጠንም ይጠላሉ::

ከእነዚህ ውስጥ ዋናዎቹ:- የፍጥረታት ሁሉ ፈጣሪ፣ ሲሳይን ለጋሽ፣ ህያው የሚያደርግ፣ ሕይወትን የሚነሳ፤ የማይሞት፣ የዚህ ፍጥረት አለም ባለቤት፣ ብቸኛ ገዥና ሕግ አውጪ መሆኑን ማመን:: ህግጋትን የመንደፍና ደንቦችን የማውጣት የእሱ ብቻ ስልጣን መሆኑን ማመን ነው:: የአላህን ደንብና ስርዓት ሳይከተል ማንም ሰው ለራሱም ሆነ ለሌላው ደንብና መመሪያ ሲያወጣ አይፈቀ

ከተውሒድ መገለጫዎች መካከልም አምልኮ ከርሱ በስተቀር ለማንም ለምንም እንደማይገባ ማመን፤ አላህ የምሉዕ ባህሪያት ባለቤት፣ ከጉድለት ሁሉ የራቀ /የነፃ/ ጌታ መሆኑን ማመን፤ ለሙእሚኖች መወገን፣ እነርሱን መውደድ፣ ለእነርሱ መርዳት፣ ለእነሱ ማዘን ግዴታ መሆኑን ማመን፤ ለዚህም አላህ እንዲህ ይላል፡-«የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ ሙሐመድ እና እነዚያ የእርሱ ጓደኞች በከሐዲያን ላይ ብርቱዎቹ በመካከላቸው ተዛዛኞች ናቸው፡፡ አጎንባሾች፣ ሰጋጆች ሆነው ታያቸ፡፡ ሁልጊዜም ከአላህ ችሮታንና ውዴታን ይፈልጋሉ፡፡ ምልክታቸው ከስግደታቸው ፈለግ ስትሆን በፊታቸው ላይ ናት፡፡ ይህ በተውራት የተነገረላቸው ፀባያቸው ነው፡፡ በኢንጅል ውስጥ የተጠቀሰው ምሳሌያቸው ደግሞ ቀንዘሉን እንደ አወጣ አዝመራና (ቀንዘሉን) እንዳበረታታው እንደ ወፍራምና ገበሬዎቹን የሚያስደንቅ ሆኖ አገዳዎቹ ላይ ተስተካሎ እንደቆመ አዝመራ ነው፡፡ ያበረታታቸውና ከሐዲያን በእርሱ ሊያሰቆጭ ነው፡፡ አላህ እነዚያን በእሱ ያመኑትንና ከእነርሱ በጎዎችን ተግባራት የሰሩትን ሁሉ ምህረትንና ታላቅ ምንዳን ቃል ገበቶላቸዋል». አል-ፈትህ 29 .




በአንፃሩም ለከሀዲያን አለመወገንና የእነሱን የሕይወት ፈለግ መቃረን ተገቢ ነው፡፡ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ኢብራሂም አባታቸውና ሕዝባቸው የአላህ ጠላቶች ሆነው በማግኘታቸው ለእነርሱ ከመወገን ተቆጥበዋል፡፡ እርቀዋቸዋልም፤ በማህበራዊ ኑሮ እንኳን ሳይቀር ተለይተዋቸዋል፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡- «ኢብራሂምና እነዚያ ከእርሱ ጋር አብረው የነበሩት ምዕመናን ለእናንተ መልካም አርአያ ናቸው፡፡ ይኸዉም ለህዝቦቻቸው እኛ ከእናንተና ከእዚያ ከአላህ ሌላ ከምትገዙት ጣዖታት ሁሉ ንፁሆች ነን፡፡ በእናንተም ካድን፡፡ በአላህ አንድ ብቻ ሲሆን እስከምታምኑ ድረስ በእኛና በእናንተ መካከል ጠብና ጥላቻ ዘወትር ተገለፀ፡፡ ባሉ ጊዜ ኢብራሂም ለአባቱ ፡- ለአንተ ከአላህ ቅጣት ምንም የማልጠቅምህ /የማላድንህ/ ስሆን ለአንተ በእርግጥ ምህረትን እለምንልሃለሁ ማለቱ ብቻ ሲቀር ጌታችን ሆይ በአንተ ላይ ተመካን ወደ አንተም ተመለስን መመለሻም ወደ አንተ ብቻ ነው»አል-ሙምተሒናህ- 4.

የዲነል ኢስላም መግቢያ በር የሆነው ተውሒድ የሚጠይቃቸው ዋና ዋና ግዴታዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡ ይህንን ተውሒድ፡- በእውነተኛ አምኖ፣ ከልቡ ተቀብሎ፣ በአንደበቱ የመሰከረና በተግባር ያረጋገጠ በአላህ ፈቃድ ጀነት ይገባል፡፡ ይህን ከላይ የተጠቀሰዉን መስፈርት ያሟላ ሰው ሁሉ የተለያዩ ኃጢያቶችን ሰርቶ ተውባህ ሳያደርግ ቢቀር እንኳን አላህ ሊምረው ወይም የጥፋቱን ያህል በጀሀነም ከቀጣው በኋላ ከእሳት አውጥቶ ጀነት ሊያስገባው ይችላል፡፡ በነቢያዊ ሐዲስ በተወራው መሠረት ነብዩ (ﷺ) ሙሳ (صلى الله عليه وسلم) አላህን የሚያመልኩበተ ልዩ ቃል እንዲሰጣቸው ሲጠይቁ አላህ "ሙሳ ሆይ ላኢላሀ ኢለሏህ በል" የሚል መልስ ሰጣቸው፡፡ እሳቸውም "ጌታዬ ሆይ! ይህንንማ ባሮችህ ሁሉ ይሉታል" አሉት፡፡ አላህ "ሙሳ ሆይ ሰባቱ ሰማይና ሰባቱ ምድር እንዲሁም በውስጣቸው ያለው ነገር በአንድ ሚዛን «ላኢላሀ ኢለሏህ» የሚለው ቃል ደግሞ በሌላ ሚዛን ቢቀመጡ ወይም ቢመዘኑ የላኢላሀ ኢለሏህ ሚዛን ይደፋል ወይም ይመዝናል" አላቸው፡፡ ነቢያችንም "በጣዕረሞት ላይ እያሉ የመጨረሻ ንግግሩ ላኢላሀ ኢለሏህ ያለ ጀነት ይገባል" ብለዋል፡፡



ባጠቃላይ ላኢላሀ ኢለሏህ የሚለውን የምስክር ቃል በአንደበት ብቻ መናገር በቂ አይደለም፡፡ ምክኒያቱም ከላይ እንዳየነው ሁሉ እውነት ሲባል በልብ ሰርፆ በአንደበት የሚነገር፣ በተግባር የሚተረጎም እንጂ በአንደበት መናገር ብቻ በቂ አይለም፡፡ ምክንያቱም ቅድመ ሁኔታዎቹን ሊሟሉለት የሚገባ ጉዳይ ነውና፡፡ አላህ እውነተኛና አንድ አምላክ መሆኑን፣ ኢባዳ ለርሱ ብቻ እንጂ ለሌላ ፍጡር የማይፈቀድ፣ ከእርሱ ሌላ ያሉት አማልክት ሁሉ ከንቱ /ባጢል/ መሆናቸውን፣ እነዚህ አማልክትም የማይጠቅሙና የማይጎዱ መሆናቸውን ማመን፣ ይህንኑ ሀቅ በእርግጠኝነት የማያሻማና መወላወል በሌለበት መልኩ በሚገባ ጠንቅቆ ማወቅና መረዳት፣ ይህን ተውሒድ እስከ መጨረሻው አጥብቆ መያዝ፣ ሁሉንም ሙስሊም የሚመለከቱ የአላህን ጌትነትና ብቸኛ አምላክነት የነቢዩ ሙሐመድን (صلى الله عليه وسلم) መልዕክተኛነት ወዶ በመቀበል ምስክርነቱ የሚጠይቀውን መስፈርት ሁሉ ተግባራዊ ማድረግ፣ የላኢላሀ ኢለሏህን ግዴታዎች ሁሉ መሥራት ለዚሁ ዓላማ ማደርና እውነተኛ ታማኝ መሆን፣ በዚህ ረገድ የሚከናወነውን ስራ ሁሉ ለሌላ ዓላማ ሳይሆን ለአላህ ፈቃድ ብቻ ማድረግ፣ አላህን መልክተኛውን (صلى الله عليه وسلم) እና ለአላህ ያደሩትንና እርሱን የሚገዙትን ሙዕሚኖች ሁሉ ከልብ መውደድ፣ በመጨረሻም አላህ ያዘዘውን ሁሉ መፈጸምና የከለከለውን ነገር ሁሉ መታቀብ፡፡ ከላይ የተጠቀሱትን በሙሉ ተግባራዊ ማድረግ ያለብን አላህን በመውደድ፣ ቅጣቱን በመፍራትና ምንዳውን ተስፋ በማድረግ፣ ምህረቱን በመከጀልና በዚህም የነቢያችን ሙሐመድን (صلى الله عليه وسلم)ተከታይነትን በማረጋገጥ ነው፡፡

ነቢዩ ሙሐመድም (صلى الله عليه وسلم) የነቢያት መደምደሚያ ሲሆኑ ይዘውት የመጡት ሸሪዓም ከሳቸው በፊት የተላኩት ነቢያት ያመጡትን ህግጋት /ሸሪዓ/ በሙሉ ያልተሻረዉን የሚያካትት የቀረዉን የሚሽር ነው፡፡ ምክንያቱም የርሳቸው ሸሪዓ ከእርሳቸው በፊት የወረዱትን ሸሪዓዎችና ይዘውት የነበረውን ትሩፋት /መልካም ነገሮች/ ሁሉ አጠቃሎ የያዘ በመሆኑ ነው፡፡ እናም ኢስላም የሁሉም ነቢያት አስተምህሮት በመሆኑ የሰው ዘር ሁሉ ሊከተለው የሚገባ ብቸኛ ሃይማኖት ነው፡፡ አላህ እንዲህ አለ፡- «ከኢስላም ሌላ ሃይማኖትን የሚፈልግ ሰው ሁሉ ፈፅሞ ከእርሱ ተቀባይነት የለውም፡፡ እርሱም በመጨረሻይቱ ዓለም ከከሳሪዎቹ አንዱ ነው በል፡፡ »



# የትክክለኛ አምልኮት መስፈርቶች

አላህ እንዲህ ‹‹ኢጋንንትንና ሰውን ሊገዙኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም፡፡ ከእነሱም ምንም ሲሳይ አልፈልግም፡፡ እንዲ መግቡኝም አልፈልግም፡፡ አላህ ሰጪና የብርቱ ሀይል ባለቤት ነውና››.አዝዛርያት 56. እንዳለው ሁሉ ጋኒንንም ሆነ ሰውን እሱን ብቻ እንዲያመልኩት ነው የፈጠራቸው፡፡ ክብራቸውና ማእረጋቸው የሚረጋገጥበትም በዚህ ስለሆነ ለአንድ አፍታም ቢሆን ሊተዉት አይገባም፡፡ አላህ ግን ከነሱም ሆነ ከአምልኮታቸው ቅንጣት ታህል ክጃሎት የለውም፡፡ ቁርኣን እንዲህ አለ ‹‹ሰዎች ሆይ ! በአላህ ብትክዱ አላህ ከእናንተ የተብቃቃ ነው፡፡ ››አዝ-ዙመር 7. እንዲህም አለ ‹‹ሙሳ፡- እናንተም በምድር ያለውም ሁሉ በመላ ብትክዱ አላህ ተብቃቂ ምስጉን ነው አለ፡፡›› ኢብራሂም 8.

አምልኮ አላህ በደነገጋቸው ተግባራትም ሆነ አንደበት አማካኝነት ወደ እርሱ መቃረብ ነው፡፡ ነብያት የተላኩት፤ መጽሃፍት የወረዱት፤ ይህንኑ እውነታ ለማስረዳት ነው፡፡ ቁርኣን እንዲህ አለ ‹‹በየሕዝቡ ሁሉ ውስጥ አላህን ተገዙ ጣዖታትን ራቁ በማለት የሚያስተምር መልዕክተኛን ልከናል፡፡ ከእነርሱም ውስጥ አላህ ያቀናው ሰው አለ፡፡ ከእነርሱም ውስጥ በእርሱ ላይ ጥመት የተረጋገጠበት ሰው አለ፡፡ እናም በምድር ላይ ኺዱ፡፡ የአስተባባዮችም መጨረሻ እንዴት እንደ ነበር ተመልከቱ›› አን-ነህል 36. እንዲህም አለ፡-‹‹መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ! ከአንተ በፊትም እነሆ ፤ ከእኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ በማለት ወደ እርሱ የምናወርድለት ቢሆን እንጅ ከመልዕክተኛ አንድንም አላክንም››አንቢያ 25. እነዚህን ሁሉ ትቶ ስሜቱ ባለው መንገድ አላህን እንኳን ቢሆን ያመለከ ሁል ከትክክለኛው መንገድ አፈንግጧል፡፡ ይህ ሰው አላህን አመለከ ሳይሆን የሚባለው ስሜቱን አመለከ ነው የሚባለው፡፡ ቁርኣን እንዲህ አለ ‹‹እሺ ባይሉህም የሚከተሉት ዝንባሌዎቻቸውን ብቻ መሆኑን ዕወቅ፤ ከአላህም የሆነ መምሪያ ሳይኖረው ዝንባሌውን ከተከተለ ሰው ይበልጥ የጠመመ አንድም የለም፤ አላህ በደለኞች ህዝቦችን አይመራምና ››አል ቀሰስ 50. አምልኮ በቁርኣንና በሃዲስ በተደነገጉ መሰረታዊ ህጎች ላይ ተመስርቶ ከተፈጸመ ብቻ ነው አላህ ዘንድ ተቀባይነት የሚኖረው፡፡ እናም አምልኮ ትክክለኛ አምልኮ ነው ለማለት ከዚህ በታች የተወሰኑት መስፈርቶች ያስፈልጉታል፡፡

አንደኛ፡- አምልኮት ከአላህ ወይም ከመልእክተኛው በመደንገግ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ ቁርኣን እንዲህ አለ‹‹ልክ እንደታዘዝከው ቀጥ በል ከአንተ ጋር ያመኑትም ቀጥ ይበሉ ወሰን

ንም አትለፉ እርሱ የምትሠሩትን ሁሉ ተመልካች ነውና» ሁድ 112. እንዲህም አለ «መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! ከዚያም ከሃይማኖቱ በትክክለኛው ሕግ ላይ አደረግንህ፡ ፡ ስለዚህ ተከተለው፡፡ የነዚያን የማያውቁትን ህዝቦች ዝን ባሌዎች አትከተል»አል ጃሲያ 18. ስለ ነቢዩ ﷺ ሲናገ ርም እንዲህ አለ«መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! የአላህ ግምጃ ቤቶች እኔ ዘንድ ናቸው አልላችሁም፡፡ ሩቅ ሚስጥ ርንም አላውቅም፡፡ መላዕክት ነኝም አልልም፡፡ ወደ እኔ የሚወርድልኝን መልዕክት ብቻ እንጂ ሌላን አልከተልም በላቸው፡፡ እውርና የሚያይ ይስተካከላሉን? አታስተነትኑ ምን! በላቸው፡፡» አል አንኣም 50.



ሁለተኛ፡- አምልኮቱ ከሽርክ መቀላቀል የጸዳ መሆን አለበት፤ ቁርኣን እንዲህ አለ «መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! እኔ አምላካችሁ አንድ አምላክ ብቻ ነኝ የሚል መል ዕክት ወደ እኔ የሚወረድልኝ መሰላችሁ ሰው ነኝ፡፡ እናም ከጌታው ጋር መገናኘት የሚፈልግ ሰው ሁሉ መልካም ሥራን ይሥራ፡፡ በጌታውም መገዛት ላይ አንድንም አያጋራ በላቸው» አል ከህፍ፡110.

መልካም ስራ ማለት ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል፡-«አላህ ውጫዊ አካላችሁን እና ገንዘባችሁን አይመለከትም፡፡ ግና ልቦናች ሁን እና ተግባራችሁን ነው የሚመለከተው»

አምልኮት የሽርክ ነገር አንዲት ነገር እንኳን ከተደባለቀ ባት ያፈርሰዋል፤ ቁርኣን እንዲህ አለ «በአላህ ባጋሩም ኖሮ ይሰሩት የነበሩት መልካም ተግባር ሁሉ ለእነርሱ በታበሰ ባቸው ነበር፡፡» አል አን ዓንም 88. ቁርኣን እንዲህ አለ መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ! አናንተ መሃይማን ሆይ ! ከአላህ ሌላን እንድገዛ ታዙኛላችሁን? በላቸው፡፡ መልዕ ክተኛችን ሙሐመድ ሆይ! ብታጋራ ስራህ በእርግጥ ይታ በሳል፡፡ በእርግጥም ከከሃዲዎቹ ትሆናለህ በማለት ወደ አንተና እኒያ ከአንተ በፊት ወደ ነበሩት ሰዎች በእርግጥ ተወርዷል፡፡ መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! ይልቅ አላህን ብቻ ተገዛም፡፡ ከአመስጋኞችም ሁን» አዝ-ዙመር 65-66. ሶስተኛ፡-አምልኮ ነብዩ (ﷺ) ባስተማሩትና በፈ ጸሙት መሰረት ብቻ መሆን አለበት፡፡ ቁርኣን እንዲህ አለ «ኢብራሂምና እነዚያ ከእርሱ ጋር አብረው የነበሩት ምዕመናን ለእናንተ መልካም አርአያ ናቸው »አል ሙምተ ሂና 4 .እንዲህም አለ«ከእናንተ መካከል አላህንና የመጨ ረሻውን ቀን ለሚፈራ ሰው ሁሉ እነርሱ መልካም አርአያ ዎች አሉለት» ሙምተሂና 6. እንዲህም አለ «እማኞች ሆይ ፣ከእናንተ መካከል አላህንና የመጨረሻውን ቀን ለሚፈራና አላህንም በብዙ ለሚያወሳ ሰው ሁሉ በአላህ መልዕክተኛ መልካም /መከተል/አርአያ አለለት» አል አህዛብ21.

እንዲህም አለ «መልዕክተኛው የሰጣችሁን ሁሉ ማንኛ ውም ነገር ያዙት፡፡ የከለከላችሁን ነገር ሁሉም ተከልከሉ» አልህሺር 7.ነቢዩ ﷺ «.የእኛ መመሪያን ባልተከተለ መልኩ የጠፈፀመ አምልኮ ሁሉ ተቀባይነት የለዉም.» ሙስሊም. ብለዋል፡፡ እንዲህም ብለዋል፡፡ነቢዩ ﷺ «እኔ እንደሰገድኩ ስገዱ.........» ብለዋል፡፡ ነቢዩ ﷺ «ሐጃችሁን ከኔ ተማሩ ..»ሙሰስሊም. ብለዋል፡፡አራተኛ፡-አንዳንድ አምልኮቶች በወቅት፤ በልክ የተገደቡ እና መጨመርም ሆነ መቀነስ የማ ይቻልባቸው አሉ፤ ለምሳሌ፡-


1-ሶላትን አስመልክቶ ቁርኣን እንዲህ አለ «...ሶላት በምዕመ ናን ላይ በጊዜያት የተወሰነች ግዴታ ናትና»አን ኒሳእ 103.

2-ሐጅን አስመልክቶ፡-ቁርኣን እንዲህ አለ «ሐጅ የሚፈፀ መው በተወሰነለት ወራት ዉስጥ ብቻ ነው» አል-በቀራህ 197

.3-ፆምን አስመልክቶ፡-ቁርኣን እንዲህ አለ «ከእናንተ መካከል ወሩን ያገኘ ሰው ይፁመው፡፡ በሽተኛ ወይም በጉዞ ላይ የሆነ ሰው ካፈጠረ ከሌሎች ቀናት ባልፆማቸው

ቀናት ልክ ቁጥሮችን (በልኩ) መፆም አለበት» አል በቀራ 185.

እነዚህ አምልኮቶች ከዚህ በላይ በተደነገጉት መሰረት እንጂ ከዚህ ውጪ በሆን ሰአታትና ስርአቶች ብንፈጽማ ቸው ተቀባይነት የለላቸውም፡፡



አምስተኛ፡- አምልኮት ሁሉ አላህን በመውደድና ለሱ በመ ተናነስ እሱን በመፍራትና ከሱ ተስፋ በማድረግ ላይ የተመ ሰረተ መሆን አለበት፡፡ ይህን አስመልክቶ ቁርኣን እንዲህ አለ «እነዚያ እነርሱ የሚገዟቸው እራሳቸው ማንኛቸውም ወደ አላህ በጣም ቀራቢ ለመሆን ወደ ጌታቸው መቃረቢ ያን ሥራ ይፈልጋሉ፡፡ » አል ኢስራእ 57. እንዲህም አለ «እነሱ በበጎ ስራዎች የሚቻኮሉ ከጃዮችና ፈሪዎች ሆነው የሚለምኑንም ነበሩ፡፡ ለእኛ የሚተናነሱም ነበሩ» አል አንቢያ 90. እንዲህም አለ «መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ !፡- አላህን የምትወዱ እንደሆናችሁ እኔን ተከተሉኝ፡ ፡ አላህ ይወዳችኋል ፡ ኃጢአቶቻችሁንም ለእናንተ ይም ራልና፡፡ አላህ መህሪ አዛኝ ነውና በላቸው፡፡ መልዕክተኛ ችን ሙሐመድ ሆይ!፡- አላህንና መልዕክተኛውን ታዘዙ፡፡ ብትሸሹም (ቢሸሹ) አላህ ከሃዲያንን አይወድም በላቸው»

ኣሊ ዒምራን 31-32. በዚህ አላህን መውደድ ምልክቱ ምን እንደሆነ ተመልክቷል፡፡ ከነብዩ ሙሐመድ (ﷺ)መንገድ ውጭ ሆኖ አላህን እወዳለሁ የሚል ሰው፤ አባባሉ ውሸት መሆኑንና ቁርኣንና ሱናን በመከተል የሙሐመድን ሸሪዓ በቃሉና በተግባሩ እስካልተከተለ ድረስ አላህን መውደድ እንደማይችል የሚደነግግ አንቀፅ መሆኑን ኢብኑ ከሲር ተናግረዋል፡፡ አላህንና ነብዩ ሙሐመድን (ﷺ) መውደድ ማለት ቃላቸውን በመፈፀመና ከከለከሉት በመታቀብ ለት ዕዛዛቸው ማደር ማለት ነው፡፡ የአላህ ሰዎችን መውደድ ማለት ደግሞ ምህረቱን ለእነርሱ መለገስ ማለት ነው፡ ፡ እናም አላህን የመውደድ ምልክት ቁርኣንን መውደድ ነው፡፡ ቁርኣንን የመውደድ ምልክት ደግሞ ነብዩ ሙሐ መድን (ﷺ)መውደድ ነው፡፡ ነብዩ ሙሐመድን (ﷺ) መውደድ ደግሞ ሱናቸውን መከተል ነው፡፡ ስለዚህም አላህን መውደድ እውን የሚሆነው የእርሱ መልዕክተ ኞችን መታዘዝና ፈለጋቸውን በመከተል ብቻ ነው፡፡ አይሁዶች እኛ የአላህ ወዳጆች እና ልጆቹ ነን በማለ ታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው፡፡ ዋሂዲ፡፡ በነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ዘመን የተወሰኑ ሰዎች አላህን እንወዳ ለን በማለታቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው፡፡ ከነጅራን የመጡ ክርስቲያኖች እኛ ዒሳን የምናከብረው እና የምን ገዛው አላህን ለመውደድና ለማክበር ስንል ነው በማለታ ቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው፡፡ በመካ የሚገኙ ጣዖታ ትን የምንገዛው ወደ አላህ እንዲያቃርቡን ነው በማለታ ቸው ነው ይህ አንቀፅ የወረደው፡፡ አላህ የአላህን መውደድ ምልክቶችንና ውጤቶቹን ነግሮናል፡፡ ምልክቶቹ መልክ ተኛውን መከተል፤ አላህን መታዘዝ እና መልዕክተኛውን መታዘዝ ናቸው፡፡ ፈሬዎች ደግሞ የአላህን ውዴታ ማግኘ ትና ምህረቱን ማረጋገጥ ከእዝነቱም ተስፋ ማድረግ ነው፤ ስድስተኛ፡-አምልኮት ለአቅመ አዳም ከደረሱ አንስቶ እስከ እለተ ሞት ድረስ አይቆምም፤ ቁርኣን እንዲህ «እናንተም ሙስሊሞች ሆናችሁ እንጂ አትሙቱ»ኣሊ ኢምራን 102. እንዲህም አለ «መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! እውነ ቱም ነገር/ ሞት/ እስኪመጣልህ ድረስ ጌታህን ተገዛ»አል ሂጅር 99.

አምልኮ ብዙ አይነት ነው ምክንያቱም አምልኮ ማለት አላህ

የሚወዳቸውና የሚደሰትባቸውን ተግባራትም ሆነ አንደበቶች ዉጫዊም ሆነ ዉስጣዊ የሚያጠቃልል በመሆኑ ነው፡ ፡ ለምሳሌ ሶላት፤ ዘካ፤ ፆምና ሀጅ ከአምልኮ ተግባራት ዋና ተግባራት ናቸው፡፡ የኢስላም ማእዘናትም ናቸው፡፡ እንደዚሁም መልካም ስነ ምግባርና መልካም ባህሪያት ከአምልኮ ባህሪያት ዉስጥ ናቸው፡፡ ለምሳሌ እውነት መናገር፣ ተአማኒነት፣ ለወላጆች ደግ መሆን፣ ዝምድናን መቀጠል፣ ቃልን ማክበር፣ መልካም ምክር መምከር፣ በደግ ማዘዝ፤ ከመጥፎ መከልከል፣ ጅሃድ፣ ለጎረቤት፤ ለየቲም እና ለምስኪን ደግ መዋል፣ ለእንሰሳ ማዘን፤ ድዓ ፤ዚክር፤ ቁርአን መቅራት፤ የልብ ተግባራት፤ ማለትም አላህን መውደድ፤ መልክተኛውን መውደድ፤ አላህን መፍራትና ወደ እርሱ መመለስ፣ አምልኮትን ለሱ ፍጹማዊ ማድረግ፤ ለውሳኔው መታገስ፣ ለጸጋው ማመስገን፤ ቀደሩን መቀበል፣ በሱ ላይ ብቻ መመካት፣ ከረሀመቱ ተስፋ ማድረግ፤ ከቅጣቱ መፍራት እና ሌሎችም የዲን ተግባራት ሁሉ የአምልኮት ተግባራት አካል ናቸው፡፡ በአካል ከሚፍጸሙ ተግባራት

የአምልኮ ተግባራት መካከል ሶላት ነው፡፡ ቁርአን እንዲህ አለ «ስገድ፤ ወደ አላህም ተቃረብ»፡፡አል አለቅ 19. ነቢዩም እንዲህ አሉ «የሰው ልጅ ወደ ጌታው በጣም የሚቀርብበት ወቅት ሱጁድ ባደረገበት ቀወቅተ ነው፡፡ እናም ዱዓ አብዙ...». ሙስሊም. ኢንዲህም አሉ «ማንም ሰው ሶላት ላይ ሲቆም ከጌታው ጋር ነው የሚነጋገረው» ቡኻሪ. ሆኖም ይህ ሶላት ዛሬ ዛሬ ብዙዎች ዘንድ ክብደቱ ቀንሷል፡፡ ቁርአን እንዲህ አለ «ከእነሱም በኋላ ሶላትን ያጎደሉ ከንቱ ፍላጎቶችንም የተከተሉ መጥፎ ትውልዶች ተተኩ፡፡ ገይ የሚባልን የገሀነምንም ሸለቆ በእርግጥ ያገኛሉ፡፡ ግና ከእነሱ የተፀፀቱ በአላህ ያመኑ በጎንም ስራ የሰሩ ሰዎች ወደ ገነት ይገባሉ፡ ፡ አንዳችንም አይበደሉም»መርየም 59-60. እዚህ ላይ በጣም የሚገርመው ጉዳይ ደግሞ አንዳንድ ሰዎች

በትርፍ ጉዳዮች ላይ በጣም ሲሯሯጡ ሶላትን ግን ችላ ብለው መታየቱ ነው፡፡ ለምሳሌ ሶላትን ሳይሰግዱ ብዙ ሶደቃዎችን የሚሰጡ፤ ዘካን በትክክል ሳይሰጡ ዑምራ ንና ሐጅን ሲደጋግሙ የምናያቸው ፤ ወላጆቹን ሳይቀር ቤተሰብን እያበሳጩ ለዉጭ ሰው መልካም የሚመስሉ ብዙ ናቸው፡፡ ነቢዩ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ የፍትሃዊነትን ግዴታነት እንዲህ በማለት «አዋጅ ! ሁላችሁም እረኞች ናችሁ፡፡ ሁሉም ከተጣለበት ሀላፊነት ተጠያቂ ነው» አስተምረዋል፡፡ ለቤተሰብ ከሚደረጉ እንክብካቤዎች መካከል ዋናው በበጎ ነገር ማዘዝና ከመጥፎ ነገር መከልከል ዋናው ነው፡፡ በሶላት ላይ እንዲጠነክሩ ፤ከሙዚቃ፤ ከመጥፎ ፊልሞችና ድራማዎች እንዲርቁ ፤በመጥፎ አስተሳሰብ ላይ እንዳይገቡ ጎጂ ሱሶችን እንዳይለምዱ መጠበቅ ነው፡፡ ሆኖም አንዳንድ አባቶች እነዚህን ነገሮች በገነዛ እጃቸው እያመጡ ለቤተሰብ ጠንቅ የሚሆኑ አሉ፡፡ ትክክለኛ የአላህ ባሪያዎች ግን ቤቶቻቸዉን በዒባዳ ያንፃሉ፡፡ ቤተሰቦቻቸዉን በዒባዳ ላይ አርአያ በመሆን ያበረታታሉ፡፡ ቁርአን እንዲህ አለ (እነዚያ ለጌታቸው በግንባራቸው ተደፊዎችና ቋሚዎች ሆነው የሚያድሩት ሰዎች ናቸው፡፡ እነዚያ ጌታችን ሆይ! የገሀነምን ቅጣት ከእኛ ላይ መልስልን ቅጣቷ የማያልቅ ነውና፡፡ የሚሉት ናቸው» አል ፉርቃን 64-66.

በይበልጥም አላህን ቤተሰቦቻቸዉን እንዲያስተካክልላቸው ጧት ማታ ይለምናሉ፡፡ ቁርአን እንዲህ አለ «እነዚያ ጌታችን ሆይ ! ከሚስቶቻችንና ከዘሮቻችን ለዓይኖች መርጊያን ለእኛ ስጠን አላህን ለሚፈሩትም መሪ አድርገን የሚሉ ናቸው»



አልፉርቃን 74.

አምልኮ በአጭር የሚገደብ ጉዳይ አይደለም:: የምላስን እንቅስቃሴ፣የልብን ዝንባሌ፤ የአካልን ተግባራት ሁሉ ሌላውቀርቶ መብላት መጠጣት እና መተኛት እንኳን ሳይቀር ዒባዳ ከታሰበበት ዒባዳ ይሆናል:: የወሴብ ግን ኙነት እንኳን በሐላሉ ከሐራም ለመጠበቅ ከታሰበበት አጅር አለው። ይህን በተመለከተ የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ አሉ <<ጥቂት የአላህ መልዕክተኛ ሰሓባዎች ለነቢዩ ‹የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ሃብታሞች በምንዳ በለጡን፣ እኛ እንደምንሰግደው ይሰግዳሉ፤ እኛ እንደምንፆመው እነሱም ይፆማሉ፤ ከሃብታቸው ትሩፋትም ይመፀውታሉ› አሏቸው:: (ነብዩም) እንዲህ ሲሉ መለሱላቸው:- "አላህ ለናንተስ የምትመፀዉቱትን አላደረገላችሁምን? በእርግጥ እያንዳንዱ ተስቢሕ (አላህን ማጥራት) ምፅዋት ነው:: እያ ንዳንዱ ተክቢር (የአላህን ትልቅነት ማውሣት) ምፅዋት ነው:: እያንዳንዱ ተሕሚድ (አላህን ማመስገን) ምፅዋት ነው:: እያንዳንዱ ተህሊል (የአላህን አንድነት ማውሳትም) ምፅዋት ነው:: አንዳችሁ የሐላል (ሕጋዊ) ግብረ-ሥጋ ግን ኙነት ቢያደርግ ይህም ምፅዋት ነው::" "ሰሐቦችም አንዳ ችን የግል ስሜቱን ቢያረካ እንዴት በሱ ምንዳ ያገኛል?" ሲሉ ጠየቁ:: ነብዩም "አንድ ሰው በብልቱ ሐራም (ሕገ-ወጥ) ቢሠራ ወንጀል አይሆንምን? እንደዚሁም በብልቱ ሐላል (ሕጋዊ) ግብረ-ሥጋ ግንኙነት ቢያደርግ ምንዳ ያገኝ በታል" አሉ:: (ሙስሊም ዘግበውታል).

እንዲህም አሉ "ፀሀይ በወጣችበት ቀን ሁሉ የማንኛውም ሰው መገጣጠሚያዎች ሰደቃ (ምፅዋት) ማቅረብ አለባ ቸው:: በሁለት ሰዎች መካከል በትክክል ብትፈርድ ሰደቃ ነው:: አንድን ሰው በመጓጓዣው ላይ ብታወጣው፣ ዕቃው ንም ብትጭንለት ሰደቃ ነው:: መልካም ንግግርም ሰደቃ ነው:: እያንዳንዷ ወደ ሶላት የምታመራ እርምጃም ሰደቃ ነች:: ከመንገድ ላይ ጎጂ ነገሮችን ማስወገድም ሰደቃ ነው "(ቡኻሪና ሙሰሊም).

## ዒባዳዎችን ከሚያበላሹ ወይም ከሚያጎሉ ነገሮች

መጠንቀቅ ግድ ነው:: ይህም ማለት:-

1-ከሺርክ መራቅ ነው::

2-ከቢድዓ መጠበቅ ያስፈልጋል::

3-ሰዎችን ከመበደልም ራስን መጠበቅ የግድ ነው:: ይህ ካልሆነ ግን ነቢዩ « ከሰዎች መካከል የቂያማ እለት እን ደጋራዎች የገዘፉ ስራዎችን ይዘው የሚመጡና አንዱን ደብድቦ፤ ሌላዉን ሰድቦ፤ ሌላዉን ገንዘብ በልቶ የሚመ ጣና ከዚያም ለዚህኛው ከመልካም ተግባሩ ፤ለዚያናዉም እንዲሁ ተነስቶ ይወሰደበታል:: በጎ ተግባሩ በደሎቹን ሳይ ከፍሉ ካለቁ ደግሞ ከተበዳዩች ወንጀሎች ተነስቶ በሱላይ ተጭኖ ወደ ጀሀነም ይወረወራል» እንዳሉት ነው የሚሆ ነው::

4-እንደዚሁም በድንገት ከሚያመልጡ መጥፎ ንግግ ሮች መጠንቀቅ ግድ ነው:: ነቢዩ ﷺ «አንድ ሰው ምንም ትኩረት ሳይሰጠው አላህን ከሚያስቀይሙ ንግግሮች በተ ናገረው ምክኒያት ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ካለው ርቀት ያራቀ በጀሀነም ዉስጥ እንድ ሚወረወር ነግረዉናል::

5-ምቀኝነትን መራቅ ግድ ነው:: ምክኒያቱም ነቢዩ ﷺ «ምቀኝነት የበጎ ተግባርን ወሮታዎች እሳት ሳርን እንደሚበ ላው ሁሉ ይበለዋል» ብለዉናል:: ስለዚህ የአምልኮ መስ ፈርቶችን በትክክል በመረዳት በጥንቃቄ መፈፀምይኖርብ ናል:: ይህ ካልሆነ ግን የልፋታችን ዋጋ አላህ እንዳለው «መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ፤በሥራዎች በጣም ከሳ ሪዎቹን እንንገራችሁን ? በላቸው:: እነዚያ እነሱ ሥራን የሚያሳምሩ የሚመስላቸው ሲሆኑ በቅርቢቱ ህይወት ሥራቸው የጠፋባቸው ናቸው:: እነዚያ እነርሱ በጌታቸው ማስረጃዎችና በመገናኘቱ የካዱት ናቸው ሥራዎቻቸውም ተበላሹ:: ለእነርሱም በትንሳኤ ቀን ሚዛንን አናቆምላቸ ውም:: ነገሩ ይህ ነው:: በክህደታቸው አንቀፆቼንና መል ዕክተኞቼንም መሳለቂያ አድርገው በመያዛቸው ፍዳቸው ገሀነም ነው» አል ከህፍ፡ 103-106.

እንዳለው እና መልዕክተኛው (ﷺ) ሙሰሊም በዘገቡት ሐዲስ «ማንም ሰው በጉዳዮችን ላይ በኢስላም ከርሱ ያል ሆነን አዲስ ነገር ካመጣ አዲሱ ነገር ውድቅ ነው» እንዳሉት ሁሉ ከሳራ ይሆናል» አላህ ከከሳራ ይጠብቀን::

# የክህደትና የሽርክ አደገኝነት

ክህደትና ሽርክ በአላህ ዘንድ በጭራሽ አይማርም፡፡ የወንጀሎቹ ሁሉ አደገኛውም ክህደትና ሽርክ ነው፡፡ በቁርኣንና በሐዲስ ዉስጥ በብዛት ከተጠቀሱት ወንጀሎች ዋና ዋናዎች ክህደትና ሽርክ ናቸው፡፡

ሀ-ክህደት

ክህደት ማለት፡-የአላህን ህልዉና መኖር ሙሉ በሙሉ የካደ፤ ወይም ከስሞቹ ወይም ከባህሪያቱ ወይም ከተግ ባሩ አንዱንም ቢሆን የካደ፤ ወይም በነቢያት ላይ ካወረዳ ቸው መፅሐፍት ከፊሉንም ቢሆን ወይም የአምልኮት ተግ ባራት፤ ወይም ከኢማንም ሆነ ከኢስላም ማዕዘናት አንዱ ንም ቢሆን የካደ፤ ለምሳሌ መልዕክትን የካደ፤ ወይም ሞቶ መነሳትን፤ ወይም ጀነትን ወይም እሳትን፤ ወይም ግዴታ ከሆኑት የአምልኮ ተግባራትም ሆነ ሌሎችንም መለኮታዊ ህግጋትን ማስተባበል፤ ለምሳሌ ሶላትን መካድ፤ ወይም ዘካን፤ ወይም ሐጅን፤ ወይም ዝምድና መቀጠልን፤ ወይም የዝሙትን ሐራምነት፤ ወይም የኸምርን ሐራምነት፤ የዉ ሼትን ሐራምነት፤...በዚህ መልኩ የካደ ሁሉ ስሙ ከሃዲ ነው፡፡ ከዚያም ይህ ሰው ከአላህ ምህረት የማገኘት እድል የለዉም፡፡ የሙስሊሙ ማህበረሰብም አካል አይደለም፡፡ የክህደትን አደገኝነት ከሚጠቁሙ የቁርኣን አናቅፅ መካከል አላህ እንዲህ አለ፡-

1- «እነዚያ የካዱት ሰዎች ግን ረዳቶቻቸው ጣኦታት ናቸው፡፡ ከብርሃን ወደ ጨለማ ይመሯቸዋል፡፡ እነዚያ የእሳት ጓዶች ናቸው፡፡ እነርሱ በውስጧ ዘውታሪዎች ናቸው» አልበቀረህ 254.

2-እንዲህም አለ፡- (ከሓዲያንም ለእነርሱ ብርቱ ቅጣት አለ ላቸው፡፡) አሹራ 26.

3-እንደዚህም አለ፡-«መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! እነዚያ በአላህ ብቸኛ አምላክነት፣ በአንተ መልዕክተኛነትና በአላህ አንቀፆች የካዱ ሰዎች ሁሉ ብታስጠነቅቃቸውም ባታስጠነቅቃቸውም ለእነርሱ ሁሉም እኩል ነው፡፡ ምንም ለውጥ አያመጣም አያምኑምና፡፡ አላህ እነዚያ እውነትን እያወቁ የካዱ ሰዎችን በልቦቻቸው ላይና በመስሚያቸው ላይ አትሞባቸዋል፡፡ በዓይኖቻቸው ላይም መሸፈኛ አለ፡ ፡ ለእነርሱ በሲኦል ውስጥ ከባድ ቅጣት አለባቸው) አል በቀረህ 6.

4-እንደዚህምአለ «እነዚያ በአላህና በመልዕክተኞቹ የሚክዱ፤ በአላህና በመልዕክተኞቹም መካከል መለየትን የሚፈልጉና በከፊሉም እናምናለን በከፊሉ ደግሞ እንክዳ ለን የሚሉ ሰዎች ሁሉ በዚህ መካከል መንገድን ሊይዙ የሚፈልጉ፡፡ እነዚያ በእውነቱ ከሐዲያን እነርሱ ብቻ ናቸው፡፡ ለከሐዲያንም አዋራጅን ቅጣት አዘጋጅተናል» አን-ኒሳእ 151.

5-እንዲህም አለ «ከኢስራኤል ልጆች መካከል እነዚያ በአላህ የካዱ ክፍሎች በዳውድና በመርየም ልጅ በዒሳ ምላስ«መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ! ከእነርሱ መካከል ብዙዎቹን ከእነዚያ በአላህ ከካዱት ሰዎች ጋር ሲወዳጁ ታያለህ፡፡ በእነርሱ ላይ አላህ የተቆጣባቸው በመሆኑ ለእ ነርሱ ነፍሶቻቸውን ያስቀደሙት ስራ በጣም ከፋ! እነርሱ በጥፋት ውስጥ ዘወታሪዎች ናቸው» አልማኢደህ 80.

ከሃዲያን አመፀኞች ለመሆናቸው ቁርኣን እንዲህ ይላል፡፡ (...ከዚያም በኋላ በሱ የካዱ ሰዎች እነዚያ አመፀኞች ማለት እነሱ ብቻ ናቸው) አን-ኑር 55.

6-ከሃዲያን የግፈኞች ሁሉ ግፈኞች እንደሆኑ በመግ ለፅ (በዳዮች ማለት ከሐዲያን ብቻ ናቸው)

5- ወደ ገሀነም እንደሚነዱ፡-መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ!ለእነዚያ በአላህ ለካዱ ሰዎች በቅርብ ጊዜ ትሸነፋ ላችሁ፡፡ ከእዚያ ገሀነም ትሰበሰባላችሁ፡፡ ምንጣፊቱም ገሀነም ምን ትከፋ በላቸው፡፡ 3፡12-13.

6-መመለሻቸው ገሀነም እደሆነ፡-መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! የእነዚያ በአላህ የካዱ ሰዎች በየሀገሮች መንፈላሰስ አይግረምህ፡፡ አነስተኛ ጥቅም ነውና፡፡ ከእዚያ መኖሪያቸው ገሀነም ናት፡፡ ገሀነም ደግሞ ማረፊያነቷ ምን ትከፋ። ኣሊ ዒምራን፡196-198.

8-የአላህ ጠላት መሆናቸዉን በግልፅ ማወጅ፡-.እነዚ ያ በአላህ የካዱ ሰዎች ይህንን ቁርኣን አታዳምጡ ታሸን ፉም ዘንድ ሲነበብ በእሱ ውስጥ ተንጫጩ አሉ፡፡ እነዚያ ንም በአላህ የካዱ ሰዎች ብርቱን ቅጣት እናቀምሳቸዋለን፡ ፡ የዚያም ይሰሩት የነበሩትን መጥፎውን ምንዳ እንመነዳ ቸዋለን፡፡ ይህ የአላህ ጠላቶች ፍዳ ነው፡፡ እሳት በውስጧ በእነርሱ የዘላለም መኖሪያ አገር አላቸው፡፡ በአንቀፆቻቸው ይክዱ በነበሩት ምንዳ ይመነዳሉ፡፡ 41፡ 26-28

8-ከአላህ የሚደበቁ አለመሆናቸዉም፡-.እነዚያ አንቀፆቻች ንን የሚያጣምሙ በእኛ ላይ አይደበቁም፡፡ የሚያጣምምና በእሳት ውስጥ የሚጣለው ሰው ይበልጣልን ? ወይስ በትን ሳኤ ቀን ፀጥተኛ ሆኖ የሚመጣው ሰው ? ያሻችሁትን ስሩ ዋጋችሁን ታገናላችሁ፡፡ እርሱም የምትሰሩትን ሁሉ ተመ ልካች ነውና፡፡

ለ-ታላቁ ሽርክ ነው፡፡ እሱም ፡-ለአላህ በሩቡብያ፤ በኡ ሉህያ እና በአስማ ወሲፋቱ ላይ አጋርን ማበጀት ነው፡ ፡ ማለትም ከአላህ ውጪ ያለ አካል ወይም ከአላህ ጋር፤- ፈጣሪ፣ ሊመለክ የሚገባው አካል፤ አልያም እሱን በስም እና በባህሪ የሚመሣሠለው አለ ብሎ ማመን ሢሆን ይህንን እምነት ያራመደው ግለሠብ ሁሉ ሙሽሪክ ይባላል። ሆኖም ሽርክ በሶስት ይከፈላል፡-እነሱም፡- ትልቁ ሽርክ፣ ትንሹ ሽርክ እና ድብቁ ሽርክ ናቸው።

የትልቁ ሽርክ ትርጉም ፡- ከአላህ ውጪ ያለ አካል (ነብይ ንም ፣መላይካም ፣ ወልይም...) ከአላህ ጋር (በውዴታ ፣ በፍራቻ ፣ በመታዘዝ እንዲሁም በሌሎች የኢባዳ ክፍሎች) እኩኩል ማድረግ ነው፡፡

## የታላቁ ሽርክ አይነቶች

1-በሩቡብያው ማጋራት ሲሆን፡-እሱም ከአላህ ውጪ ወይም ከአላህ ጋር ፈጣሪ፣ ነገራቶችን የሚያስተናብር፣ የሚሠጥ፣ የሚጎዳ፣ የሚጠቅም... አለ ብሎ ማመን፤ ወይም የአላህን ፈጣሪነት፣ መጋቢነት ፣ተንከባካቢነት ... ማስተባ በል ነው፡፡ ይህም ትልቁ ሽርክ ይባላል ይህ የሽርክ አይነት በሁለት መልኩ ሊከሠት ይችላል፡፡

1 የአላህን ጌትነት ሙሉ በሙሉ ከአላህ መሻር ነው፡፡ ይህ የሽርክ አይነት ከተወሡኑ ሠዎች በቀር ሌላው ህብረተሠብ ላይ የሚስተዋል የሽርክ አይነት አይደለም፡፡

2 -የአላህን ፈጣሪነት አምኖ ከአላህ ጋር ሌሎች ፈጣሪዎች፤ ተንከባካቢዎች አለ ብሎ በማሠብ ከአላህ ውጪ ያሉ አካ ላትን እንደ መልዐክ፤ ነቢያት፤ ቀብር፣ ጣኦት እና ለመሣ ሠሉ ለአላህ ብቻ መሠጠት የነበረበትን አምልኮ አሣልፎ መስጸት ነው፡፡ ከአላህም ጋር እኩል ሙብት እንዳላቸው አድርጎ ማሰብ ነው፡፡ ይህ የሽርክ አይነት ዛሬ ላይ አንዳንድ ሙስሊም ነን ብለው ከሚሞግቱ ግለሠቦች ዘንድ ሣይቀር የሚገኝ የሽርክ አይነት ነው የተለያዩ ወልይ ብለው የሚ

ያስቧቸው ሠዎች ቀብር ጋር በመሄድ ሪዝቅ እንዲያሠፉላቸው፣ ልጅ እንዲሠጣቸው፣ ከመጥፎ እንዲጠብቃቸው ጥሩ ነገር እንዲሠጣቸው... ይለምኗቸዋል፡፡ ይህም ከአላህ ውጪ ልጅ የሚሠጥ፣ የሚጠብቅ፣ ሪዝቅ የሚያሠፋ አለ ብሎ ከማሠባቸው የተነሣ ነው፡፡

2 በስም እና በባህሪያት ማጋራት ነው፡፡ ይህንንም የሽርክ አይነት በሁለት ከፍል መመልከት እንችላለን፡-

- ትርጉም አልባ በማድረግ ወይም በማራቆት ሲሆን፡- አላህ ስለራሡ የተናገረውን እና በመልዕክተኛው አንደበት እንዲደርሠን ያደረገውን ስሞቹና ባህሪያቱን እንደተባለው አምኖ መቀበል የከበዳቸው አንዳንድ ጠማማ አንጃዎች የአላህ ስምና ባህሪያትን ይመሣሠልብናልን በሚል ስጋት ከአላህ እንደሻሩት ማለት ነው፡፡

-በስሙ እና በባህሪው ለአላህ አምሣያን (ቢጤን) በማበጀት ፡- አላህ እራሡ የተነጠለበትን ስም እና ባህር ከእርሡ ፍጥረት ጋር የሚያመሳስል ነው፡፡

3 በአምልኮ ማጋራት፡- ይህን የሽርክ አይነት ለሦስት ከፋፍለን መመልከት እንችላለን።

ስለ ሺርክ አስከፊነት አላህ እንዲህ ብሏል፡፡

1-«መስጊዶች የአላህ ብቻ ናቸው፡፡ በመሆኑም ከአላህ ጋር ማንንም አታምልኩ» (አል-ጅን 18)

2-«ጌታችሁ አላህ ይህ ነው፡፡ ንግሥና የርሱ ብቻ ነው፡፡ እነዚያ ከርሱ ሌላ የምታመልኳቸው ቅንጣት ያህል ኃይል የላቸውም፡፡ ብትጠሯቸውም ጥሪያችሁን አይሰሙም፡፡ ቢሰሟችሁም ምላሽ አይሰጧችሁም፡፡ የትንሳኤ ቀንም የናንተን ማጋራት ይከዳሉ፡፡ (የሰው ልጅ ሆይ) ሁሉንም ዐዋቂ እንደሆነው አምላክ አድርጎ ማንም አይነግርህም» (ፋጢር 13-14)

3-«ከአላህ ጋር ሌላን አምላክ የሚያመልክ ለዚህ (ድርጊቱ) (ቅንጣት) መረጃ የለውም፡፡ ምርመራውም ከጌታቸው ዘንድ ነው፡፡ እነሆ ከሐዲያን ስኬትን ፈጽሞ አያገኙም» (አል-ሙእሚኑን 117) ይህን መልእክት ያዘሉ የቁርአን አንቀጾችብዙናቸው፡፡ ይህ ድርጊት የቁረይሽ ከሐድያንና የሌሎች የጥንት ጣኦታውያን ድርጊት ነው፡፡ አላህ መልእክተኞችን ሁሉ የላከውና መጽሐፍትን ያወረደው ይህን የሽርክ ተግባር ለማስጠንቀቅ ነው፡፡

4-መልዕክተኞችን አላህን ብቻ እምልኩ ጣዖታትንም ተከልከሉ» (የሚል መልዕክት አስይዘን በሁሉም ህዝቦች ውስጥ በእርግጥ ላክን»(አል-ነህል 36)

አላህ በነዚህ አንቀጾች መልእክተኞችን የላከውና መጽሐፍትን ያወረደው የሰው ልጆች በብቸኝነት እንዲያመልኩትና ሌላን አካል በአምልኮ ማለትም በዱዓ እገዛ በመጠየቅ፤ በመፍራት፤ ተስፋ በማድረግ፤ በሶላት፤ በጾም፤ በእርድና በሌሎችም ኢባዳዎች እንዳያጋሩ ነው፡፡ የቁረይሽ ጣኦታውያንና ሌሎችም ለመልክተኞችና ለሌሎች የእውነት ተጣሪዎች ወልዮችን ወደ አላህ እንዲያቃርቡን እንጅ እና መልካቸውም ይሉ እንደነበር ነግሮናል፡፡ ይህም ማለት ወደ አምላክ ያቃርቧቸዋል፤ አማላጅ ይሆኗቸው ዘንድ አመለኳቸው እንጅ ይፈጥራሉ፤ ሲሳይ ይለግሳሉ ፤ፍጥረተአለሙን ይመራሉ ያሰማራሉ የሚል እምነት አልነበራቸውም፡ ፡ አላህ ግን ይህ እምነታቸው ሐሰት መሆኑን በመግለጽ ከሐዲነታቸውን አረጋግጧል፡፡

አላህ እርሱ ብቻ እንዲለመን አዟል፡፡ የሚለምኑትንም ለመስማት ቃል ገብቷል፡፡ ከዱዓ የሚኩራሩትን የተዋረዱ ሆነው ጀሃነም እንደሚገቡዝቷል፡፡«ጌታችሁ፤- «ጥሩኝ፤ለጥሪያችሁ ምላሽ እሰጣለሁ፡፡ እነዚያ እኔን ከማምለክ የኮሩት ገሃነም ውስጥ የተዋረዱ ሆነው በእርግጥ ይገባሉ፡፡ »ብሏል፡፡ (ጋፊር 60)

የአላህ መልእክተኛ በሐዲሳቸው ዱዓ ኢባዳ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ለኢብን አባስ እንዲህ ብለዋቸዋል፡-‹አላህን ጠብቀው ይጠበቀሐል› አላህን ጠብቀው ከፊት ለፊትህ ታገኘዋለህ፡፡ስትለምን አላህን ብቻ ለምን፡፡ እገዛ ስትሻም አላህን ብቻ ጠይቅ፡፡ (ቲርሙዚና ሌሎችም ዘግበውታል) ‹ለአላህ ባላንጣ የሆነን አካል እየተማፀነ የሞት እሳት ገባ› (ቡኻሪ)

ቡኻሪና ሙስሊም እንደዘገቡት ነቢዩ ‹ከወንጀሎች ሁሉ ትልቁ የትኛው ነው ? ተብለው ተጠይቀው ‹ለአላህ ባላንጣ ማድረግ ሲሉ መልሰዋል፡፡

ከአላህ ውጪ ሌላን አካል የተማፀነና እገዛውን የጠየቀ፣ ለዚህአካልየተሳለ፣ ያረደለት ወይም ከኢባዳዎች መሀከል አንዱን ለእርሱ ያዋለ የአላህ ባላንጣ አድርጎ ይዞታል፡ ፡ ነቢይ፤ ወልይ፣ ንጉስ፤ ጋኔን፤ ጣኦት ወይም ሌላ ነገር ሊሆን ይችላል፡፡ በህይወት ያለን ሰው አንዳች ቁሳዊና ተጨባጭ እገዛን መጠየቅ ግን ሽርክ አይሆንም፡፡ የተፈ ቀደነገርነው፡፡ አላህ በሙሳ ታሪክ ውስጥ እንዲህ በማለት እንደገለፀው፡-‹‹ያ የርሱ ወገን የሆነው ከጠላቶቹ ወገን ከሆነው ሰው (ጥቃት) ያግዘው ዘንድ ጠየቀው፡፡ (አል ቀሶስ 15) እንዲህ ብሉዋል፤-(ከፉ ነገር እንዳይደርስበት) እየፈራ (እና) እየተጠባበቀ ከተማዋን ለቆወጣ፡፡ *(አል ቀሶስ 21) ሰውየው በጦርነትም ሆነ በሌላ ነገር በወንድሙ መታገዙ የተለመደና ተቀባይነት ያለው ነው፡፡ ሰዎች እርስ በርስ ይደጋገፉሉ፡፡ አንዱየሌላውን እገዛ ይሻል፡፡ የአላህ መልእክተኛ ማንንም መጥቀምም ሆነ መጉዳት እንደማይ ችሉ ይገልፁ ዘንድ አላህአዙዋቸዋል፡፡ እንዲህ ብሉዋል፤- ‹‹ሙሐመድሆይበል ‹‹እኔ የማመልከው ጌታዬን ብቻ ነው፡፡ በርሱ አንድንም(ኃይል)አላጋራም›› በልም፡‹‹እናንተን መጉ ዳትም ማቅናትም አይቻለኝም፡፡ (አልጅን 20-21) ‹‹አላህ ከሻው በቀር ራሴን መጥቀምም ሆነ መጉዳት አልችልም፡ ፡ ሩቅ ምስጢሮችን የማውቅ ቢሆን ኖሮ መልካም ነገሮችን በብዛት በፈፀምኩ፤ከፉ ነገርም ባላገኘኝ ነበር፡፡ እኔ (ከሐዲ ያንን) አስጠንቃቂና አማኞችን አብሳሪ ብቻ ነኝ›› በላቸው›› (አልአእራፍ 188) ይህን መልእክት ያዘሉ አንቀጾች በርካታ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለቱን ወንጀሎች እየፈፀመ የሞተ ሰው ከጀነት ተስፋ የለዉም፡፡

ሀ- የጥሪ (የልመና ሽርክ) (( ከአላህ ውጪ ያለን አካል ጥሩን ነገር ያስገኛል አልያም መጥፎን ነገር ያስወግዳል በሚል እሣቤ መለመን ሽርኩል አክበር በመባል ይጠራል፡ ፡ አላህ እንዲህ ሢል መልእክተኛውን ይገስፃል” ከአላህ ውጪ የማይጠቅምህ እና የማይጎዳህን አትጣራ ይህንን ከሠራህ አንተ ከበደለኞች ነህ “ በሌላም አንቀፅ እንዲህ ይላል “ከአላህ ውጪ ያለን አካል ከሚጣራ ይበልጥ የጠመመ ማን ነው ? “

በዚሁ ስር ከሚካተቱት አንዱ በንያ ማጋራት ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል « የዱንያን ህይወት እና ጌጣጌጥዋን ለሚ ፈልግ ሠው የስራቸውን (ምንዳ) እሥ ውስጠ እንሞላላቸ ዋለን። እነሡም በሦ (በዱንያ) ውስጥ ምንም የሚጎድል ባቸው አይደሉም ፤ እነዚያ እነሡ በመጨረሻይቱ አለሞ ከእሣት በስተቀር ምንም የላቸውም ። በሦም ውስጥ የሠሩት ስራ ተበላሸ። በቅርቢቱ አለም የሠሩት ስራ ውድቅ ነው » ።((ሁድ 15 –16)

**የትዕዛዝ ሽርክ** ፦ ይህም የሽርክ አይነት ሠዎች አላህ ያዘዘውን ነገር ፤የተከለከለን ነገር ሢያደርጉ ወይም አላህ የከለከለውን የሚፈቀድ ሢያደርጉ የአላህን ማዘዝ እና መከ ልከል ወደ ጎን ትቶ የነሡን መቀበል ማለት ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል ‹‹ቀሳውስቶቻቸውና እና ባህታዊያኖቻቸ ውን ከአላህ ውጪ ጌቶች አድርገው ያዙ ፣ የመርየም ልጅ መሢህም አንድን አምላክ ሊገዙ እንጂ አይደለም የታዘዙት ከእርሡ በቀር በእውነት የሚመለክ አምላክ የለም እነሡ ከሚያጋሩት የጠራ ነው)ተውባ 31. ይህም ማለት ለአዲይ ኢብኑ ሀቲም አልተገዛናቸውም እኮ ብሎ በጠየቃቸው ግዜ እነሡን መገዛት ማለት አላህን እያመፁ እነሡን መታዘዝ ነው ብለው እንዳብራሩት እንጂ እነሡን መለመን ማለት አይደለም፡፡

## በትንሹ ሽርክ እና በትልቁ ሽርክ መካከል ያለው ልዩነት ፦

ትንሹ እና ትልቁን ሽርክ አንድ የሚያደርጋቸው ነገር ሁለቱም ለአላህ የሚገቡ መብቶችን ከሡ ውጫ ላለ አካል አሣልፎ መስጠት መሆኑ ነው ፡፡

★ የሚለያቸው ደግሞ፦ ትልቁ ሽርክ በተውበት እንጂ እን ደማይማር ሁሉም ኡለሞች አንድ አይነት አቋም ሲይዙ በትንሹ ሽርክ ላይ ግን ሁለት አይነት አቋም አላቸው ፡፡ እነሡም፦

1 የአላህ ፍላጎትውስጥ ይገባል.፤

2 በወንጀሉ ልክ ይቀጣል ትልቁ ሽርክ ስራን በአጠቃላይ ያበላሻል ትንሹ ሽርክ ግን በሡአቱ የተሠራውን የሽርክ ስራ ብቻ ነው የሚያበላሸው ፤

3-ትልቁ ሽርክ ከኢስላም ያስወጣል ትንሹ ግን አያስወጣም

4- ትልቁ ሽርክ እሣት ውስጥ ያዘወትራል ትንሹ ግን አያ ዘወትርም ፤

5-ትልቁ ሽርክ ደም እና ገንዘብ ሀላል ያደርጋል ትንሹ ደግሞ በተቃራኒው የሽርክ አደገኝነትን አስመልክቶ አላህ እንዲህ ብሏል፡"አላህ እርሱ ጋር ተጋሪ መደረጉን ፈፅሞ አይምርም፡፡ ከዚህ በታች ያሉትን ጥፋቶች ግን ለሚሻው ሰው ይምራል"(አን-ኒሳእ 48).

-እርሡን በብቸኝነት እንድናመልከው እና ከእርሡ ውጪ ሌላን አካል እንዳንገዛ ከገለፀባቸው አናቅፆች መካከል ((አላህን ተገዙ በሡም ቅንጣት ታክል እንዳታጋሩ))

-ፍጡርን የፈጠረው እሱን በብቸኝነት እንዲያመልኩት መሆኑን በመናገር ከገለፀባቸው አንቀፆች መካከል ((የሡ ውንም ልጅ ሆነ ጋኔንን እኔን ሊገዙኝ እንጂ አልፈጠርኳ ቸውም)

3-መልዕክተኞችን የላከበትን ምክንያት በመናገር (በእርግጥ ወደ ሁሉም ህዝቦች አላህን ተገዙ ጣኦትንም እራቁ የሚሉ መልዕክተኞችን ልከናል))

4-በመፍጠሩ ብቸኛ በመሆኑ በመመለኩም ብቸኛ እንደ ሆነ በመናገር« ለፀሀይ እና ለጨረቃ አትስገዱ ለዛ ለፈጠራ ቸው አላህ ስገዱ »

5-በስም እና በባህሪው ብቸኛ በመሆኑ በመመለኩም ብቸኛ መሆኑን በመናገር «ለአላህ መልካም የሆኑ ስሞች አሉት በእነርሡም ለምኑት»

6- ከእርሡ ውጪ የሚመለኩ አማልክቶች ደካማ መሆና ቸውን በመናገር እናንተ ሠዎች ሆይ! ምሣሌ ተደረገላችሁ ለሡም አድምጡት እነዚያ ከአላህ ውጪ የምትለምኗቸው ቢሠባሠቡ ዝንብ መፍጠር አይችሉም ዝንብ የሆነ ነገር ቢወስድባቸው ማስጣል አይችሉም የሚለመነውም የሚለ ምነውም ደካማ ነው

7-ከእርሱ ውጪ ያለን አካል የሚገዙትን ሠዎች ጅል መሆ ናቸውን በመናገር «ከአላህ ውጪ የማይጠቅማችሁን እና የማይጎዳችሁን ትገዛላችሁን? ለእናንተ እና ከአላህ ውጪ ለምትገዟቸው "ኡፍ! " አትገነዘቡምን?»

8 የሙሽሪኮች መጨረሻ የከፋ መሆኑን በመናገር «የቂያማ ቀን እናንተ በማጋራታቹ (ተጋሪዎች) ይክዳሉ እንደ ውስጥ አዋቂው ማንም አይነግርህም» በማለት እና ሌሎች መንገ ዶችንም በመጠቀም አላህ በብቸኝነት መመለክ እንዳለበት እንዲሁም ከሡ ውጪ ያሉ አካላትን ማምለክ እንደሌለ ብን ያስተምረናል፡፡

## ከትንሹ ሽርክ ምሳሌዎች

ከንግግራዊ - ከአላህ ውጪ ባለ መማል; አንተና አላህ ከፈ ቀዳችሁ ብሎ መናገር ይመስል ነው፡፡

ከተግባራዊ ፡-በገድ ማለት ማመን; ወደ ጠንቋይ ዘንድ መሔድ; ህርዝን ማንጠልጠል ይመስል ነው፡፡

ከልባዊ፡-እዩልኝ እና መሠሎቹ;ናአው፡፡ ሆኖም ትንሹ ሽርክ ከእምነት ጋር ከተቆራኘ ወደ ትልቁ ሽርክ የሚሸጋገርበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

ተውሒድን ማረጋገጥና የላኢላሃ ኢለላህን መስፈርቶች ማሟላት ግዴታ እንደሆነብን ሁሉ ሽርክን መፍራትና በየ ትኛውም መንገድ እንዳያጠቃን መጠንቀቅ ግድ ይለናል፡፡ የሽርክ ዓይነት ሁሉም ትልቁም ትንሹም ትልቅ በደል ነው፡ ፡ አላህ ሁሉንም ወንጀሎች ይምራል ሽርክ ሲቀር፡፡ ከሽርክ ላይ የወደቀ አላህ ጀነትን እርም አድርጎበታል፡፡ መኖሪያ ውም እሳት ነው፡፡ እናም እምነትን የሚንዱ ጉዳዮች ብዙ በመሆናቸው በዚህ አጭር ፁሐፍ ማጠቃለል ባይቻልም

ከዚህ በታች ያሉትን እንመልከት ፡፡

1-ከነሐስ፣ ከመዳብ፣ ከብረት ወይም ከቆዳ የተሰራን አንዳች ነገር መከራን ለመከላከል፤ ወይም ለማስወገድ ሲሉ በአካል ላይ ወይም በሰዉነት ላይ ማንጠልጠል ሽርክ ነው፡፡

2.ሸሪዓዊ መሠረት የሌለውን መንፈሳዊ ሕክምና (ሩቃ) ማድረግ ወይም ማስደረግ፣ እንዲሁም መንፈሳዊ ሕክምና የሚባለው ትርጉም አልባ ፅሑፎችን፤ ወይም ግልጽ መል ዕክት የሌላቸውን ቃላት ያካተተ፤ ወይም ደግሞ በሽታን ለማስወገድም ይሁን ድግምትን ለማስፍታት በአጋንንት መታገዝ፤ ወይም ሂርዝን ማንጠልጠልን ሁሉ ያጠቃል ላል፡፡ ሂርዝ ማለት ከሰው ወይም ከእንስሳት ላይ የሚን ጠለጠል መሠረት አልባ ንግግሮች የተፃፉበት የቁርአንና የሐዲስ ቃላት የተከተቡበበት የሚንጠለጠል ነገር ሲሆን ይህ ሁሉ ለሽርክ ምክንያት ይሆናል ከሚባሉ ነገሮች አንዱ ነው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡፡"ሩቃ፣ ሂርዝና መስተፋቅር ሽርክ ናቸው" አህመድና አቡዳውድ.


3-ከሰው ዓይን ወይም ከክፉ ነገር ይከላከላል በሚል እምነት የአላህን ስም ወይም አያተልኩርሲ የሰፈረበትን ቁራጭ ወረቀት፣ ወይም ነሐስን፤ ወይም ብረትን ማን ጠልል ወይም ከመኪና ውስጥ ማስቀመጥ የሽርክ አካል ነው፡፡ በመዳፍ ውስጥ የተፃፈ የቁርኣን መልዕክት፣ ወይም ደግሞ የአይን ስዕል የሰፈረበትን ነገር ማስቀመጥም እንዲሁ የሰው ዓይን ይከላከላል የሚል እምነት ከታከለበት ሽርክ ይሆናል፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ﷺ እንዲህ ብለዋል:-"አንዳ ች ነገርን ያንጠለጠለ ሰው ሁሉ ለርሱው ይትተዋል"(አህ መድ፣ ቲርሚዚና ሐኪም)

## የሽርክ ክፉነት

ሽርክ የበደሎች ሁሉ ትልቁ በደል ነው፡- ምክኒያቱም በደል ማለት ፡-አንድን ነገር ያለ ቦታው ማስቀመጥ ማለት ነው። አሁንም አላህ ብቻውን ፈጥሮ ሌላን ምንም ያልፈጠረን አካል ከአላህ ጋር አስጠግቶ ከማምለክ በላይ የባሰ ምን በደል አለና አላህ እንዲህ ይላል «ሽርክ ታላቅ በደል ነው» (ሉቅማን 13)

ሽርክ ምህረት የሌለው እርኩስ ወንጀል ነው፡-ከሽርክ በታች ያሉ ወንጀሎች ምንም ያክል የበዙ ቢሆኑም እንደ አላህ ፍላጎት ይወሠናሉ ለፈለገው ይምራል የፈለገውን ደግሞ ይቀጣል፡፡ ሽርክ ግን አማራጭ ውስጥ የሚገባ አይ ደለም ((ምህረት የሚባል ነገር የለውም)) አላህ እንዲህ ይላል «አላህ በሱ የሚያጋራውን አይምርም ከሽርክ ውጪ ያለውን ለሻው ሠው ይምራል» (አን-ኒሣእ 48)

ሽርክ መልካም ስራን ያብሣል፡፡ ስለዚህ ጉዳይ አላህ እንዲህ አለ፡፡ «በእርግጥ ወደ አንተና ከአንተ በስተፊት ወደ ነበሩት መልዕክት አስተላለፍናል ብታጋራ ስራህ በሙሉ ከአንተ ይታበሣል ከከሰሩትም ትሆናለህ» (ዙመር 65).





# የሶላት ክብደት በኢስላም

ሶላት በኣላህና በኛ መካከል ያለው ዋናው መገናኛ ችን ነው፡፡ ሶላት የቋንቋ ትርጉሙ፡- ፀሎት; መለመን; መማፀን ማለት ሲሆን ሃይማኖታዊ ትርጉሙ ግን በአላሁ አክበር ተጀምሮ በአሰላሙ አለይኩም የሚጨረስ የአምልኮ ተግባር ነው፡፡

ሶላት አላህ በሰዎች ላይ ግዴታ ካደረጋቸው ዋና ዋና ጉዳዮች መካከል አንዱ ከመሆኑም በተጨማሪ ከሁለቱ የምስክር ቃላት በመቀጠል በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ የኢስላም ማእዘን ነው፡፡

ሶላት ባሪያን ከፈጣሪው ጋር የሚያገናኝ ጠንካራ መስመር ነው፡፡ በውስጡ አያሌና ወሳኝ የሆኑ የባርነት መገለጫዎች አሉት፡፡ በሶላት ውስጥ ባሪያው ጌታውን በግልፅ ቃል ይለ ምናል፡፡ በሚስጥርም ከሱ ጋር ያወራል፡፡ በምርጥ ቃላት እርሱን ያወድሳል፡፡ በስረዐቱ ሂደትም ባሪያው የነፍሱን ማንነት በግልጽ ያስታውስበታል፡፡ የዚህችን አለም እውነታ በትክክል ይረዳበታል፡፡

የዚህ አይነቱ ሶላት ሲጋጁ በአላህ ህግጋትና ድንጋጌዎች ላይም ፅኑ እንዲሆን ያስችለዋል፡፡ እናም ከግፍ፤ ከዝሙት፤ ከሀሜት፤ከአሉቧልታ፤ እና ከመሳሰሉት፤ ፀያፍ ተግባራት እንዲርቅ ያስተምረዋል፡፡ አላህ በቁርአን ይህንን ሁኔታ እንዲህ ሲል ይገልፀዋል፡፡ «መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ! ከመጽሐፉ ወደአንተ የተወረደውን አንብብ፡፡ ሶላት ንም ደንቡን ጠብቀህ ስገድ፡፡ ሶላት ከመጥፎና ከሚጠላ ነገር ሁሉ ትከለክላለችና፡፡ አላህን ማውሳት ከመልካም ነገር ሁሉ በላጭ ነው፡፡ አላህም የምትሠሩትን ስራ ሁሉ ያውቃል» ” አል-ዐንከቡት 45”

ኢማሙ ማሊክ በሙወጦ ሸንደዘገቡት ኡመር ኢብን አል ኸጣብም ወደ የግዛታቸው በጻፉት አንድ ደብዳቤ ላይ “ከሁሉ ነገራችሁ ሁሉ የሚያሳስበኝ ጉዳይ የሶላት ጉዳይ ነው፤ ሶላትን በደንብ ጠብቆ የሰገደ ሁሉ ዲኑን በደንብ ጠብቋል፡፡ ሶላትን ያጓደለ ሰው ግን ሌሎችን ለማጓደሉ አያ ጠራጥርም” /“ሶላትን የተወ ሰው በኢስላም ምንም ድርሻ የለውም” /ብለዋል።

የሰዎች ከኢስላም ድርሻቸው ከሶላት ባላቸው ድርሻ ልክ ነው፡ ፡ ወደ ኢስላም ያላቸው ፍላጎት ከሶላት ባላቸው ልክ ነው፡፡ የግዴታ ሶላቶችን አያወቁ መተው ከታላላቅ ወንጀ ሎች ማለትም ከዝሙት፣ ከሌብነት፣ ወዘተ ሁሉ የበለጠ በመሆኑ በሙስሊሞች መካከል ምንም ልዩነት የለም፡ ፡ ከዚያም አልፎ ከኢስላም ውጭ ይሆናል በሚል ላይ ከፍተኛ ሙግት አለ፡፡ ይህንኑ አቋም አያሌ የቁርአንና የሀዲስ ማስረጃዎች እያጣቀሱ ህዝብን የሚያስተምሩ አንቱ

የተባሉ እውቅ አሊሞች ብዙ ናቸው:: ቢያንስ ቢያንስ ሰዎች የሶላትን ነገር በከባድ ደረጃ እንዲያዩትና እንዲተገብሩት በሃይለኛው ያሳስባሉ:: ወቅቱንና ስርአቱን ጠብቀው እንዲሰግዱ ይገፋፋሉ:: አላህ በቁርአን እንዲህ አለ« «ነፍስ ሁሉ በሰራችው ስራ ተያዥ ናት:: እኒያ መዝገባቸውን በቀኝ እጃቸው የሚሰጡት ብቻ ሲቀሩ:: እነርሱማ በገነቶች ውስጥ ሁነው እርስ በራሳቸው ከአመፀኞች ሁኔታ ይጠያየቃሉ:: ከዚያም ለእነርሱ እንዲህ ይሏቸዋል::« በሰቀር ውስጥ ምን አገባችሁ ? ከሰጋጆች አልነበርንም:: ለድሆችም የምናበላ አልነበርንም:: እርግጠኛው ነገር ሞት እስከመጣብን ድረስ ከዘባራቂዎችም ጋር እንዘባርቅ ነበር:: በፍርዱ ቀንም እናስተባብል ነበርና ነው ይላሉ:: »ሱረቱል -ሙደሲር 38-47”

እንዲህም አለ «ሆኖም ቢፀፀቱ፣ ሶላትን በደንቡ ቢሰግዱና ግዴታ የሆነባቸውን የዘካ ምጽዋትን በትክክል ከሰጡ መንገዳቸውን ልቀቁላቸው:: አላህ መሀሪ፤ አዛኝ ነውና»አል-ተውባ 5.

ነብዩ ሙሐመድ(ﷺ)ካለፉ በኋላ አቡበክር ኸሊፋ ሲሆኑ፤ከዐረቦች መካከል በአላህ ካመነው ክፊሉ አላህን ካደ፤ ክፊሉ ደግሞ ዘካን ከለከለ ። እናም አቡበክር ጦርነት ሲያዉጁባቸው ዑመር «አቡበክር ሆይ! የአላህ መልዕክተኛ(ﷺ)ሰዎች ከአላህ በስተቀር አምልኮት የሚገባው አምላክ የለም እስኪሉ ድረስ እጋደላቸው ዘንድ ታዝዣለሁ:: ከአላህ በስተቀር አምልኮት የሚገባው አምላክ የለም ያለሰው ንብረቱንና ሕይወቱን ከኔጠብቋል:: ሌላው መተሳሰቡግን በአላህ ላይነው» አሉ::

ዑመርም «ሰዎችን እንዴት ትጋደላለህ?» ሲሉጠየቋቸው:: አቡበክርም «በአላህ እምላለሁ !» በሶላትና በዘካ መካከል ልዩነትን የፈጠረን ሁሉ እዋጋዋለሁ:: በእርግጥ ዘካ ገንዘባዊ ግዴታ ነው:: በአላህ እምላለሁ ለአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ይሰጡት የነበረውን የግመል ማሰሪያ ገመድ እንኳን ቢከለክሉኝ እሷን በመከልከላቸው እጋደላቸዋለሁ»አሉ:: ዑመርም «በአላህ እምላለሁ! በእርግጥ አላህ የአቡበክርን ልቦና ለመጋደል እንዳሰፋ ከመመልከት በስተቀር ሌላ ነገር አላየሁም:: እኔም እሳቸው የወሰኑት ውሳኔ ትክክል መሆኑን አረጋገጥኩ» ሲሉ ተናሩ:: ቁርኣን እንዲህም አለ «ሙስሊሞችሆይ ! ቢፀፀቱ፤ሶላትንም ደንቡን አሟልተው ቢሰገዱና ግድ የሆነባቸውንም ዘካን በትክክል ቢሰጡ የእምነት ወንድሞቻችሁ ናቸው:: ለሚያውቁ ህዝቦች ሁሉ አንቀጾችን እናብራራለን » አልተውባህ 11.

ኢብኑ ዘይድ:- አላህ ሶላትንና ዘካን በአንድ ደነገገ:: በመሐላቸውም በምንም አልለየም:: ሶላትን ያለ ዘካ በምንም መልኩ አይቀበልም:: አቡ በክር አላህ «በጌታዬ ይሁንብኝ በነብዩ ሙሐመድ (ﷺ)ጊዜ ይከፍሉት ከነበረው አንዲት ገመድ እንኳን ቢከለክሉኝ ጦርነት አውጅባቸዋለሁ» አሉ::

-ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ ዑመር እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል:-«ኢስላም በአምስት መሰረቶች ላይ ታንጿል:: እነርሱም ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለና ሙሐመድም የአላህ መልዕክተኛ መሆናቸውን መመስከር፤ ሶላትን በወቅቱ መስገድ፤ ዘካን መስጠት፤ ሐጅ ማድረግና ረመዷንን መፆም ናቸው» ::

ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ ቡረይደት እንዳስተላለፉት ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:- «በኛና በነርሱ በሙናፊቆች መካከል ያለው ቃል ኪዳን ሶላት ነው እርሷን የተዋት በእርግጥ ካደ» ::

ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ ሸቂቅ ኢብኑ ዐብደላህ የተባለ ታላቅ ታቢዒይ እንዲህ ብለዋል:-«የነብዩ (ﷺ) ባልደረቦች ከስራዎቹ መካከል አለመፈፀሙን እንደ ክህደት የሚያዩት ተግባር ሶላት ብቻ ነበር» አላህ እንዲህም አለ « ከእነሱም



በኋላ ሶላትን ያጎደሉ ከንቱ ፍላጎቶችንም የተከተሉ መጥፎ ትውልዶች ተተኩ »መርየም 59.

እንዲህም አለ «ለእነሱ ስገዱም በተባሉ ጊዜ አይሰግዱም፡ ፡ ለአስተባባዩች ሁሉ በዚያ ቀን ወዮውላቸው»አል-ሙርሰላህ 48-49.

ነቢዩ እንዲአሉ "በሰው ልጅ እና በክህደት ወይም በሽርክ መካከል ያለው ነገር ሶላት መተው ብቻነው" ቡረይዳህ በዘ ገቡት ሃዲስ "በኛና በነሱ መካከል ያለው ኪዳን ሶላት ነው፤ ሶላትን የተወ ሰው በአላህ ክዷል" አህመድና ትርሚዚ፣ ከአነስ ኢብኑ ማሊክ በዘገቡት ሃዲስ "ሶላታችንን የሰገደ ወደቂብላችን የዞረ ያረድነውን የተመገበ ሁሉ ሙስሊም ማለት እሱ ነው ከዚያም ልክ እንደ ነባር የሙስሊሞች መብቶችም ሆኑ ግዴታዎች ይኖሩታል" ቡኻሪ.

በዚሁ ጉዳይ ከሶሃቦች ብዙ ተዘግቧል ከነዚህም መካከል ኢብኑ መስኡድ "ነገ ከአላህ ሲገናኝ ሙስሊም መሆን የፈለገ ሰው ሁሉ እኒህ ሶላቶችን በተጠሩበት ቦታና ጊዜ ይስገድ አላህ ለመልክተኛው ቅን መንገዶችን ደንግጎለ ታል፡፡ እነዚህ ሶላቶችም የዛው አካል ናቸው፤ ያ በየቤቱ እንደሚሰግዳቸው በየቤታችሁ ብትሰግዷቸው የነብያች ሁን ሱና ትነቅፋላችሁ የነብያችሁን ሱና ብትነቅፉ ደግሞ ትጠማላችሁ...."ብለዋል።

በጀማዓ ባለመስገድ ይህ ከሆነ ቅጣቱ ሶሃቦች ሙናፊቅ ብለው የሚቆጥሩት ከሆነ አላህ ይጠብቀን እና በጭራሽ የሚተወው ሰውስ ቅጣቱ ምን ሊሆን ነው? ስለዚህ በኢ ስላም የሶላት ክብደት ከፍ ያለ ነው፡፡ ለዚህም ይመስላል አላህም ሶላትን ለነብዩ(ﷺ)ያስተማራቸው ያለምንም መል ክተኛ በዚያው ሚዕራጅ በወጡበት በሰማይ ቀበሌ ነው፡ ፡ ሆኖም በብዙ ሰዎች ዘንድ የሶላት ክብር እየቀነሰ መጥ ቶዋል፤ በጭራሽ የማይሰግዱ ሲኖሩ ሌሎች ቢሰግዱትም እንኳን ስርኣተደንቡን የማያሟሉ ብዙ ናቸው፡፡ ሌሎች ደግሞ በየቤታቸው እየሰገዱ የጀመዓ ነገር የማያጅባቸው ጥቂት አይባሉም፡፡ ነገር ግን ይህ ተግባር በሰሃቦች ዘንድ የሙናፊቆች ተግባር ይባል የነበረ ነው። ስለዚህ ሁላችንም ይህን የተከበረ የእምልኮ ተግባር ጠንክረን ልንተገብረው ግድ ይለናል፡፡ከእኒያ አመፀኞች ካላቸው ቡድኖች ተግባር መጠንቀቅ አለብን። አላህ በቁርአን « ሙስሊሞች ሆይ ! ሶላቶችን በተለይ መካከለኛይቱን የአስርን ሶላት ወቅታቸ ውንና ስርዓታቸውን ጠብቃችሁ ስገዱ፡፡ በሙሉ ታዛዥ ነትም ለአላህ ቁሙ» "አልበቀራህ 238" እንዳለው መሆን ይገባናል፡፡



መካከለኛይቱን የሚለው የዐስርን ሶላት ማለት ነው የሚሉ ከፍሎች ብዙ ናቸው፡፡ የአላህመልዕክተኛ(ﷺ)ቡኻሪ በዘ ገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡- «የዐስርን ሶላት ሆን ብሎ ያሳለፈ ሰው ልክ ቤተሰቡንና ሀብት ንብረቱን እንዳጣ ሰው ነው፡፡ »

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡአል-መሊሕ እንዲህ ብለዋል፡- «ደመና በሆነበት አንድ ዘመቻ ላይ ከአቡረዳህ ጋር ሳለን «የዐስርን ሶላት በወቅቱ ስገዱ፤ ምክንያቱም የአላህ መልዕ ክተኛ «የዐስርን ሶላት የተወ ሰው መልካም ስራዎቹ በርግጥ ተበላሽተዋል» ብለዋል» አለን፡፡

ኢስላም ከእያንዳንዳችን ሶላትን ለብቻው በግሉ እንዳይሰ ግደው እና በመስጂድ ከህዝቡ ጋር እንዲሆን አላህ ኢንዲህ ይላል « ሶላትን ደንቡን ጠብቃችሁ ስገዱ፡፡ ዘካንም ለተ ገቢው አካል ስጡ፡፡ ለጌታችሁም ከአጎንባሾች ጋር አጎን ብሱ፡፡ ከሰጋጆች ጋር ስገዱ»



## በሶላት ዉስጥ መመሰጥን አስመልክቶ

በሶላት ዉስጥ መመሰጥ የሶላት እውነተኛ መገሰጫና አንኳር ነጥብ ነው:: መመሰጥ ማለት አንድ ሰጋጅ በሶላት ዉሰጥ የተናነሰና እራሱን ዝቅ ያደረገ ሆኖ የሚያነበዉን የቁርአን አንቀፅ ያሎቱንና ዉዳሴን በሕሌናው እያስተነተነ አላህ ፊት መቆሙ ነው::


መመሰጥ ከአምልኮዎች ሁሉ በላጩና የላቀ የታዛዥነት መገለጫ ነው:: ሁዘይፋ የንፍቅናን መተናነስ ተጠንቀቁ ሲሉ ይህ ማለት ምን ማለት ነው ብለው ጠየቋቸው ሽና እሳቸውም ሲመልሱ አካሉን ስትመለከቱ የፈራ የሚመስል ውስጡ ግን የማይፈራ ነው:: ሁዘይፋ በሌላ ጊዜም ለመጀመሪያ ከዲናችሁ የምታጡት ነገር ኹሹዕ ነው ብለዋል::

ኹሹዕ የሚያስፈልገው የአምልኮ ተግባር ሁሉ ምንዳው በኹሹዑ ልክ ነው:: ለምሳሌ ሶላት:: ነቢዩ ሙሐመድ ሶላት የሚሰግድ ሰው (አንዳንድ ሰው ሰግዶ ምን አልባትም ከሶላቱ ዉስጥ አስረኛው፤ወይም ዘጠነኛው ፤ወይም ስምንተኛው ፤ወይም ሰባተኛው፤ወይም ስደስተኛው፤ወይም አምስተኛው፤ ወይም አራተኛው፤ወይም ሶስተኛው፤ ወይም ግማሹ እንጂ የሌለው ይኖራል) ብለዋል::

ከቶውንም ጭራሽ ኹሹዕ በማጣቱ ምንም የማይኖረው አለ:: ከሌብነቶች ሁሉ ከፉው ሌብነት የሶላት ሌብነት ነው:: ነቢዩ (ከሌቦች ሁሉ አስከፊው ሌባ ከሶላቱ የሚሰርቅ ሰው ነው:: የአላህ መልዕክተኛ እንዴት ከሶላቱ ይሰርቃል ! ሲሏቸው ሩኩዑን እና ሱጁዱን አለመሙላት ነው ብለዋል):: አህመድ.

በሶላት ዉስጥ መረጋጋት ግዴታ ነው:: ያለሱ ሶላት ሁሉ ባጢል ነው:: ነቢዩ ያን በሶላቱ ያጠፋዉን ሰው ሲመክሩት (ወደ ሶላት ስትቆም አላሁ አክበር በል፤ከዚያም ከቁርአን የቻልከዉን ያክል አንብብ፤ ከዚያም አካሎችህ እስከሚረጋጉ ድረስ ሩኩዕ አድርግ፤.......) ብለዋል:: ቡኻሪና ሙስሊም .

መረጋጋት ማለት በሩኩዕ፤ በሱጁድ፤ እና በሌሎችም የሶላት ተግባራት አካላቶቻችን እስከሚረጋጉ ድረስ መቆየት ነው:: በመሆኑም በሶላት ዉስጥ አለመረጋጋት እንደሌብነት ከመቆጠሩም በላይ ዋናው ሌብነት ነው:: እያንዳንዱ የሶላትን ተግባራት ግዴታቸዉን ብቻ ሳይሆን የሚወደዱትንም አሟልቶ መስገድ ከዚህ መከራ ያድናል:: በሩኩዕና በሱጁድ ሰዓት አካላቶቻችን እስከሚረጋጉ ድረስ መቆየትን አስመልክቶ የተዘገቡ ሐዲሶች ብዙ ናቸው ከላይ የተጠቀሱት ለአብነት ያክል ነው ::




# ዱዓ

በአላህ ዘንድ የዱዓ ክብር ከባድ ነው፡፡ ጥቅሙም ሰፊ ነው፡፡ በዲንም የተሰጠው ክብር ወደር የለሽ ነው፡፡ ፀጋዎችን ለማግኜት ፍቱን መንገድ እሱው ነው፡፡ ከላያችን ላይ ክፉ ነገሮችን ለማስወገድም ዋና አማራጭ ነው፡፡ ይህም የሆነበት ዱዓ የአላህን የአምልኮ ብቸኝነት የሚያጠቃልል በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ በመቀጠል ስለ ዱዓ አንዳንድ ነገሮች ለአንባቢያን ቀርቧል፡፡

ሀ-ዱዓ ማለት የአላህ አገልጋይ የሆነ ሁሉ ጌታዉን መጠየቅ ማለት ነው፡፡

## ለ-የዱዓ አስፈላጊነት

ሁሉም ፍጡር ወደ አላህ ከጃይ ነው፡፡ እሱ ዘንድ ያለው ነገር ያስፈልገዋል፡፡ እሱ ደግሞ ከፍጡሩ ሁሉ የተብቃቃ ነው፡፡

## ሐ-የዱዓ ቱሩፋቶች

ዱዓ ብዙ ቱሩፋቶች፤ አያሌ ፍሬዎች እና ድንቅ ድንቅ ሚስጥሮች አሉት፡፡ ከነዚህም መካከል

1-ዱዓ የአላህ ትእዛዝ ነው፡፡ አላህ ባሮቹን (ጌታችሁም አለ፡፡ ለምኑኝ እቀበላችኋለሁና፡፡....) ጋፊር:60 በማለት እንዲለምኑት ግዴታ አድርጓል፡፡

2-ዱዓ ዒባዳ ነው፡፡ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ (ዱዓ ዒባዳ ነው) ብለዋል፡፡

3-ዱዓ ከኩራት በሺታ ነፃነት ነው ፡፡ አላህ ባሮቹን እንዲህ አለ(እነዚያ እኔን ከመለመን የሚኮሩት ተዋራጆች ሆነው ገሀነም ይገባሉ) ጋፊር:60. ብልዋልና።

4-ዱዓ አላህ ዘንድ ክብር ካላቸው ነገሮች ሁሉ ዋናው ነው፡፡ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) አህመድና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ (አላህ ዘንድ ከዱዓ የበለጠ ክብር ያለው ምንም ነገር የለም) ብለዋል፡፡

5-ዱዓ የአላህን ቁጣ ለመከላከል ዋና ምክኒያት ነው፡፡ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) አህመድ በዘገቡት ሐዲስ (አላህ ያለመነዉን ሰው ሁሉ ይቆጣበታል) ብለዋል፡፡

6-ዱዓ በአላህ ላይ ብቻ መመካትን ያመለክታል፡፡

7-ዱዓ ስንፍናን ከላይ ላይ ያራግፋል፡፡ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ኢብኑ ሒባን በዘገቡት ሐዲስ (ከደካሞች ሁሉ ደካማ ማለት ከዱዓ የደከመ ነው፡፡ የንፉጎች ሁሉ ንፉግ ሰላምታ ከማለት የነፈገ ነው) ብለዋል፡፡

8-ዱዓ ዉጤቱም በአላህ ፍቃድ የተረጋገጠ ነው፡፡ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) አህመድና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ (ማንም ሰው ዱዓ አድርጎ አላህ የለመነዉን ይሰጠዋል፡፡ ወይም የሱን መሰል ክፉ ነገር ይከላከልለታል፡፡ ይህም የሚ ሆነው በወንጀል ወይም ዝምድናን በመቁረጥ ዱዓ እስካላ ደረገ ነው) ብለዋል፡፡

9- ዱዓ አላህ ይደሰትበታል፡፡ አላህ አገልጋዩ ሲለምነው ይደሰታል፡፡ እሱን በመለመን ችክ ባዮችንም ይወዳል፡፡ ወደራሱም ያቀርባቸዋል፡፡ የነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ባል ደረቦችም ይህን እውነታ ተረድተው የተኛዋንም አነስተኛ ጉዳይ አላህን ከመጠየቅ አይንቁም ነበር፡፡ የትኛውንም ጉዳይ ለአላህ እንጂ ለማንም ተራ ፍጡር አያቀርቡትም ነበር፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው (ባሮቼ ከኔ በጠየቁህ ጊዜ በላ ቸው- እኔ ቅርብ ነኝ፤ የለማኝን ፀሎት በለመነኝ ግዜ እቀበ ለዋለሁ) ባለው ቁርአናዊ አስተምህሮት መሰረት እነሱ በጌ ታቸው ላይ ካላቸው የሙጥኝ ባይነት፤ ወደ አላህ ካላቸው ቅርበትና እሱም ወደ እነሱ ካለው ቅርበት እንጂ ሌላ አይ ደለም፡፡

10-የአላህንም ቀደር ሊመልስ /ሊቋቋም/ ይችላል፡፡ የሙ ስሊም ዱዓ ቅድመ ሁኔታዎች ከተሟሉና እንቅፋቶች ከተ ወገዱለት ሁልጊዜም ተቀባይነት አለው፡፡ ዱዓ የሚያደ ርግ ሰው ሁሉ አህመድና ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ ነቢዩ (ማንም ሙስሊም ወንጀል ወይም ዝምድናን መቁረጥ ያልተቀላቀለበት ዱዓ ካደረገ ከሶስት ነገሮች አንዱን ይሰ ጠዋል፡፡ የለመነው በዚሁ በዱንያ ህይወት ሊፋጠንለት፤ ወይም ወደ አኺራ ተላልፎ ሊቀመጥለት ወይም ሊያገ ኘው የነበረውን ክፉ ነገር በዱዓው አቅም ልክ ሊከላከ ልለት ነው፣ ሲሉ ሰሃቦችም እንግዲያውማ- ዱዓ እናብዛ ማለት ነው- ሲሏቸው- የአላህ ይበዛል) በማለት መልሰው ላቸዋል፡፡

## መ-የዱዓ አይነቶች

የዱዓ አይነቶች ሁለት ናቸው፡፡

1-አምልኮታዊ ዱዓ ፡ ሶላት;ፆምና የመሳሰሉት፡፡

2-የልመናና የጥያቄ ዱዓ፡፡

ሰ-በቀንና በሌሊት ውስጥ የሚገኙ ምርጥ የዱዓ ሰዐቶች፡-

1-አላህ ወደቅርቢቱ ሰማይ በሚወርድበት በመጨረሻው አንድ ሶስተኛ የሌሊት ክፍል ሲቀር፣

2-በአዛንና በኢቃማ መካከል፣

3-አዛን ሲደረግ፤

4-ከውዱዕ በኃላ፣

5-ቡሱጁድ ላይ እያለ፣

6-ከሶላት ማሰላመት በፊት፣7-በዝናብ ሰዐት፤

8-ከየሶላቶች በኃላ፣

9-በሶፋ ላይ፤

10-ቁርኣን በሚኸተምበት ጊዜ፣

11-ዶሮ ሲጮህ፣

12-በመንገድ ላይ እያሉ ፤

13-የተበደለ ሰው ዱዓ፣

14-የተቸገረ ሰው ዱዓ፣

15-አባት ለልጁ የሚያደርገው ዱዓ፣

16-የፆመኛ ዱዓ፤

17-የዘምዘም ዉሃ ሲጠጣ የሚደረግ ዱዓ፤

18-ሙስሊም ወንድሙ በርቀት ለሌላው ሙስሊም ወንድሙ የሚያደርግለት ዱዓ፤

19-ከጠላት ጋር ሲገናኙ የሚደረግ ዱዓ ናቸው፡፡

20-በአጠቃላይ መስጂዶች በተለይም በመካ ካዕባ አጠገብ፣

21-ብሙልተዘም ዘንድ፣

22-ካዕባ አጠገብ ያለው መቃሙኢብራሂም/የኢብራሂም መቆሚያዘንድ፣

23-በሰፋና በመርዋ ላይ፣

24-በሐጅጊዜ በዐረፋ፣

25-በሐጅጊዜ በሙዝደሊፋ ና በሚና ላይ፣

26-የዘምዘም ውሃ በሚጠጡበት ጊዜ ናቸው፡፡

ረ-በሳምንት ውስጥ ያሉ -


1-የጁሙዓ ዕለት በተለይም በቀኑ የመጨረሻዋ ሰዐት ላይ፤


ከወሮች ውስጥ-

2-በረመዷን ወር በፊጥር ና በሱሁር ሰዐት፣

3-ለይለተል ቀደርና፣

4-የዐረፋ ቀን ናቸው፡፡





ድብቅ ምክንያቶች- እነኝህም፡-

1-እውነተኛ ተውበትን ማስቀደም፣

2-በበደል የወሰዱትን ነገር መመለስ፣

3-ምግብን፣ መጠጥን፣ ልብስንና መኖሪያን ማሳመርና ከሐላል ማድረግ፣

4-ዒባዳን ማብዛት፣

5-ወንጀሎችንመራቅ፣

6-ከሹብሃዎችም ሆነ ከስሜቶች ነፃ መሆን፣

7-በዱዓጊዜ- ዱዓን ከልብ ማድረግ፣በአላህ መተማመን፣

የተስፋ ስሜትን ማዳበር፣

ወደ አላህ መጠጋት፣

ራስን ማስተናነስና በአላህ መለመን ላይ ችክ ማለት፣ ሁሉን ነገር ወደ እሱ ማስጠጋትና ከሱ ሌላ ከሆኑ ሁሉ ተስፋ መቁረጥ ናቸው፡፡

ሸ-ዱዓን ተቀባይነት የሚያሳጡ ነገሮች፡-



የሰው ልጅ አንዳንድ ጊዜ ዱዓ አድርጎ ተሰሚነት ያጣ ይሆናል፡፡ ወይም ይዘገይበት ይሆናል፡፡ ታዲያ የዚህ ምክን ያቶቹ ብዙ ናቸው፡፡ ከነሱም ውስጥ:-

1-ከአላህ ጋርሌላን አካል መጥራት /ሽርክን መፈፀም፣

2-በልመናው ውስጥ ዝርዝር ነገሮችን መጥቀስ:- ለምሳሌ ከእሳት ጠብቀኝ የሚለው በቂ ሁኖ ሳለ ከጀሀነም ከጥበቷ፣ ከጨለማዋ ጠብቀኝ ማለትን ይመስል፣

3-አንድ ሰው በራሱ ላይ ወይም በሌላው ላይ በግፍ ዱዓ ማድረግ፣

4-በወንጀልና ዝምድናን በመቁረጥ ዱዓ ማድረግ፣

5-ልመናውን ከፈለክ አድርግልኝ ስትፈልግ ማረኝ- ብሎ መለመን፣

6ዱዓ አድርጌ ነበር ነገር ግን ተቀባይነት አላገኘሁም በማለት መልሱን ለማግኘት መቸኮል፣

ዱዓ ከማድረግ መሰላቸት፣

በተዘናጋ ልብ ዱዓ ማድረግ፣ ከአላህ ፊት ተገቢውን ስርአት አለመያዝ፣ ነቢዩ አቡ ዳውድ እና ቲርሚዚበዘገቡትሐዲስ (አንድን ሰው በሶላት ውስጥ በርሳቸው ላይ ሶለዋት ሳያ ወርድ ዱዓ ሲያደርግ ሰምተውት (ይህ ሰው ቸኮለ) አሉና እሱን ጠርተው ወይም ለሌላ ሰው (ማንኛውም ሲሰግድ በመጀመሪያ አላህን በማመስገንና በማወደስ ይጀምር፣ ከዚያም በነቢዩ ላይ ሶለዋት ያውርድ፣ ከዚያም የፈለገ ውን ይጠይቅ) ብለዋል፡፡ አቡዳውድናቲርሚዚዘግበው ታል፡፡ ሊሆን የማይችልን ነገር መለመን፣ ለምሳሌ በዚህች ዐለም ላይ ለዝንት ዐለም አኑረኝ ማለት፣ በግድ በግጥም መልክ ለማድረግ መልፋት ተገቢ አይደለም፡፡ ምክንያቱም አላህ እንዲህ ብሏል (ጌታችሁን ተናንሳችሁና ተዋርዳችሁ በድብቅ ለምኑት፣ እርሱ ወሰን አላፊዎችን አይወድምና)

ቡኻሪ በዘገቡት ሀዲስ እብኑ ዐባስ ስንኝ ያለበትን ዱዓ እያየህ ራቀው፡፡ ነቢዩና ባልደረቦቻቸውን ያገኘሁት እንዲህ ያለውን ዱዓ ሲርቁ ነው በለዋል፡፡ ድምፅን ከመጠን በላይ ማጉላት አይገባም፡፡ አላህ እንዲህ አለ (በስግደትህ (ስታነብ) አትጩህ፡፡ በርሷም ድምጽህን ዝቅ አታድርግ በሁለቱ መካከል መንገድ ያዝ) እናታችን ዐኢሻ እንደሚ



# ኢስላማዊ ወንድማማችነት

ኢስላማዊ ወንድማማችነት ማለት መዋደድ፣ መተዛዘን፣ መረዳዳት መተባበር ማለት ነው፡፡ ሙስሊሞችን ከሚያስተሳስሩ ነገሮች መካከል  ጠንካራውና የማስቀጠል አቅም ያለው መተሳሰሪያ ኢስላማዊ ግንኙነት ብቻ ነው፡፡ ምክንያቱም የተለያዩ አገሮችን፣ ዘሮችን፣ የተራራቁ ቦታዎችንና የተለያዩ ባለ ቋንቋ ተናጋሪ ሰዎችንም የሚያስተሳስር ፍቱን ገመድ በመሆኑ ብቻ ሳይሆን ከእምነቱም አንኳሩ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳይ ቁርኣን እንዲህ አለ ‹‹ምዕመናኖች ወንድማማቾች ናቸው፡፡ በሁለት ወንድሞቻችሁም መካከል አስታርቁ፡፡ ይታዘንላችሁም ዘንድ አላህን ፍሩ›› አል-ሁጁራት10.

ነብዩ እንዲህ  አሉ ‹‹ለአላህ ብሎ የወደደ፣ ለአላህ ብሎ የጠላ፣ ለአላህ ብሎ የሰጠ፣ ለአላህ ብሎ የከለከለ እምነቱን አሟልቷል›› አቡ ዳውድ፡፡  እንዲህም አሉ ‹‹ሰዎች!  ስሙ፡፡ ጌታችሁ አንድ ነው፡፡ አባታችሁም አንድ ነው፡፡ ስሙ፡፡ ዐረብ ከሌላው ሰው በምንም አይበልጥም፡፡ ሌላዉም ከዐረብ አይበልጥም፡፡ ቀይ ከጥቁር፣ ጥቁርም ከቀይ አይበልጥም፡፡ አላህን በመፍራት እንጂ፡፡ አደረስኩኝ›› አህመድ.

<u>ኢስላማዊ ወንድማማችነት ብዙ መብቶች እንዳሉት ሁሉ አያሌ ግዴታዎችም አሉት፣ ከብዙ ግዴታዎቹ መካከል በጥቂቱ</u>

1፡-ሙስሊም ለሙስሊም ወንድሙ ረዳትና ድጋፍ ሰጪ መሆን ነው ያለበት፡፡ ይህን አስመልክቶ ቁርኣን እንዲህ አለ፣ (...ከተከበረው መስጊድ ስለ ከለከሏችሁ ሰዎችን መጥላታችሁ በእነሱ ላይ ወሰንን እንድታልፉና ፍትህን እንድታዛቡ አይገፋፉዋችሁ፡፡በበጎ ተግባር አላህን በመፍራት እርስ በእርስ ተባበሩ፡፡ ኃጢአትና ወሰንን በማለፍ ግን አትተባበሩ ›› አል-ማኢዳህ 2.

ቁርኣን እንዲህም አለ (የወንድ አማኞችና የሴት አማኞች ከፊሎቻቸው ለከፊሉ ረዳቶች ናቸው፡፡ በደግ ነገር ያዝዛሉ፡፡ ከክፉም ነገር ይከለክላሉ፡፡ ሶላትን ይሰግዳሉ፡፡ ዘካን ይሰጣሉ፡፡ አላህንና መልዕክተኛውን ይታዘዛሉ ›› አል-ተውባህ 71. ቁርኣን እንዲህም አለ (እነዚያ በአላህ ያመኑና ለእሱ ሲሉ ከሀገራቸው የተሰደዱ በአላህ መንገድ ላይ በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸው የታገሉ እና እነዚያም ስደተኞቹን ያስጠጉና የረዱ ሰዎች እነዚያ ከፊሎቻቸው ለከፊሉ ረዳቶች ናቸው›› አል-አንፋል 72.

ነቢዩም እንዲህ አሉ፡-‹‹ወንድምህን ሌላን ሲበድልም ሆነ እራሱ ሲበደል እርዳው አሉ፡፡ አንድ ሰው ያአላህ መልዕክተኛ ሲበደል እረዳዋለሁ ሲበድልስ እንዴት ነው የምረ

ዳው አላቸው በደል እንዳይፈፅም መከልከል ነዋ ! አሉት» ቡኻሪ፡፡

2፡-ሙስሊም ውንድሙን አለመበደል ሲሆን ይህ ዘርፍ የትኛውንም የበደል አይነት ያጠቃልላል፡፡ (ሰዎች ! ስሙ አላህ በናንተ ላይ ደማችሁንና ንብረታችሁን ልክ በዚህ ወርና በዚህ ሀገር ይህ ቀን እንዳለው ክብር አይነት አክብ ሮላችኋል፡፡ስሙ መልዕክቴን አደረስኩን ሲሉ ፡፡ ሰዎችም አዎ አድርሰዋል አሏቸው፡፡ እሳቸዉም አላህ መስክር አሉ) ቡኻሪ.

እንዲህም አሉ (አትመቅኙ፤ ዋጋ አታሳቅሉ፤ በመካከላ ችሁ ጥል አይኑር፤ አትኳረፉ፤ ከፊሉ በከፊሉ ገበያ ጣልቃ አይግባ፤ እናንተ የአላህ ባሪያዎች ወንድማማች ሁኑ፡፡ ሙስሊም ለሙስሊም ወንድም ነውና አይበድለው፤ እር ዳታውንም አያቋርጥበት፤ አይዋሸው፤ አይናቀው፤ ወደልባ ቸው ሦስት ጊዜ በማመልከት አላህን መፍራት እዚህ ነው፡ ፡ አንድ ሙስሊም ወንድሙን መናቁ ብቻ ለወንጀልነት በቂ ነው፡፡ ሙስሊም የሌላውን ሙስሊም ደም፤ ገንዘብና ክብር (መንካት) ክልክል ነው) ሙስሊም.

3-እርስ በርስ መተዛዘንና መዋደድ ነው፤ ነብዩ ﷺ ይህንን ውዴታና መተዛዘን ልዩ በሆነ መንገድ ነው የገለጹት፤

4-እርስ በርስ መመካከር ሲሆን ይህም በዲን ጉዳይም ሆን በዱንያ ጉዳይ መመካከርን ያጠቃልላል፤ ለምሳሌ የማያቅን ማሳወቅ፤ የተሳሳተን ማቃናት፤ ያጠፉን መምከር፤ የተዳከ መን ማበረታታት እና ከዚህ ሁሉ ይበልጥ ወደ ተውሂድ ጥሪ ማድረግንና ከሽርክ መከልከልንን ያጠቃልላል፡፡

5-ሰላምታ መመለስን፤ጥሪ ማክበርን፤ ሲያስነጥስ ዱዓ ማድ ረግን፤ የታመመን ማየትን የሞተን መቅበር ነው፡፡

6-ለራሳችን የምንወደውን ለሙስሊም ወንድሞቻችን መውደድ ነው። ቁርአንና ብሐዲስ የሙስሊሞችን አንድነ ትና የመሃከላቸውን ግንኙንት የሚያጠናክሩ አያሌ ጥቅሶች አሉ፤ «እነዚያ ከበኋላቸው የመጡት ጌታችን ሆይ! ለእኛም ለእነዚያም በእምነት ለቀደሙን ወንድሞቻችን ምህረት አድርግ፡፡ በልቦቻችንም ውስጥ ለእነዚያ ለአመኑት ሰዎች ሁሉ ጥላቻን አታድርግ፡፡ ጌታችን ሆይ ! አንተ ሩህሩህ; አዛኝ ነህና ይላሉ» አል-ሐሽር 10፡፡

አንዳንድ አሊሞች ሙስሊሞችን መርዳት በብዙ መንገ ዶች ይቻላል በገንዘብ መርዳት፤ በስም መርዳት፤ በአካል መርዳት በምክር መርዳት፤ በዱዓ መርዳት እና መሰሎችም አሉ፡፡

## የአንድነትና የትብብር አስፈላጊነት

ወገኖቼ ሆይ ! ስለ አንድነት ሁሉም በየአጋጣሚው እን ደሚያስፈልግ ሲያስተጋባ“ ሲናገር ይደመጣል፡፡ ቁርዓንና ሱናም ለአንድነት ከፍተኛ ትኩረት ሰጥተው ሙስሊሙን ኡማ መክረዋል፡፡ ህዝበ ሙስሊሙም በአንድ ድምፅ ይቀበ ለዋል፡፡ እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው አንድነት አላህና ረሱል የሚሹት አንድነት በእውነት በላ ኢላሃ ኢለላህ እና በቁርአንና በሱና ላይ የተመሰረተውን እንደሆነ ሊታወቅ ግድ ይላል፡፡

ቁርአን እንዲህ አለ ፡ (የአላህንም (የማመን) ገመድ ሁላ ችሁም ያዙ አትለያዩም ጠበኞችም በነበራችሁ ጊዜ በናንተ ላይ (የዋለውን) የአላህን ጸጋ አስታውሱ በልቦቻችሁም መካከል አስማማ በጸጋውም ወንድማማቾች ሆናችሁ በእሳት ጉድጓድ አፋፍም ላይ ነበራችሁ ከእርሷም አዳና ችሁ እንደዚሁ ትመሩ ዘንድ አላህ ለናንተ አንቀፆቹን ያብራ ራል) ሱ.ኢምራን ቁ.103.

መበታተንና መለያየት እንዲሁም በጠላትነት መተያየት የመ ጨረሻ ውጤቱ እሳት መሆኑን በመግለፅ ሷሀቦችን ከዚህ አደጋ እንዳተረፋቸው በመግለፅ ለውለታው ምላሽ እንዲ ሰጡ ይጋብዛል፡፡ እንደነዚያም ግልጽ ታአምራት ከመጣላ ቸው በኋላ እንደ ተለያዩትና እንደ ተጨቃጨቁት አትሁኑ እነዚያም ለነርሱ ታላቅ ቅጣት አላቸው፡፡ ኣሊ ኢምራን ቁ.105

ቁርአን እንዲህ አለ ለሰዎች ከተገለጸች ሕዝብ ሁሉ በላጭ ሆናችሁ በጽድቅ ነገር ታዛላችሁ ከመጥፎ ነገር ትከለክላላ

ችሁ በአላህም አንድነት ታምናላችሁ$ ኣሊ ኢምራን 110

ቁርኣን እንዲህም አለ (ችግር ሲፈጠር) አስታርቁ ይታዘንላ ችሁም ዘንድ:: አላህን ፍሩ» አል -ሑጅራት ቁ.10. «እናንተ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! ከጥርጣሬ ብዙውን ራቁ:: ከጥር ጣሬ ከፊሉ ኀጢአት ነውና:: ነውርንም አትከታተሉ :: ከፊላችሁም ከፊሉን አይማ:: አንደኛችሁ የወንድሙን ስጋ የሞተ ሆኖ ሊበላ ይወዳልን ? (መብላቱንም) ጠላችሁትም (ሐሜትንም እንደዛው ጥሉ):: አላህንም ፍሩ አላህ ጸጸትን ተቀባይና አዛኝ ነውና» ሱረቱል ሑጅራት 12.

ቁርኣን እንዲህም አለ"አላህ ከበላያችሁ ወይም ከእግሮቻ ችሁ በታች ቅጣትን በናንተ ላይ ሊልክ ወይም የተለያዩ ህዝቦች ስትሆኑ ሊያደባልቃችሁ እና ከፊላችሁን የከፊሉን ጭካኔ ሊያቀምስ ቻይ ነው በላቸው:: ያውቁ ዘንድ አንቀ ፆችን እንዴት እንደምናብራራ ተመልከት" ሱ. አንዐም 65

በዚህ አንቀጽ ውስጥ የምናገኘው ትምህርት አላህ ህዝቦች ከርሱ ጎዳና ሲወጡና አመፅኝነት ጎልቶ ሲታይባቸው እን ዲሁም በቁርኣን መመከርንና መገሰፅን ሲተው ከሚወስ ድባቸው የቅጣት እርምጃዎች አንዱ ህዝቡን በመከፋፈል ከፊሉን በከፊሉ ላይ የበላይ በማድረግ እንዲያጠቃና እን ዲያሰቃይ በመፍቀድ የሚቀጣቸው መሆኑን በማያሻማ መልኩ አስቀምጧል::

እንግዲህ ልብ በሉ አላህ ህዝቦች" ከሚቀጣባቸው መን ገዶች አንዱ በመሀከላቸው ልዩነትን በመፍጠር አንዱ አንዱን እንዲያጠቃ በማድረግ መሆኑን ከተረዳን ዛሬ እኛ ያለንበት ተጨባጭ ከምን የሚታይ ይሆን? መለያየታችን የአላህ ቅጣት ቢሆንስ? ለምን መለስ ብለን አናስብም ቁር ኣንና ሀዲሱን ለምን በጥልቀት አንመረምርም ? ቁርኣ ንና ሱና በዚህ መልኩ ትኩረት ለሰጡት ነገር እኛስ ለምን አንሰጥም? ይህን ለማድረግ (ለማስተካከል) ካልሞከርን አደጋው እጅግ በጣም አስከፊ እንደሚሆን አትጠራጠሩ::

ቁርኣን በሌላ ቦታ መለያየትን፣ መቃረንንና መበታተንን አስመልክቶ እምነታቸውን ከፋፍለው የተለያዩና አካሄዳቸ ውን ለየቅል ያደረጉ የእምነት ባለቤቶችን ሲኮንን እንዲህ ብሏል:: (እነዚያ ሀይማኖታቸውን የለያዩ አህዛቦችም የሆኑ ሰዎች በምንም ከነሱ አይደለህም:: ነገራቸው ወደ አላህ ብቻ ነው:: ከዚያም ይሰሩት የነበሩትን ሁሉ ይነግራቸዋል) አንዓም ቁ.159

አብደላህ ቢን አባስ (ረ.ዐ) ይህን አንቀጽ አስመልክቶ ሲናገር አንቀጹ የወረÅው ዲናቸውን (እምነታቸውን) በመ ከፋፈል ልዩነትንና ተቃርኖን በፈጠሩ አይሁድና ክርስቲያ ኖች ላይ ነው በማለት ይገልፃል:: መልእክቱ እኛንም እንደ ሚመለከተን መገንዘቡ ጠቃሚ ነው::

በመለያየትና በመቃረን «ዲን» እምነትን መገንባት አይቻ ልም:: ዲን መገንባት ከተፈለገ «ተፈሩቅ» መቃረንና መከ ፋፈል መቅረት ይኖርበታል:: ሁሉንም ሰላማዊና ከአቅም በላይ በሆነ ሁኔታ የ}ከሰተን ልዩነት በመተሳሰብና በመወ ያየት ለመፍታት መሞከር ግድ ይሆናል ማለትን እስካሁን ካየነው ቁርአናዊ መልእክት መረዳት ይቻላል::

ነብያዊ ሐዲሶች ቁርኣን ያስቀመጣቸውንና ትኩረት የቸራ ቸውን ጉዳዮች ማለትም አንድነትንና ወንድማማችነትን በማብራራf መለያየትንና መቃረንን የሚከለክሉ ህግና ስር ዓቶች በማጠናከር እንዲሁም በማረጋገጥ በኩል ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቷል::

ነብያዊ ሀዲሶች ሙስሊሙን ህብረተሰብ ወደ አንድነ ትና መቀራረብ በመጥራት ከመለያየትና ከመከፋፈል በጥብቅ ከልክሏል:: ወደ ወንድማማችነትና ወደ መዋደድ ጋብዟል በዚህም ዙሪያ በርካታ ሀዲሶች ቀርበዋል:: ጥቂቱን አብረን እንይ::

በአንድ ወቅት መዲና ውስጥ በሚኖሩ የአውስና የኸ ዝረጅ ጎሳ አባላት በሆኑ ሁለት ጎሳዎች:መካከል አላስፈ ላጊ ፀብና ጭቅጭቅ ተፈጠረ ይሄኔ የአውስ ጎሳ አባላት ለአውስ የኸዝረጅ ጎሳ አባላት ለኸዝረጅ አባላቸው በመወ ገን ግሩፕ ፈጥረው በመሰዳደብ ወደ ፀብ ገቡ:: ከዚህም አልፈው ጦር ወደ መማዘዝ ደረሱ:: ይህን ጊዜ ወሬው

ለረሱል ደረሰ፡፡ ረሱልም ወደነርሱ በመሄድ እንዲህ አሉ፡ - «እናንተ ሙስሊሞች ሆይ አላህን ፍሩ አላህን ፍሩ! እኔ በመሀከላችሁ እያለሁ በጃሂሊያው (የአስተሳሰብ ቀንበር ስር ሆናችሁ) ትጠራራላችሁ? አላህ ወደ ኢስላም ከመራ ችሁ በኋላ፣በኢስላም ካከበራችሁና ከናንተ ላይ የጃሂሊያ ውን ግብስባስ ቆርጦ ከጣለው በኋላ፣እንዲሁም በኢስላም ምክንያት «ከኩፍር» ከክህደት በማዳን በመካከላችሁ በሱ ሳቢያ ትስስርንና መላመድን ከፈጠረ በኋላ (አሁን) ወደ ነበራችሁበት የክህደት ህይወት ትመለሳላችሁ» በማለት ሰሃቦችን ወቀሱ «ይሄኔ ሰሃቦችም ጉዳዩ የሸይጣን ጉትጎ ታና የጠላታቸው ሴራ መሆኑን አወቁ፣መሳሪያዎቻቸው ንም ጣሉ፣ በሰሩት ስራ ተፀፅተው አለቀሱ ከፊሉ ከፊሉን አቀፈ፡፡ ከዚያም ነብዩን የሚታዘዙና የሚሰሙ ሆነው ተነ ስተው ሄዱ፡፡

በሌላ ሐዲስ ነብዩ እንዲህ ብለው ነበር፡፡ «በመሰባሰ ብና አንድ በመሆን ላይ አደራችሁን ከመለያየትና ከመከፋ ፈል ተጠንቀቁ» ከዚህ ሐዲሳቸው በኢስላም ጥላ ስር ያሉ ወገኖች ከመከፋፈል ይልቅ በመሰባሰብና አንድ በመሆን ለጋራ ዓላማ በጋራ መስራት እንዳለባቸው በግልጽ የመከ ሩበትን ሁኔታ ለማየት ሞክረናል፡፡ ይህን መሰል በርካታ ሐዲሶች ከነብዩ (ﷺ) ተነግረዋል፤ በሌላ አባባላቸው፡ -«ከእናንተ አንዳችሁ አላመነም ወይም ኢማኑ ሙሉዕ አይ ሆንም ለራሱ የወደደውን ነገር ለወንድሙ እስካልወደደ ድረስ» በማለት የሙእሚኖች ትስስር ምን ያህል ጠንካራ እንደሆነና ለራሱ እንዲሆንለት የሚፈልገውን (የሚሻውን) ነገር ወንድሙ እንዲያገኝ እስካልተመኘ ድረስ ኢማኑ ላይ ሁሌም ጉድለት ሊኖርበት እንደሚችል አሳይተዋል፡፡

«ሙስሊም ለሙስሊምወንድሙ ነው» ባሉት መሠረት ወንድማዊነቱን በተግባር ለማሳየት እስካልሞከረ ድረስ እንከን እንደማያጣውና ኢማኑ ሊሞላ እና የተስተካከለ ሊሆን እንደማይችል በግልጽ አስቀምጠዋል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎን ይህን ወንድማማችነት ሊያጠናክር የሚችል ጥቆማም ሰጥተዋል፡፡

«በዚያ ነፍሴ በእጁ በሆነው ጌታ እምላለሁ፡፡ ጀነትን አት ገቡም እስካላመናችሁ፡፡ አማኝ ልትሆኑም አትችሉም እስ ካልተዋደዳችሁ ድረስ ፡፡ ከሰራችሁት የሚያዋድዳችሁን ተግባር ልንግራችሁን ? (አሉ ቀጠል አድርገውም) በመካከ ላችሁ ሰላምታን አብዙ» ሙስሊም፡፡

እኛም ይህን ሀዲስ በአግባቡ በመገንዘብ ሊያዋድዱንና አን ድነታችንን ሊያጠናክሩ ከሚችሉ ተግባሮች መካከል አንዱ የሆነውን ሰላምታን በመጠቀም ለአንድነታችን የበኩላችንን አስተዋፅኦ እናድርግ እንላለን፡፡

አንድነትን ሊያናጉና ሊያደፈርሱ ከሚችሉ መጥፎ ድርጊ ቶች እንድንቆጠብ ሲመክሩን እንዲህ ይላሉ፡-አነስ ኢብኑ ማሊክ ባስተላለፈው ሀዲስ ላይ ነብዩ እንዲህ ብለዋል «አትጠላሉ (አንዳችሁ አንዳችሁን አይጥላ) አንዱ በአንዱ ላይ አይመቀኝ (አትመቀኛኙ)፣ ጀርባ አትሰጣጡ፣ የአላህ ባሪያ ወንድማማቾች ሆኑ፣ ሙስሊም ሙስሊም ወን ድሙን ከሶስት ቀን በላይ ሊያኮርፍ አይፈቀድለትም» ቡኻሪና ሙስሊም፡፡

አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት ነብዩ (ﷺ) « ጥርጣሬን አደራ ተጠንቀቁ ጥርጣሬ የውሸት ወሬ ነው፡፡ አትፈላፈሉ፡ ፡ አንዱ አንዱን ምን እንደሚሰራ አይከታተል እንዲሁም አንዱ አንዱን አይሰልል… የወንድማችሁን ገንዘብ አታስቦ ጭቁ (ያለ አግባብ ገንዘቡ" አያስበላው) » በማለት ለአን ድነት ጠንቅ ከሆኑ የአንድነት ቫይረሶች በጥብቅ ይከለክ ሉናል፡፡

ቁርኣንና ሱናን መከተል ሲባል አንዱን ተቀብሎ ሌላውን መተው እንዳልሆነ መቼም ይገባናል፡፡ ስለዚህ እኛ ሙስሊ ሞች፣የነብዩ ተከታይ ነን እስካልን ድረስ ይህን እና መሰል መመሪያዎችን ልንተገብር የግድ ይለናል፡፡

የአላህ መልእክተኛ (ﷺ) «ሙእሚኖች ካላቸው መዋደድ፣ መተዛዘንና ከመተሳሰር አኳያ እንደ አንድ አካል ይመስ ላሉ፡፡ አንዱ አካል በበሽታ ሲጠቃ ሌላው አካል በህመምና እንቅልፍ በማጣት የችግሩ ተካፋይ ለመሆን ይጠራራሉ»




በማለት አስተምረዋል፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም.

የአላህ መልእከተኛ  ኢማሙ ቲርሚዚይ በዘገቡት ሐዲስ፡ -(ሙእሚን ለሙእሚን መስታወት ነው፡፡ ሙእሚን ለሙእሚን ወንድሙ ነው፡፡  ከጠፊዎች ሳይሆን ከእድለኞች ይሆን ዘንድ  ምላሱን ይቆጥባል፣የሰዎችን መብት አውቆ ያከብራል )ብለዋል ፡፡

የሰውን ክብር መንካትን  አስመልክቶ ቁርአን እንዲህ በማለት ይገልጸዋል፡

ሁለት የምዕምናን ጭፍሮች እርስ በእርስ ቢጋደሉ በመካከላቸው አስታርቁ፡፡ ከሁለት አንደኛይቱ የሌላኛይቱ ላይ ወሰን ብታልፍ ያችን ወሰን የምታልፈውን ወደ አላህ ትዕዛዝ እስከምትመጣ ድረስ ተጋደሉ ብትመለስ ግን በመካከላቸው በትክክል አስታርቁ፡፡ በነገሩ ሁሉ አስተካክሉ፡፡ አላህ አስተካካዩችን ይወዳልና፡፡ ምዕመናኖች ወንድማማቾች ናቸው፡፡ በሁለት ወንድሞቻችሁም መካከል አስታርቁ፡፡ ይታዘንላችሁም ዘንድ አላህን ፍሩ፡፡አል ሑጁራት. 10-11. ምክኒያቱም የዚህ  አንቀፅ የወረደበት ምክንያትን ስንመለከት ከላይ ያለዉን ያረጋግጣል፡፡

አንዳንድ ሶሃቦች ወደ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) እየመጡ ዐብደላህ ኢብኑ ኡበይን ቢያናግሩት ጥሩ ነበር እያሉ ሲነግሯቸው ሊያናግሩት እሳቸው በአህያ ላይ ሁነው ሌሎች ሙስሊሞች ደግሞ በግራቸው ሁነው ሄዱ፡፡ እዚያ እንደደረሱ ግን ዐብደላህ እባክህን ውጣልኝ የአህያህ ግማት አስቸገረኝ አላቸው በዚህ ጊዜ አንድ ሱህባ ተነስቶ ወላሂ ከአንተ ሽታ የነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) አህያ ሽታ ይሻላል፡፡ አለው፡፡ በዚህ ጊዜ አንድ የእሱ ወገን የሆነ ተነስቶ መልስ ሲሰጥ በሁለቱም ወገኞች እልህ ተጋቡና ችግሮች ተፈጠሩ በጫማ በእጅ መመታታት ተጀመረ፡፡ ይህን ምክንያት አድርጎ ነበር ይህ አንቀፅ የወረደው፡፡





# የአማና ክብደት በኢስላም

አማና ከቃሉ ጀምሮ ከኢማን ጋር ከፍተኛ ትስስርነት ያለው ቃል ነው፡፡ እንደዚሁም ከአምን/ፀፅታ/ ፤ ከታማኝነት ጋርም የተያያዘ ቃል ነው፡፡ በመሆኑም አማና ማለት በኢስላም እንድን ሰራው የታዘዝነዉና እንዳንሰራው የተከለከልነው ሁሉ ማለት ነው፡፡እናም አማና ዘርፉ-ብዙ ቢሆንም በዋነኘነት ገንዘብ ነክ ነገሮችን፤ ዉሎችን፤ አደራዎችን ፤ ምስጢሮችን፤ ሃላፊነቶችን፤ ሶላትን፤ ዘካን፤ ፆምን፤ ሀጅን፤ አካልን፤ ንብረትን፤ እውቀትን፤ ምስክርነትን፤ ዳኝነትን፤ እና ሌሎችንም ያጠቃልላል፡፡ ታማኝነት ትልቅነት ነው፡፡ አማኞችም የሚፈተኑበት ዋናው እሱው ነው፡፡ ይህን አስመልክቶ አላህ እንዲህ አለ «እኛ አደራን በሰማያት በምድር እና በተራራዎች ላይ አቀረብናት፡፡ መሸከሚንም እንቢ አሉ፡፡ከእርሷም ፈሩ፡፡ሰው ግን ተሸከማት፡፡እርሱ በጣም በደለኛና ተሳሳች ነውና፡፡ ወንዶች መናፍቃንንና ሴቶች መናፍቃትን ወንዶች አጋሪዎችንና ሴቶች አጋሪዎችን አላህ ሊቀጣ በምዕምናንና በምዕመናት ላይ አላህ ንስሃን ሊቀበል አደራዋን ሰው ተሸከማት፡፡አላህ መሃሪና አዛኝ ነው»አህዛብ 72. አማና ግዴታ ነገሮችን ሁሉ መፈጸምን የተከለከሉ ነገሮችን መተዉን ያጠቃልላል፡፡ ምክንያቱም በቁርአን ግዴታዎችን አለመወጣት በሚያመለክት አላህ እንዲህ አለ «እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ ! አላህንና መልዕክተኛውን አትካዱ፡፡ አደራዎቻችሁንም እያወቃችሁ አትካዱ») አል-አንፋል 27. የአማና አስፈላጊነትም በጣም ከፍተኛ እንደሆነ ብዙ መዘርዝር ባያስፈልግም በጥቂቱ ለማስታወስ ያክል ከዚህ በታች ያለዉን ታሪክ እናንሳ፡፡ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) በኒ ቁረይዛዎችን ለማጥቃት ሃያ አንድ ቀን ከበባ አድርገው መውጫ መግቢያ ባሳጧቸው ጊዜ በኒቁረይዛዎች ከረሱልሙሐመድ (ﷺ) ጋር ድርድር ለማድረግና ስምምነት ላይ ለመድረስ ጥያቄ አቀረቡ፡፡ ነብዩ ሙሐመድም (ﷺ) ሰዐድ ቢን ሙዐዝ በሚሰጡት ውሳኔ እንዲስማሙ ሀሳብ ሰነዘሩ፡፡ በኒ ቁረይዟዎች ግን የሰዐድ ቢን ሙዐዝን ውሳኔ ከመስማታችን በፊት አቡ ሉባባህ የተባሉ የቀድሞ ወዳጃቸውን እንዲልኩላቸው ጠየቁ፡፡ ረሱልም አቡ ሉባባህን ላኩላቸው፡፡ በኒቁረይዟዎችም ለአቡ ሉባባህ «በሰዕድ ቢን ሙአዝ ሀሳብ ብንስማማ ምን ይመስልሀል» ሲሉ ጠየቋቸው፡፡በዚህ ጊዜ በምልክት ወደ ጉሮሮአቸው በማመላከት በሰዕድ ቢን ሙአዝ ውሳኔ ከተስማሙ የሚጠብቃቸው ሞት መሆኑን በመግለፅ ካስጠነቀቋቸው በኋላ ተፀፀቱ፡፡ ወዲያውም በመስጊድ ውስጥ ባሉ ቋሚ ምሰሶዎች ራሳቸውን አስረው አልበላም አልጠጣም በማለት ሰባት ቀናት አሳለፉ፡፡ በጣም ለተዳከሙና ስለ ተጐሳቆሉ ነብዩ ሙሐመድ በዚህ ጊዜ በምልክት ወደጉሮሮአቸው በማመላከት በሰዕድ ቢን ሙአዝ ውሳኔ

ከተስማሙ የሚጠብቃቸው ሞት መሆኑን በመግለፅ ካስ ጠነቀቋቸው በኋላ ተፀፀቱ፡፡ « ከአላህ ተውበት እንደመ ጣለት ንገሩት » በማለት ላኩባቸው አቡሉባባ ግን ወላሂ ራሴን አልፈታም ነብዩ (ﷺ) እስካልፈቱኝ ድረስ በማለት በአቋማቸው ፀኑ፡፡ ነብዩ ይህ ሲነገራቸው መጥተው በእጃ ቸው ፈቷቸው፡፡ አቡ ሉባባ ወደ አላህ ከመቶበቴ ምልክ ቶች አንዱ ይህን ወንጀል የፈፀምኩባትን አገር ለቆ መሄድና ንብረቴንም በሙሉ ለአላህ መስጠት ነው ሲሉ ነብዩ (ﷺ) አንድ ሦስተኛውን መስጠት ይበቃሃል አሏቸው፡፡ ይህን ታሪክ ምክንያት በማድረግ ነበር ይህ አንቀጽ የወረደው በማለት ጦበሪ፤ ዋሂዲ እና ሱዩጢ ይስማማሉ፡፡

2. አደራን በአግባቡ ጠብቆ መመለስን አስመልክቶም አላህ እንዲህ አለ« አላህ አደራዎችን ወደ የባለቤቶቻቸው እንድ ታደርሱና በሰዎች መካከል በፈረዳችሁ ጊዜም በትክክል እንድትፈርዱ ያዛችኋል፡፡አላህ በእርሱ የሚገስፃችሁ ነገር ምን ያምር ነው፡፡ አላህ ሰሚ እና ተመልካች ነውና፡፡አን-ኒሳእ58

ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) መካን በተቆጣጠሩበት ዕለት የካዕ ባን ቁልፍ ይዞ የነበረው ዑስማን ቢን ጠልሀ ቁልፉን እን ደያዘ ካዕባ ጣሪያ ላይ ወጣና ለነብዩ (ﷺ) ቁልፉን አልሰ ጥም በማለት ከለከለ፡፡ ከዚያም አሊይቢን አቡጣሊብ ወደ ጣሪያው በመውጣት አስገድደው ተቀበሉት፡፡ ይህን ጊዜ ነብዩ ወደ ካዕባ ገብተው ሰግደው ሲወጡ እነዚህ የቁር ኣን አንቀፆች ወረዱ፡፡ ነብዩ (ﷺ) ለአሊይ ቢንአቡጣሊብ «ሄደህ ይቅርታ ጠይቀውና ቁልፉን መልስለት» አሉት፡፡ አሊይም ሄደው ቁልፉን ሲመልሱለት አስገድደህ «ወስደህ ስታበቃ እንደገና ትሰጠናለህ» በማለት በቁጣ ተናገረ፡፡ አሊይም በበኩላቸው «አላህ በአንተ ምክንያት የቁርኣን አንቀፅ አውርዷል» አላቸውና አንቀፁን አነበቡለት፡፡ ኡስ ማንም እዚያው ኢስላምን ተቀበሉ፡፡ በደስታም ተዋጡ፡ ፡ ነብዩ (ﷺ) «እስከመጨረሻ ድረስ ውሰዳት፡፡ ይህችን ቁልፍ ከአንተ የሚወስዳት ግፈኛ ነው አሉ» እነሆ እስከ ዛሬም ድረስ በዚሁ ሰውዬ ዘሮች እጅ ነው ቁልፉ የሚገ ኘው፡፡ (ዋሂዲ እና ሱዩጢ) ኢብኑ ተይሚያ ይህ አንቀፅ በዋነኝነት ባለስልጣናትን ነው የሚመለከተው ይላሉ፡ ፡ ሸውካኒም ይህ አንቀፅ ብዙ ህግጋትን ያካተተ አንቀፅ ነው ይላሉ፡፡ እናም በዋነኝነት ባለስልጣናት ንየሚመለከት ቢሆንም ሁሉንም ህዝብ ያጠቃልላል፡፡

3. ኢስላም ሌላው ቀርቶ ጥብቅነትንም አማና ብሎ ነው የሰየመው መሆኑን አላህ እንዲህ አለ ((ከሁለቱ አንደኛይ ቱም ከሀፍረት ጋር የምትሄድ ሆና ወደ እርሱ መጣች፤ አባቴ ለእኛ ያጠጣህልንን ዋጋ ሊሰጥህ ይጠራሃል አለችው፤ ወደ እርሱ በመጣና ወሬውን በእርሱ ላይ በተረከለትም ጊዜ አትፍራ፡፡ ከበደለኞች ህዝቦች ድነሃል አለው፡፡ ከሁለቱ አን ደኛይቱም አባቴ ሆይ! ቅጠረው ከቀጠርከው ሰው ሁሉ በላጩ፤ ብርቱው፤ ታማኙ ነውና አለችው)) አል-ቀሰስ፡ 26.

4-አማና ከፍተኛ ደረጃ ያለውና በአግባቡ ሊወጡት የሚገባ ሃላፊነት ነው፡፡ ቁርኣን እንዲህ አለ፡- በጉዞ ላይ ብትሆኑና ፀሐፊ ባታገኙ በእጅ የተጨበጡ መተማመኛዎ ችን ያዙ፡፡ ከፊላችሁ ከፊሉን ቢያምን ያ የታመነው ሰው አደራውን በትክክል ያድርስ፡፡ አላህን ጌታውን ይፍራ፡፡ ምስክርነትንም አትደብቁ፡፡ ምስክርነትን የሚደብቃት ሰው ልበ ኃጢአተኛ ነው፡፡ አላህ የምትሰሩትን ሁሉ አዋቂ ነውና፡፡ አል-በቀራህ 283.

5-አማናን በአግባቡ መወጣት ከትክክለኛ አማኞች መለያ ባህሪያት አንዱ ነው፡፡ ቁርኣን እንዲህ አለ፡- (....እነዚያም ለአደራዎቻቸውና ለቃልኪዳናቸው ጠባቂዎች፣ እነዚያ በስ ግደቶቻቸው ላይ አላህን የሚጠባበቁ፣ ወራሾቹ እነርሱ (ብቻ) ናቸው፤ እነዚያ ፊርደውስን፤ የሚወርሱ እነሱ ናቸው፡፡ እነሱ በእርሷ ውስጥ ዘውታሪዎች እነሱ ብቻ ናቸው) አል-ሙዕሚኑን8-11.

6-አማናን ቁርኣን ብቻ ሳይሆን የነቢዩ (ﷺ) ሐዲሶችም በከፍተኛ ትኩረት የሰጡት ጉዳይ ነው፡፡ ምክኒያቱም ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ከመላካቸው በፊት አል አሚን ይሏቸው ነበር፡፡ ይህን ስም ያገኙት አንድ ስራ ድንቅ ስራ ብቻ ስለሰሩ አልነበረም፤ ምክንያቱም ነብዩ (ﷺ) በን



ግግራቸው፤ በቃላቸው፤ አደራ በማስቀመጣቸው፤ሚስጥር በመጠበቃቸው፤ እና በሌሎችም ነገሮች ሁሉ ታማኝ ስለ ነበሩ ነው፡፡ ነቢዩ ስለ አማና አያሌ ሐዲሶችን ተናግረዋል፡ ፡ ከዚህ በታች የተጠቀሱት ሐዲሶች ለአብነት ይሆናሉ፡፡

1-አቡ ሱፍያን በሮም መንግስት ፊት ቀርቦ ስለ ነቢዩ ማንነት ተጠይቆ ሲመልስ...... በምን በምን ያዛል ለተባለው ሲመልስ በሶላት፤ በእውነተኝነት፤ በጥብቅነት፤ ቃልን በማ ክበር፤ አማናን በመጠበቅ ....) በማለት ነበር የገለፃቸው፡፡

2-ነብዩ (ﷺ) አህመድ በዘገቡት ሐዲስ (አራት ነገሮ ችን ካሟላህ ሌላ ነገር አመለጠኝ ብለህአትሰብ፡፡ አማናን መጠበቅ ፤ እውነት ማውራትን፤ መልካም ባህሪን መላበስ፤ ሐላልን መብላት)ብለዋል፡፡

3-አንድ ዘላን መጥቶ ቂያማ መች ነው ? በማለት ቢጠ ይቃቸዉ ዝም ብለው ማስተማራቸዉን ቀጠሉ አንዳን ዶች ባይሰሙት ነው እስከሚሉ ደርስ ሌሎች ደግሞ ሰም ተዉት ስላላስደሰታቸው ነው አሉ፡፡ እሳቸው ግን ትምህ ርታቸዉን ሲጨርሱ ስለቂያማ የጠየቀው ሰው የት አለ በማለት ሲጠይቁ አለሁ አላቸው አማና ሲጠፋ ቂያማን ጠብቅ አሉት፡፡ እሱም እንዴት ነው አማና የሚጠፋው በማለት ሲጠይቃቸው ነገሮች ሁሉ ለማይመለከታቸው አካላት ሲሰጡ ነው አሉት፡፡) ቡኻሪ

አማናን በአግባቡ የመጠበቅ ትሩፋት

1-የአላህን ዉዴታ ለማግኜትና ወደ አላህ ለመቅረብ ዋናው መስመር ነው፤

2-የእምነት ጥንካሬ ምልክት ነው፤

3-የማህበረሰብ አለኝታ ነው፤

4-የማህበረሰብ ትስስርነትን ማጉያ ነው፤

5-የሰዎች መብትና ሐቅ በአግባቡ ለመወጣት ትልቅ አርአያ ነው፤

6-ከንፍቅና ነፃነትማወጃዎችአንዱነው፤

በአጠቃላይ አማናን ማክበር፡-

1-የአላህን ትዕዛት ማክበር፤

2-ንብረት ነክነገሮችን ለየባለቤቶች ማድረስ፤

3- የሰዎችን ክብርና ስም ዝና የመጠበቅ ሃላፊነትን መወጣት፤

4-ሰዉነታችንን የመጠበቅ ሃላፊነት ፤

5-እውቀቶቻችንን በአግባቡ የመጠበቅና ማስተላለፍ ሓላ ፊነት፤

6-ስልጣኖቻችንን በአግባብበመጠቀም ፤

7-ምስክሮቻችንን በትክክልማድረስሃላፊነት፤

8-ዳኝነታችንን እና ሺምግልናችንን በአግባቡ መወጣት፤

9-የፁሑፍ ሃላፊነታችንን በአግባቡ መወጣት እና መሰሎች ንም ሀላፊቶች በአግባቡ መወጣት ነው፡፡

አላህ አማናችንን በትክክል የምንወጣ ያድርገን፡፡

# የሴቶች ክብር በኢስላም



ኢስላም ለሴት ልጅ  የአጎናፀፋትን ክብር በየትኛውም ሐይማኖት ወይም ምድራዊ ህግጋት ወደር አይገኝለትም:: በአላህ ፊት የሴቶች መብትና ግዴታዎች በምድራዊም ይሁን በመጭው ዓለም ምንዳቸው ከወንዶች ጋር እኩል ነው:: እምነትንና መልካም ስራን መሰረት አድርጎ አሏህ ዘንድ በሚገኝ ምንዳና ትሩፋት ሴት ልጅ ከወንድ ጋር እኩል ናት:: ይህንን እውነታ ነብዩ (ﷺ) አቡ ዳዉድ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ በማለት አስተምረዉታል:: «....ሴቶች የወንዶች ከፋዮች ናቸው» ብለዋል:: በመሆኑም ሁለቱም ለሠሩት እኩይ ሥራ በእኩል ይጠየቃሉ:: ለሠሩት በጎ ተግባርም በሚቀጥለው ዐለም በእኩል ይመነዳሉ::  ኢስላም ሴትን ልጅ ገና ከልደቷ ጀምሮ መብቷን የጠበቀና ተገቢውን ክብር የሰጣት መለኮታዊ ሀይማኖት ነው:: ቀደም ሲል ሴት ልጅ ግማሽ ሰብአዊና ፍጡር ወይም ከዚያ በታች ደረጃ ያላትና ለወንድ አገልግሎት ብቻ የተፈጠረች ሆና ትገመት በነበረበት በዚያ የአረቢያ ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ  አዲስ ክብርና ዓለም አቀፋዊ የሆነ መልዕክት የሰውን ዘር ለማስተማር እንዲህ ሲል አስተጋባ:- (እርሱ ያ ከአንዲት ነፍስ (ከአደም) የፈጠራችሁ ከእርሷም መቀናጀዋን ወደርሷ ይረካ ዘንድ ያደረገ ነው:: (ዕራፈ: 189) እንዲህም አለ (ሰማያትና ምድርን ፈጣሪ ነው:: ከነፍሶቻችሁ ሴቶችን ከቤት እንስሳትም ወንድና ሴትን ለእናንተ አደረገላችሁ) (አሽ-ሹራ:11) እንዲህም አለ (አላህም ከነፍሶቻችሁ ለእናንተ ሚስቶችን አደረገ፤ ለእናንተም ከሚስቶቻችሁ ወንዶች ልጆች የልጅ ልጆችንም አደረገላችሁ፡ ከመልካሞችም ፀጋዎች ሰጣችሁ) (አን -ነህል:72)  እንዲህም አለ (ጌታቸውም እኔ ከናንተ ከወንድ ወይም ከሴት የሠሪን ስራ አላጠፋም ከፊላችሁ ከከፊሉ ነው በማለት ለነርሱ ልመናቸውን ተቀበለ) (ኣሊ ኢምራን:195) እንዲህም አለ (ከወንድ ወይም ከሴት እርሱ አማኝ ሆኖ በጎን የሰራ መልካም ኑሮን በእርግጥ እናኖረዋለን ይሰሩትም ከነበሩት ነገር መልካም ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን) (አን -ነህል:97) እናም በኢስላም መምጣት ህብረተሰቡ የነፈጋትን መብት ተቀዳጀች፤ የሴት ክብርና ሰበአዊነቷ ሲመለስ ከወንድ ጋር እኩል ፍጡር መሆኗ ተረጋገጠ:: ሴት ህፃንን መግደል ህገ ወጥ እርኩስ ተግባር በመሆኑ በቁርአን ተወገዘ:: አላህ እንዲህ አለ«ከነሕይወቷ የተቀበረችው ሴት ልጅ በምን ወንጀል እንደተገደለች፤ በተጠየቀች ጊዜ፤ » የአላህ መልዕክተኛም ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ ብለዋል:. «በእርግጥ አላህ ለወላጆቹ ቅን አለመሆንን፤ ሴት ልጆችን በሕይወት መቅበርንና ልመናን በናንተ ላይ ክልክል አድርጓል:: እንዲሁም አሉባልታን፤ ጥያቄ ማብዛትንና ገንዘብ ማባከንን ጠልቶባችኋል» ሴቶች ከተጎናፀፋት የተፈጥሮ መብታቸው ዉስጥ የንብረታቸው ብቸኛ ባለቤት መሆናቸው፤ የራሳቸው ገንዘብና ሃብት ያላቸውና ለቤተሰቡ ማውጣት ግዴታ እንደሌለባቸው፤ ትዳር በፍቃዳቸው እንጂ እንደማይሆን እና ካገባች በኋላ ስሟ በባሏ ስም እንደማይጠራ /እንደማይለወጥ /ተረጋገጠ::

ነብዩ (ﷺ) ኢማሙ አህመድ በዘገቡት ሐዲስ «ሴትን ልጅ አትጥሉ ፤ ውዶችና አጫዋቾች ናቸውና» ብለዋል:: ይህ ነብያዊ አዋጅ የታወጀላቸው (የሴቶች) የልደት ቀን የሀዘን ቀን ተደርጎ ይታሰብ ከነበረበት የማህይም ዘመን በኃላ ነው:: ቁርአን ይህን ማህይምነት ሲገልፀው

(ለአላህ ከመላዕክት ሴቶች ልጆችን ያደርጋሉ:: ጥራት ይገባው:: ለእነርሱ ግን የሚፈልጉትን ወንዶች ልጆችን ያደ ርጋሉ:: አንዳቸው ከመሀከላቸው አንዱ በሴት ልጅ በተ በሰረ ጊዜ እርሱ የተቆጨ ኾኖ ፊቱ ጠቁሮ ቅስሙ ይሰበ ራል:: ከተበሰረበት ነገር መጥፎነት በውርደት ላይ ኾኖም ቢሆን ይያዘውን ? ወይስ በአፈር ውስጥ ይደብቀውን ? በማለት ከሰዎች ይደበቃል:: ንቁ ! የሚፈርዱት ፍርድ ምንኛ ከፋ!» አን -ነህል፡ 57-59.

ህፃኗ ከእነህይወቷ ከመቀበር ካመለጠች እንኳን ስትኖር ተዋርዳና ተንቃ እንደሀብት ትወረስና ትሸጥ የነበረችበት አስቀያሚና አስከፊ ህይወት ነው:: ቁርኣን እነዲህ አለ( (ከተከለከላችሁት ወንጀሎች ታላላቆችን ብትርቁ ትናንሽ ኃጢአቶችን እናብስላችኋለን:: የተከበረውንም ገነት እና ስገባችኋለን:: አላህ ከፊላችሁን በከፊሉ ያበለጠበትን ፀጋ አትመኙ:: ለወንዶችም ከሰሩት ስራ እድል አለላቸው:: ለሴቶችም ከሰሩት ስራ እንዲሁ እድል አለላቸው:: አላህን ከችሮታው ለምኑት:: አላህ በሁሉ ነገር አዋቂ ነውና) አን -ኒሳእ፡31-32.

አንቀፆቹ የወረዱበት ምክንያት:- ኡሙ ሰለማ የተባሉ የነብዩ (ﷺ) ሶለሏህ ዐለይሂ ወሰለም ባለቤት ሶሀብያ «በወ ንዶች ላይ ዘመቻ ግዳጅ ሆኖ ሲዘምቱ እኛስ ለምን አንዘ ምትም ! ለምንስ በውርስ ወቅት የወንድ ግማሽ ብቻ እን ድንወርስ ተደነገገ:: ብለው ላቀረቡት ጥያቄ መልስ ለመስ ጠት ወረደና በማለት ነፃነቷን አወጀላት:: :: (ቲርሚዚ ፤ ሓኪም ፤ ዋሂዲ) ከእነዚህ አናቅፅ ውስጥ የተወሰኑት ቁር አናዊ አናቅፅ ኡሙ ሰለማ የተባሉ የነብዩ (ﷺ) ባለቤት ሶሀብያ «በወንዶች ላይዘመቻ ግዳጅ ሆኖ ሲዘምቱ እኛስ ለምን አንዘምትም! ለምንስ በውርስ ወቅት የወንድ ግማሽ ብቻ እንድንወርስ ተደነገገ:: ብለው ላቀረቡት ጥያቄ መልስ ለመስጠት ወረደ:: ሚስትም ስትሆን እናንተ በአላህ ያመ ናችሁ ሰዎች ሆይ ! ሴቶችን ያስገደዳችሁ ሆናችሁ ልትወ ርሱና ግልፅ የሆነ መጥፎ ስራ ካልሰሩ በስተቀር ከሰጣ ችኋቸው ከፊሉን ልትወስዱባቸውና ልታጉላሏዋቸው አይ ፈቀድላችሁም:: በመልካም ተኗኗሯዋቸው:: ብትጠሏቸ ውም እንኳን ታገሱ:: አንድ ነገር ብትጠሉትም አላህ በእርሱ ብዙ ደግ ነገሮችን ሊያደርግላችሁ ይችላልና:: አን-ኒሳእ ከ19. የተፈቱ ሴቶች በራሳቸው ሐሊናዊ ሀላፊነት ሶስትን ወር ይጠብቁ:: እርቅን ከፈለጉ፤ በአላህና በመጨ ረሻው ቀን የሚያምኑ ከሆኑ አላህ በማህፀኖቻቸው ውስጥ የተፈጠረውን ፅንስ ሊደብቁ አይፈቅድላቸውም:: ባሎቻ ቸውም በእነዚህ ወራት ውስጥ የመመለስ መብታቸው ቅድሚያ ነው:: ለሴቶች ግዳጅ እንዳለባቸው ሁሉ ፍትሀዊ መብትም አላቸው:: ይሁንና ወንዶች የበለጠ ሀላፊነት ተጥ ሎባቸዋል:: አላህ አሸናፊና ጥበበኛ ነውና«

ከዚያም እናት ስትሆን በጣም እንድትከበር ቁርኣን እንዲህ ይላል::“የሰውን ልጅ ለወላጆቹ በጎመዋል እንዳለበት በጥብቅ አዘዝነው:: እናቱ በችግርም ላይ ሆና አረገዘችው: : በችግርም ላይ ሆና ወለደችው:: እርግዝናውና ከጡት መለያው ሙሉ ሰላሳ ወርነው:: ከእዚያ የጥንካሬውን ወቅት በደረሰ ጊዜ አርባ ዓመት በደረሰ ጊዜ ጌታዬ ሆይ! ያን በእኔ ላይና በወላጆች ላይ የለገስከዉን ፀጋን እንድናመ ሰግንህና የምትወደውን መልካም ስራ እንድሰራ ወደቀናው መንገድምራኝ:: ዘሮቼንምለ እኔአብጅልኝ:: እኔ ወደ አንተ ብቻ ተመለስኩ:: እኔከሙስሊሞችአንዱ ነኝአለ:: እነዚህ ይህንንባዩችከገነት ጓዶች ውስጥ ሲሆኑ እነዚያ ከሰሩት ስራ መልካሙን የምንቀበላቸውና ከኃጢአቶቻቸውም የምናል ፋቸውሰዎችናቸው:: ያንንተስፋይሰጡት የነበሩትን እውነ ተኛ ቀጠሮ እንሞላላቸዋለን” አህቃፍ 15-16 . አቡ ሑረይራ “አንድ ሰው ወደ ነብዩ (ﷺ) ዘንደ መጣና አንቱ የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! ከሰዎች ሁሉ በበለጠ ጓደኝነቱን ወይም ግንኙነቱን ልጠብቅለት የሚገባው ማን ነው አላቸው እሳ ቸዉም እናትህ አሉት:: ከዚያስ አላቸው እናትህ አሉት፤ ከዚያስ አላቸውእናትህ አሉት ፤ከዚያስ አላቸው እናትህ አሉት፤ ከዚያስ አላቸው አባትህ አሉት ” ብለዋል:: ቡኻሪና ሙስሊም .

አንድ ሰው እናቱን በጀርባው ተሸክሞ እየጠወፈ ዐብዱ ሏህ ኢብን ዑመርን አግኝቶ ዉለታዋን ከፈልኳት ማለት ይቻላል ሲላቸው “በፍፁም የአንዲቱን የምጥ ህመም እንኳን አይሸፍንም አሉት”ይህ ክብር በዚያ በታላቁ የመ ሰናበቻ ሐጅ ላይ በይፋ የታወጀው:: በብዙ የሐጅ ተግ

ባራት ላይ እንደ ወንድ መሆናቸውና አንዳንድ የሚለዩባቸ ዉን በግልፅ አስተምረዋል፡፡ ካላቸው ድክመት ጋር የሚ ስማሙትን ጉዳዮች ለምሳሌ ሙዚይሊፋ ከግፊው በፊት መውጣትና ጠጠር መወርወርን፣ ካልቻለች ጭራሹን ሌላን ሰው መተካትን ፈቅዶላታል፡፡ ከሴትነቷ ጋር የማ ይስማሙ ነገሮችን ለምሳሌ በጠዋፍ ላይ ሰምሶማን በሳዕይ ላይ ሩጫን አንስቶላታል፡፡ ከባዕድ ወንድ ለመደበቅና ፊትን ከኒቃብ ሌላ በሆነ ነገር መደበቅን ፈቅዷል፡፡

ሐይድ ሲመጣባት የመሰናበቻውን ጠዋፍ ፈቀደላት፡፡ ከዚያም ነብዩ (ﷺ) በዚሁ በዐረፋ ኹጥባ ላይ ሴቶችን የተመለከተ ልዩ አደራ አስተላለፉ፡፡

ሴት ልጅ በኢስላም መብቷን መጠየቅ የደረሰባትን ግፍ መከላከል መብቷ ነው፡፡ ኢስላማዊ አስተምህሮቶች በግልፅ ወንድና ሴት የሚለያዩባቸውን ጥቂት ጉዳዮች ላይ ካልሆነ በስተቀር ሌላው ነገሮች ላይ በሁሉም እኩል ናቸው፡ ፡ ሽሪዓ የፆታ ልዩነቶችንና ተስማሚነትን ይጥብቃል፡፡ አሏህ በቁርኣን “ የፈጠረ አምላክ ጥጥእርሱ እውቀት ረቂቁ ውስጥ ዐዋቂው ሲሆን (ምስጢርን ሁሉ) አያውቅምን ?” ብሏል፡፡ ሴት ልጅ ለራሷ ተስማሚ የሆነ ስራ ያላት ሲሆን ወንድም እንዲሁ የራሱ የሆነ ስራ አለው፡፡ አንዱ በሌላው ስራ ጣልቃ መግባት በህይወት ሚዛን ላይ ችግር ይፍጥ ራሉ፡፡ ሴት ልጅ በቤቷ ቁጭ ብላ ወንድ በየቦታው ለፍቶ የሚያገኘውን ያህል ታገኛለች፡፡

ሀ. ነብዩ (ﷺ) በይሀቂ በዘገቡት ሀዲስ አስማእ ቢንት የዚድ የተባለች ሴት ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ከሱሃባወቻ ቸው መካከል ባሉበት መጥታ እኔ ወደ እርስዎ የተላኩ የሴቶች መልእክተኛ ነኝ በምስራቅ ትሁን በምዕራብ የእኔን ተልዕኮ ትስማም አትስማም ሁሉም ሴቶች በዚሁ ሀሳብ ላይ ይስማሙበታል፡፡ ይኸው አሏህ ለወንዶችም ለሴቶ ችም በትክክል ለከዎታል እናም በእርሰዎም በላከዎት ጌታም በአሏህ አምነናል፡፡ እኛ ሴቶች በቤት ውስጥ የተ ገደብንና የተወሰንን የቤቶቻችሁ ጠባቂዎች የስሜታችሁ መጫወቻ የልጆቻችሁ ተሸካሚዎች ነን፡፡ እናንተ ወንዶች ግን ከእኛ በተለየ በጁመዓና በጀመዓ በሺተኞችን በመጎብ ኘት የሞተን በመቅበር በየጊዜው ሀጅ በማድረግ ታድላች ኋል፡፡ ከዚህ ሁሉ የሚበልጠው ደግሞ ለአሏህ ሲባል እስከ ህይወት መሰዕዋት ለመክፈል ተመርጣችኃል፡፡ ወንዶች ለሀጅ ወይም ለኡምራ ለጅሀድ ስትወጡ ንብረታችሁን እን ጠብቃለን ልብሶቻችሁን እንፈትላለን ልጆቻችሁን እናሳድ ጋለን እና በምንዳው አንጋራችሁምን? አለች፡፡ በዚህ ጊዜ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ( ወደ ሰሃቦች መለስ ብለው ስለዲኗ የጠየቀች ሴት ከዚች ሴት የበለጠች ሰምታችኃል? ሱሃቦ ችም ሲሉ መለሱ የአሏህ መልእክተኛ ሴት ልጅ እንዲህ ያለ ጥያቄ ታቀርባለች ብለን አስበን አናውቅም አሉ፡፡ ከዚያም ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ወደ እርሷ ዘወር ብለው “ ተመለሺ የላኩሽን ሴቶች ማንኛውም ሴት ለባሏ ጥሩ ሴት መሆኗ የእሱን ደስታ ማሰቧ ፈቃዱን መከተሏ ይህን ሁሉ ይመዝ ናል ” ብለሽ አስተምሪ ሲሏት ላኢላሀኢለሏህ አሏሁ አክበር እያለች በደስታ ተመለሰች፡፡ ነብዩ (ﷺ) በይሀቂ በዘገቡት ሀዲስ“ ውስን ሴቶች ወደ ነብዩ (ﷺ) መጥተው ወንዶች በእኛ ከኛ በጅሃድ በለጡን እነሱን የምንደርስበት ሌላ ስራ የለንም ወይ? በማለት ጠይቀዋቸዋል ሴት ልጅ የቤት ስራዋን በመስራቷ ብቻ የሙጃሂድኖችን አጅር ያስጣታል” ብለዋል፡፡ ከዚያም አልፎ ለሴት ዘመድ በጎ መዋል ከፍተኛ ተግባር እንደሆነ ነብዩ (ﷺ) አህመድና ጦበራኒ በዘገቡት ሀዲስ “ሁለት ሴት ልጆች ወይም ለሁለት እህቶች ወይም ለሁለት ለዝምድና ባላቤት ሴቶች አሏህ እስከሚያበቃቃ ቸው ድረስ ለአሏህ ብሎ የረዳቸው ሰው ከጀሀነም እሳት መከላከያ ይሆንለታል” ብለዋል፡፡

<u>ከሴቶች ጉዳዮች መካከል በጥቂቱ</u>

ዘመዱ ካልሆነች ሴት ጋር ብቻውን መሆን ክልክል ነው፡ ፡ ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ “ ዘመዷ አብሯት ከሌለ ሴት ጋር ለብቻው አይሁን” ብለዋል፡፡

ሴት ልጅ ወደ መስጊድ ሄዳ መስገድ ትችላለች፡፡ ሆኖም ፊትና ከፈራች ግን መሔዷ ይጠላባታል፡፡ እናታችን አዒሻ ነብዩ “ ሴቶች አሁን አሁን ያመጡትን ቢያውቁ ኑሮ የቢኒ ኢስራኤል ሴቶች እንደተከለከሉ ሁሉ ይከለክሏቸው ነበር” ብለዋል፡፡ የወንድ ልጅ ሰላት በመስጊድ ሲሰገድ እጥፍ ድርብ እንድሚሆን ሁሉ የሴት ልጅ ሰላት ደግሞ በቤት ሲሰገድ እጥፍ ድርብ ይሆናል፡፡ ነብዩ (ﷺ) አህመድ በዘ

ገቡት ሀዲስ “” አንዲት ሴት ወደ ነቢይ ( መጥታ ከእር ስዎ ጋር መስገድ ደስ ይለኛል ስትላቸው አዎ! ከእኔ ጋር መስገድ ደስ እንደሚልሽ አቃላሁ ነገረ ግን በጓዳሽ ውስጥ መስገድሽ ምንዳው በቤትሽ ውስጥ ከመስገድሽ ይበልጣል፡ ፡ በቤትሽ ውስጥ መስገድሽ ምንዳው በግቢሽ ውስጥ ከመ ስገድሽ ይበልጣል፡፡ በግቢሽ ውስጥ መስገድሽ በሰፈርሽ መስጊድ ውስጥ ከመስገድሽ ይበልጣል፡፡ በሰፈርሽ መስጊድ ውስጥ መስገድሽ በእኔ መስጅድ ውስጥ ከመስገድሽ ይበል ጣል” ብለዋል፡፡ እንደዚሁም ነብዩ (ﷺ) (አህመድ በዘገ ቡት ሀዲስ “ ከሴቶች መስጊዶች የሚበልጠው ቤቶቻቸው ናቸው” ብለዋል፡፡

ሴት ልጅ አብሯት የሚሄድ ወንድ ዘመድ ካላገኘች በስ ተቀር ሀጅም ሆነ ዑምራ ግዴታ የለባትም፡፡ ያለዘመድ መጓዝም አይፈቀድላትምና ነው፡፡ ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት“ ሴት ልጅ ከሶስት ቀን ሌሊተ በላይ የሆነን መንገድ ያለ ዘመድ እንዳትጓዝ” ብለዋል፡፡

ለሴት ልጅ መቃብር መጎብኘትና ጀናዛ መሸኘት ክልክል ነው፡፡ ነብዩ (ﷺ)“ ቀብር ጎብኚ ሴቶችን አሏህ እርግማኑን ያውርድባቸው”ብለዋል፡፡ ሙስሊም በዘገቡት ዘገባ ኡሙ አጢያ“ ጀናዛ መከተል ተከልክለናል ግዴታ ግን አልተደረገ ብንም ነበር” ብለዋል፡፡

እጮኛን በማያታልል መልኩ ሴት ልጅ ፀጉሯን ከጥቁር ቀለም በስተቀር በፈለገችውየ ቀለም አይነት ማቅለምትችላ ለች፡፡ ጥቁርግንይጠላል፡፡

ሴት ልጅ አሏህ የወሰነላትን የውርስድርሻልትወስድይገባ ታል፡፡ መከልከሉምአይፈቀድም፡፡

ነብዩ (ﷺ) ኢብኑ ማጃህ በዘገቡት ሀዲስ“ የወራሹን ውርስ ያቋረጠ በጀነት የሚወርሰው የቂያማ እለት አሏህ ይቆርጥ በታል” ብለዋል፡፡

ባል ሚስትን መቀለብ ግዴታው ነው፡፡ ይህም ሲባል ሴት ልጅ የሚያስፈልጋትን ልብስ፤ ምግብና መጠለያ ያጠቃል ላል፡፡ አሏህ“ የችሎታ ባለቤት በችሎታው ልክ ይቀልብ፡ ፡ በእርሱም ላይ ሲሳዩ የተጣበበበት ሰው አሏህ ከሰጠው ይስጥ፡፡ ነፍስን የሰጣትን ያህል እንጅ አያስገድድም” ብሏል፡፡ በኢስላም ባል ሚስትን መቀለብ ግዴታው ነው፡ ፡ ሴት ልጅ፤ ባል፤ የሌላት ከሆነች አባቷ ወይም ወንድሟ ወይም ልጇ መቀለብ ግዴታው ነው፡፡ የቅርብ ዘመድ የሌላት ሴት ከሆነች ደግሞ የምትኖርበት ማህበረሰብ ሊቀ ልባት ይገባል፡፡ ምክንያቱም ነብዩ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሀዲስ (ለድሆች ባል አልባዎች የሚለፉ ሰው ጅሀድ እንደ ወጣ ወይም ሌሊቱን ቆሞ ቀኑንፆም እንደሚ ያሳልፍ ነው) ብለዋል፡፡

1-ሴት ልጅ እስካላገባች ድረስ ከቀድሞ ባሏ የወለደቻቸ ውን ልጆች ማሳደግ ላይ ባለ ሙሉ መብት ናት፡፡ አባትም በዚህ ጊዜ የልጆችን ቀለብ ለእናት መስጠት አለበት፡፡

2-የፊትንና የቅንድብን ፀጉር መንጩት ክልክል ነው፡፡ ነብዩ (ﷺ) አቡ ዳውድ በዘገቡት ሀዲስ “ ቀንዳቢን እና ተቀንዳ ቢን የአሏህ እርግማን ይውረድባቸው” ብለዋል፡፡

3- ሴት ከባሏ በስተቀር ከሶስትቀን በላይ ማዘን ክልክል ነው፡፡ ነብዩ (ﷺ) ሙስሊም በዘገቡትሀዲስ“ በአሏህና በመጨረሻው ቀን የምታምን ሴት ከባሏበስተቀር ከሶስት ቀን በላይ ማዘን አይፈቀድላትም” ብለዋል፡፡ ነገር ግን ለባሏ አራት ወር ከአስር ቀን ድረስልታዝንለትግዴታአለ ባት፡፡ በሐዘን ስዓት ጌጣጌጥና ዘዕፍራንን የመሰለ ሽቶዎች መጠቀም በጥቁር ኩል በቅባት እራሷን ማሳመር የለባትም፡ ፡ ጥፍሯን መቁረጥ ብትብቻዋን መንጩት መታጠብ ይፈ ቀድላታል፡፡ የምትለብሰው ልብስ በቀለም ለምሳሌጥቁር.... ተብሎ አይወሰንም፡፡ ዒዳዋን መቆጠር ያለባት ባሏ ሲሞት በነበረችበት ቤት ውስጥ ሆናነው፡፡ በጣም አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር ከዚያ ቤት መውጣት አትችልም፡፡ ለወሳኝ ነገር ያውም በቀን ብቻ እንጂ በዒዳዋ ጊዜ ከቤት መውጣት የለባትም፡፡

ሴት በጣም ችግር ካልገጠማት በስተቀር የራስ ፀጉሯን መላጨት ክልክል ነው፡፡ ከወንድ ጋር በማያመሳስላትመ ጠንማሳጠርትችላለች፡፡ ነብዩ (ﷺ) ቲርሚዚበዘገቡት ሀዲ ስ“በወንድ የሚመሳሰሉትን ሴቶችን ነብዩ (ﷺ) ረግመዋቸ ዋል” ወይም ከካፊር ሴቶች በማያስመስላት መልኩ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ኢባዳ“ ከሰዎች ጋር የተመሳሰለ ሰው ከእነሱ ነው”ብለዋል፡፡ ሴት ከቤቷ ስትወጣ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ባሟላ ጅልባብ አካሏን መሸፈን ግዴታ ነው፡ ፡ ገላዋንሁሉመሸፈን፤ በራሱዉበትያለሆነ; የማያሳምርወ

ፍራምየሆነ፤ የማያጣብቅሰፊየሆነ፤ ሽቶያልተቀባ፤ የወንድ ልብስ የማይመስል; የካፊር ሴቶችን ልብስ የማየመስል; ልዩ የሚያደረጋት ልብስ ያልሆነ ናቸው፡፡ በተጨማሪም የሰውም ሆነ የእንስሳ ስዕል ያለበትን መልበስ ክልክል ነው፡፡ ማንጠልጠል ግርግዳ ላይም መለጠፍክልክልነው፡ ፡ መሸጥም እንዲሁ ክልክል ነው፡፡ የሴት ልጅ ሀፍረተ ገላ ከሌላ ጋር ስትሆን ሶስት ክፍል አለው፡፡

1. ባል እሱ ከሷ የፈለገውን ማየት ይችላል

2. ሴቶችና ወንዶች ዘመዶቿ አብዛኛውን ጊዜ የሚታየውን አካሏን ማለትም ፊቷን፣ትከሻዋን፣እጇቿን ክንድ እግርና የመሳሰለውን ማየት ይቻላል 3.ሌሎች ወንዶች ለማጨት ለህክምና እና ለመሳሰሉ ምክንያቶች ካልሆኑ በስተቀር ምኗንም መቼም ጊዜ ማየት አይፈቀድላቸውም፡፡ ምክን ያቱም ሴት ልጅ የምትፈተ ነው በፊቷ ነውና፡፡ ፋጡማ ቢንቱ ሙንዚር ሀኪም በዘገቡት ሀዲስ ፊቶቻችንን ከወ ንዶች እንሸፍን ነበር ብለዋል፡፡ አዒሻ አቡዳውድ በዘገ ቡት ሀዲስ እኛ ከነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ጋር ኢህራም ላይ እያለን የወንድ ቡድኖች በአጠገባችን ሲያልፍ እያንዳንዳ ችን ጅልባባችንን ከራሳችን ወደ ፊታችን እናወርደው ነበር፡ ፡ ሲያልጁፉን ደግሞ ፊታችንን እንገልጥ እና እንደልባችን እንቀሳቀስ ነበር፡፡


ዒዳዎች፡-ዒዳዎች ብዙ ናቸው፡፡ እነሱም

1. ነፍሰጡር የሆነች ሴት የፍችም ይሁን የሞት ዒዳዋ ፅንሷን መውለዷ ብቻ ነው፡፡

2. ባሏ የሞተባት ሴት ዒዳዋ አራት ወር ከአስር ቀን መጠበቅ ነው፡፡

3. የወር አበባ የምታይ ሁናየ ተፈታች ሴት ዒዳሶስት የወር አበባ ማየት ሲሆን፤ ዒዳዋ የሚያበቃው ከሶስተኛው የወር አበባ ደም በፀዳች ጊዜ ነው፡፡

4. የወር አበባ የማታይ ሴት ደግሞ ዒዳዋ ሶስት ወር ብቻ መጠበቅነው፡፡ በአስመላሽ ፍች ዒዳ ስር ያለች ሴት ሁሉ ከባሏ ጋር መኖር ግዴታዋ ነው፡፡ ሲኖሩም ከእሷ ጋራ መቀ መጥም ሆነ ከእሷ ጋር የፈለገውን አካል ማየት ይፈቀድለ ታል፡፡ ምን አልባትም አሏህ ቢመልሳቸውና ቢያስታርቃ ችው ተብሎ ዒዳዋ እስከሚያበቃ ድረስ ከእሷ ጋር ብቻ ቸውን መሆንም እንኳን ይችላል፡፡ መልሸሻለሁ' በማለት ወይም የግብረ ስጋ ግንኙነትን በመፈፀም ብቻ የተፈታች ሴት ወደ ሚስትነት ትመለሳለች፡፡ በዚህ ላይ የሴትየዋ መስ ማማት አያስፈልግም (ግዴት አይደለም) ሴት ራሷን አት ድርም ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) አቡ ዳውድ በዘገቡት ሀዲስ“ ያለ ዘመድ ፈቃድ ራሷን የዳረች ሴት ጋብቻዋ ውድቅ ነው” ብለዋል የሌላ ሴት ፀጉርም ሆነ የእንስሳ ፀጉር በፀጉር ላይ መቀጠል ክልክል ነው፡፡ ከአካላቷ መካከልም አንዱንም መነቀስ ክልክል ነው፡፡ ሁለቱም ተግባሮች ከታላላቅ ወንጀ ሎች የሚቆጠሩ ናቸው፡፡ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሀዲስ“ ቀጣይም አስቀጣ ያዋም ነቃሿ ተነቃሿም የአሏህ እርግማን ይውረድባቸው” ብለዋል ያለ ምንም ምክንያት ፍች መጠየቅ ክልክል ነው፡፡ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) አቡ ዳውድ በዘገቡት ሀዲስ“ ያለምንም ምክንያት ከባሏ ፍች የጠየቀች ሴት የጀነት ሽታ በእሷ ላይ እርምነው” ብለዋል፡፡ ሴት ባሏን በአግባቡ መታዘዝ አለባት ፡፡ በተለይም ለመኝታ ከጠየቃት ፡፡ ይህን ጉዳይ በተመለከተ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ቡኻሪና ሙስሊም በዘ ገቡት ሀዲስ“ ባል ሚስቱን ለምኝታ ጠይቋት እምቢ ካለች እና ተቆጥቶባት ካደረ እስከጧት ድረስ መላኢካ ይረግሟታ ል”ብለዋል፡፡ በመንገዱ ላይ ወንዶች እንደሚኖሩ ያወቀች ሴት ሽቶ ተቀብታ በእነሱ አጠገብ ማለፍ የለባትም፡፡ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) አቡ ዳውድ በዘገቡት ሀዲስ“ ሴት ሽቶ ተቀብታ ወንዶች ሽታውን እንዲጣጥሙላት ብላ በወንዶች አጠገብ ካለፈች እሷ እንደዚህ ዝሙተኛ ናት” ብለዋል፡፡ የሴትን ልጅ ታላቅ ታሪክ ከሚያስታውሱን ጉዳዮች በሶፋና መርዋ መሐከል የሚደርገው የምልልስ አምልኮ ጅማሪ የሆ ነችው ሴት የሐጀር ታሪክ አንዱ ነው፡፡ በተጭማሪ የዘም ዘም ውሃን በጠጣህ ቁጥር እሷን ታስታውሳለህ፡፡ በዚህ ቦታ መወሳት ካለባቸው ሴቶች መካከል ዙበይዳ የሀሩኑ ረሺድ ባለቤት ነበረች፡፡ ከባግዳድ እስከ መካ ድረስ ለሑጃ ጆች መንገድ ያስተካከለችና በየቦታው ማረፊያ ኬላዎችን 3 ያሰራች በተጨማሪም ወደ ሀረም ውሀን ያስገባች እስከአሁ ንም ድረስ ታሪኳ ቁልጭ ያለ ነው፡፡ ይህ በአጭሩ ኢስላም ለሴቶች የሰጠውን ልዩ ትኩረት የሚጠቁም ነው፡፡ የኢ ስላም ጠላቶች እንኳን ለሴት ልጅ እንደ ኢስላም ሙሉ ክብሯንና መብቷን የሰጣት እንድሌለ በየ አጋጣሚው ይመ ሰክራሉ፡፡ በአቃላይ የሴትን ማዕረግ በተመለከተ ቁርአን እንዲህ በማለት ያጠቃልለዋል፡፡ «እናም ጌታቸው እኔ ከእ ናንተ ውስጥ የወንድም ሆነ የሴትን መልካም ስራ ወሮታ አላጠፋም፡፡ ከፊላችሁ የከፊሉ አካል ነውና በማለት ልመ ናቸውን ተቀበላቸው) 3:195. ሁለቱም የትዳር አጋሮች የአላህ አማና የሆነዉን ትዳርን በአግባቡ በመቀም የዱንያ ብቻ ሳይሆን የአኺራም ሕይወት ማሳመሪያ እንዲያደርጉት አደራ ።





# መፈተን

ይህ ዐለም የፈተና ዐለም ነው፡፡ ማንም ሰው በዚህ ዐለም መፈተኑ አይቀርም፡፡ ከዚያም መጨረሻው ወደ አላህ ነው፡፡ አላህ እንዲህ አለ፡- <<በሰማያትና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የአላህ ነው እነዚያን ያጠፉትን በተግባራቸው ልክ ሊመነዳና እነዚያን መልካም የሰሩትን በመልካሟ /በጀነት/ ሊመነዳነው፡፡ አንነጅም.31. እንዲህም አለ፡-<<ነፍስ ሁሉ ሞትን ቀማሽ ናት፡፡ ለመፈተን ምነ ብለን በክፉም ሆነ በበጎ እንሞክራችኋለን፤ወደኛም ትመለሳላችሁ›› አል-አንቢያእ.35. በዚህ ዐለም ላይ ስንኖር መፈተን አንዳንደ ጊዜ በጥሩ ነገር፤ በሌላ ጊዜ ደግሞ በመጥፎ ነገር፤ አንዳንድ ገዜ በጤና በሌላጊዜ በበሽታ፤ አንዳንድ ጊዜ በሐብት፤ በሌላ ጊዜ በችግር ሊሆን ይችላል፡፡ሙስሊም በሁሉም የፈተና አይነቶች ሊፈተን ይችላል፡፡ ሆኖም ከወፈቀው በሁሉም ጊዜ ወደ እድገት የሚረማመድበት ነው፡፡ ‹‹የሙዕሚኖች ጉዳይ ይገርማል፡፡ አላህ በሱ ላይ ምንንም ነገር አይፈርድበትም ለሱ ጥሩ ቢሆንለት እንጂ››፡፡ አህመድ.

ምንም ነገር የሚለው ቃል በደግም ሆነ በመጥፎ መፈተንን ያካትታል፡፡ ‹‹የሙእሚን ጉዳይይገርማል፡፡ የሙእሚን ነገር ሁሉም ኸይር ነው፡፡ ይህ እድል ለሙእሚን እንጂ ለማንም አይሆንም፡፡ መልካም ነገር ካጋጠመው ያ፣ መሰግንና ኸይርይሆንለታል፡፡ መጥፎም ነገር ካጋጠመው ይታገስና ጥሩ ይሆንለታል›› ሙስሊም. እንዲህም አለ፡- የሰው ልጅ ጌታው በሞከረው ጊዜ ባከበረውና ባጣቀመው ጊዜ ጌታ የአከበረኝ አበለጠኝ ይላል፡፡በሞከረውና በእርሱ ላይ ሲሳዩን ባጠበበበት ጊዜ እንዲሁ ጌታየ አሳነሳኝ ይላል›› አል ፈጅር 15-16.

አላህ በቁርኣን ዉስጥ አራት ምእራፍ ላይ እንዲህ አለ፡-(በዚህ  ውስጥ በብዙ ታጋሽና  በብዙ አመስጋኝ ለሆኑት ሁሉ በእርግጥተ አምራቶች አሉበት) ጭንቀቶችን ከላያችን ላይ ለማስወገድ ይላሉም ምስጋና ሁሉ ለእዚያ ከእኛ ላይ ሐዘንን፤ላስ ወገደልን ይገባው፡፡ አላህ ጌታችን በጣም መሃሪና አመስጋኝ ነውና፡፡  እርሱም ያ ከችሮታው የዘላለም መኖሪያን አገር ያሰፈረን ነው፡፡በእርሷም ውስጥ መከራ አይነካንም  በእርሷምውስጥድካምአይነካንም›› ፋጢር 34-35. እንዲህም አለ፡-<<ከወንድም ይሁን ከሴት አማኝ ኾኖ በጎን የሠራ መልካም ኑሮን እና ኖረዋለን ይሠሩት ከነበሩት ነገር በመልካሙም ምንዳቸውን እንመነዳቸዋለን›› አን-ነህል97. እንዲህም አለ፡-<<አማኞች ሆይ ! የመቁስል ጉዳት ቢያገኛችሁ ሌሎች ህዝቦችም መሰሉ የመቁሰል ጉዳት አግኝቷቸዋል፡፡እንዲህ አይነቶችን ቀናት በሰዎች መካከል እናፈራርቃቸዋለን፡፡ አላህ እነዚያን በትክክል በሱ ያመኑትን ሊያሳውቅና (ከእናንተም መካከል ሰማዕታትን ሊመርጥ እንዲህ አይነት ቀናት እንዲፈራረቁ ያደርጋል፡፡ አላህ በዳዩችን ሁሉ አይወድምና›› ኣሊ ዒምራን 140. እንዲህም አለ፡-<<በሰማያ

ትና በምድር ውስጥ ያለው ሁሉ የአላህ ነው፡፡ እነዚያን ያጠፉትን በተግባራቸው ለመነዳና እነዚያን መልካም የሰሩት በመልካሟ /በጀነት/ ሊመነዳ ነው>> አንነጅም31. እንዲህም አለ፡-<<እናንተ ሰዎች ሆይ ! የአላህ ቀጠሮ እውነት ነው፡፡ እናም የቅርቢቱ ህይወት አታታላችሁ፡፡ አታላዩም ሰይጣን በአላህ ትዕዛዝ ላይ አያታላችሁ» ፋጢር 5. እንዲህም አለ፡-<<መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! ባሮቼ ስለ እኔ በጠየቁህ ጊዜ እኔ ቅርብ ነኝ፡፡ የለማኝን ፀሎት በለመነኝ ጊዜ እቀበለዋለሁ፡፡ስለዚህ ወደ ቀናው መንገድ ይመሩ ዘንድ ለእኔ ብቻ ይታዘዙ፡፡በእኔም ብቻ ይመኑ በላቸው » አልበቀረህ 186.

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡-«አላህ እንዲህ ብሏል፡ - ከኔ ሌላ ያለን አምላክ አድርጎ በያዘ ሰው ላይ ጦርነት አውጀበታለሁ፡፡ ባሪያዬ እኔ በርሱ ላይ ግዴታ ካደረኩበት ነገሮች ውጪ ባሉ ተግባራት ወደኔ መቅረቡ የበለጠ በእኔ ዘንድ የተወደደ ነገር ነው፡፡ ባሪያዬ እስከወደደው ድረስ ግዴታ ባል ሆኑ ተግባራት ወደኔ ከመቅረቡ አይታክትም፡፡ ስለዚህ የሚሰማበት ጆሮ፤የሚመለከትበት አይን፣ የሚዳስስበት እጅ፣ የሚሄድበት እግር እሆን ለታለሁ፡፡ ከጠየቀኝ በርግጥ እሰጠዋለሁ፡፡ከእኔ ጥበቃን ከፈለገ በእርግጥ እጠብቀዋለሁ» ሙሳም አለ ጌታዬ ሆይ ! ልቤን አስፋልኝ» ጧሃ 25.አላህ እንዲህ አለ፡-<<መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! አንብብ፡፡ጌታህ በጣም ቸር ነው።>>አልዐለቅ፣ .እንዲህም አለ፡-<< መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! በአጀምኛ የሆነ ቁርአን ባረግነው ኖሮ አንቀፆች በምናውቀው ቋንቋ አይብራሩም ኖሯልን ? ቁርአን አጀምኛና መልዕክተኛው አረባዊ ይሆናልን ? ባሉ ነበር፡፡እርሱ ለእነዚያ በአላህ ላመኑት ሰዎች ሁሉ መመሪያና መፈወሻ ነው፡፡ እነዚያም የማያምኑና በጆሮዎቻቸው ውስጥ ድንቁርና ነው አይሰሙትም፡፡ እርሱ በእነርሱ ላይ እውርነት ነው፡፡ እነዚያ ከሩቅ ስፍራ እንደሚጠሩ ናቸው፡፡ >> ፉሲለተ44. እንዲህም አለ፡-<<ከቁርአን ለምዕመናን መድሓኒትና እዝነት የሆነን እና ወርዳለን፡፡ በዳዮችንም ከሳራን እንጂ ሌላ አይጨመርላቸውም» አል-ኢስራእ 82. እንዲህም አለ፡-<<<<እነርሱም እነዚያ በአላህ ያመኑ ልቦቻቸውም አላህን በማውሳት የሚረኩ ናቸው፡፡ንቁ ! አላህን በማውሳት ልቦች ሁሉ ይረካሉ» አር-ረዕድ28.

በአጠቃላይ በዱንያ ላይ መሞከራችን በትዕግስት ካለፍነው ለሁለተኛው ዐለም ከፍተኛ ማዕረግ ከሚያስገኙ ተግባራት አንዱ ነው፡፡ ነቢዩ ቲርሚዚ በዘገቡትሐዲስ እንዲህ ብለዋል፡፡ (በራሱ፤ በልጁ፤ በንብረቱ በኩል በሙእሚን ላይ መከራዎች ከመውረድ አይቦዝኑም ከወንጀል የፀዳ ሁኖ ከአላህ ጋር እስኪገናኝ ድረስ፡፡)





# እምነታዊ ስህተቶች

እምነት ነክ ስህተቶች በሀገራችን በጣም ብዙ ናቸው:: ዋና ዋና የተባሉት ለአብነት ያክል ከዚህ በታች ያሉት ናቸው::

ስህተቶች በሁለት ይከፈላሉ:: <u>አንደኛው በጭራሽ ከኢስላም የሚያወጣ ሲሆን::</u> ሁለተኛ ደግሞ፡ - ጥራቱን የሚያጎድሉ ጉዳዮች /ወንጀሎኞች ናቸው:: ክህደት የመጨረሻ አስከፊ ጥፋት ከአላህ እርቅ ዘንድ የተ ወገዘ ምህረት የተነፈገው ከሽርክም በላይ የሆነ ወንጀል ነው:: ቁርአን በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፊ መግለጫ ሰጥቷል::

.<u>ሁለተኛው ክፍል እምነትን የሚጎዳ ሲሆን</u>፡- እሱም አማኝ ሆኖ ታላላቅ ወንጀሎችን የፈፀመ ሰው ካልቶበተና ወንጀ ሉን የሚያሳብስ መልካም ስራ ወይም በአማላጅ አማካ ኝነት ካላገኘ እሳት ይገባል:: በርሷ ውስጥ ግን አይዘወ ትርም:: ምክኒያቱም ከልቦናው ውስጥ ኢምንት ታክል ኢማን ያለው ሰው ሁሉ እሳት ቢገባም እንኳን በመጨረሻ መውጣቱ አይቀሬ ነውና:: በዚህ ርዕስ ስር አያሌ ስህተቶች አሉ:: ከዚህ በታች ያሉት ለአብነት ያክል የቀረቡ ናቸው::

1-ተውሒድን ክፉኛ ከሚጎዱ ነገሮች መካከል፣ ከድንጋዮች ወይም ከሌላ ነገር በረከትን መሻት ሌላው ቀርቶ ካዕባን እንኳ በረከትን በመሻት መሳለም ወይም መዳበስ ሽርክ ነው:: ዑመር ቢን አልኸጧብ ሐጀረል አስወድን እየሳሙ እንዲህ ብለዋል:: “የማትጎዳም የማትጠቅምም ድንጋይ መሆንህን አውቃለሁ:: የአላህ መልዕክተኛ ሲስሙህ ባላይ ኖሮ አልስምህም ነበር::

2-ከአላህ ሌላ ላለ አካል ማረድም ተውሒድን ያበላሻል:: ለምሳሌ ለወልይ፣ ለሰይጣን፣ ለአጋንንት አንዳች ጥቅም ይለግሱት ዘንድ በማሰብ ማረድ የትልቁ ሽርክ አካል ነው:: ከአላህ ሌላ ላለ አካል ከሚታረድበት ቦታ ላይ ለአላህም እንኳ ቢሆን ማረድም ክልክል ነው:: ይህ የተከለከለው ወደ ሽርክ የሚያደርሰን መንገድ ለመዝጋት ሲባል ነው::

3-ከአላህ ሌላ ለሆነ አካል መሳልም ሽርክ ነው:: ምክን ያቱም ስለት ኢባዳ በመሆኑ ለአላህ እንጂ ለሌላ አካል ሊውል አይገባውምና ነው::

4-ከአላህ ውጭ የሌላን አካል እገዛ መሻት ወይም በርሱ መጠበቅ ሽርክ ነው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ ለኢብን አባስ እንዲህ ብለዋቸዋል፡- "ስትለምን አላህን ብቻ ለምን፡፡ እገዛ ስትሻ አላህን ብቻ ጠይቅ" እናም አጋንንትንም ሆነ ሌላን አካል መማፀን ክልክል መሆኑን ይህ ሐዲስ ያስተምረናል፡፡

5-ወልዮችንና ደጋግ ሰዎችን ከተገቢ ቦታቸው በላይ ከፍ ማድረግም ተውሒድን ይጎዳል፡፡ ይኸውም እነኚህን ሰዎች ወደ መልዕክተኞች ደረጃ ከፍ ማድረግ ወይም ከስህተት የተጠበቁ ናቸው ብሎ ማመን ነው፡፡

6-ቀብርን መጠወፍ ሽርክ ነው፡፡ ተውሒድን ይቃረናል፡፡ ከቀብር ላይ መስገድም ወደ ሽርክ የሚያደርስ በመሆኑ ክልክል ነው፡፡ ለቀብር መስገድና ቀብርን ማምለክ ክልክልነቱ ከዚህ የከፋ እንደሆነ ጥርጥር የለውም፡፡

7- ተውሒድን ከጉድለት ለመጠበቅ ሲባል ከቀብር ላይ ማነጽ፣ ቁባዎችንና መስጊዶችን ከነርሱ ላይ መገንባትና መለስን ተከልክሏል፡፡

8- ድግምት፣ ደጋሚዎችን፣ ጠንቋዮችንና ኮከብ ቆጣሪዎችን መጎብኘትና መሰል ተግባራትም ተውሒድን ይቃረናሉ፡፡ ደጋሚ ሁሉ ካፊር በመሆኑ ወደርሱ መሄድ አይፈቀድም፡፡ እነርሱን አንዳች ጉዳይ መጠየቅና ቃላቸውን አምኖ መቀበልም ክልክል ነው፡፡ ለደጋሚዎች ወልዮች፣ መሻኢኾች የሚሉና መሰል ስያሜዎችን መስጠት ይህን ብይን አይለውጠውም፡፡

9-በገድ ማመን ተውሒድን ይቃረናል፡፡ ይኸውም በአእዋፍት፣ በቀናት፣ በግለሰቦች ወይም በሌሎች ነገሮች መጥፎ ገድነት ማመን ነው፡፡ ይህ ሁሉ አይፈቀድም፡፡

ተውሒድን ከሚቃረኑ ነገሮች መካከል በሐኪም፣ በመድሀኒት፣ በሙያ ወዘተ መተማመን ነው፡፡ በሸሪዓው የተፈቀደው አንዳች ውጤትን ለማግኘት የሚያበቁንን ምክንያቶችና ጥረቶች ሁሉ እያደረግን ውጤቱን በተመለከተ ግን በአላህ እንድንመካ ነው፡፡ ለምሳሌ ሕክምና እንከታተላለን፣ ሲሳይ ፍለጋም እንሮጣለን፣ ይህን ሁሉ ስናደርግ ግን የጥረታችንን ውጤት የሚሰጠን አላህ መሆኑን በማመን መሆን አለበት፡፡ በኮከብ ማመንና ከዋክብትን ከተፈጠሩለት ዓላማ ውጭ ለጥንቆላ ተግባር መጠቀም ተውሒድን ይቃረናል፡፡ዝናብን ከከዋክብትና ከጊዜያት ጋር ማያያዝ፣ ማለትም ዝናቡን የሚያወርደው ወይም የሚያስቀረው ኮከቡ እንደሆነ ማመን የዚሁ አካል ነው፡፡

10-ከቀልብ ኢባዳዎች መካከል አንዱንም ከአላህ ውጭ ለሌላ አካል ማዋል ተውሒድን ይቃረናል፡፡ ለምሳሌ ፍፁማዊ ፍቅርን ወይም ፍፁማዊ ፍርሃትን ለፍጡራን መስጠት፡፡

11-የአላህን ቅጣት መተማመን ወይም ከእዝነቱ ተስፋ መቁረጥም ተውሒድን ይቃረናል፡፡ ከአላህ ቅጣት አትተማመን፡፡ ከእዝነቱም ተስፋ አትቁረጥ፡፡ ምንጊዜም በፍርሃትና በተስፋ መካከል ሁን፡፡

12-የአላህን ውሳኔዎች በፀጋ አለመቀበልናትዕግስትማጣት፣ ውሳኔዎቹን የሚቃረን ቃል መናገርም ተውሒድን ይቃረናል፡፡ ለምሳሌ፡- "አላህ ሆይ፣ ለምን በኔ ወይም በእገሌ ላይ ይህን አደረግክ ? ይህ ሁሉ መከራ ለምን?" የሚሉና መሰል ማማረሮች፣ ሙሾ ማውረድ፣ ልብስን መቅደድ፣ ፀጉርን መንጨት ተውሒድን የሚያጎድፉ ድርጊቶች ናቸው፡፡

13-ለይዩልኝ ወይም ለይስሙልኝ መስራት፣ በበጎ ሥራ ዓለማዊ ጥቅምን ዋነኛ ዓላማ ማድረግ የሽርክ አካል ነው፡፡

14-አዋቂዎችን፣ ባለሥልጣናትን ወይም ሌሎች ሰዎችንሐላሉንሐራም፣ ወይም ሐራሙን ሐላል ሲያደርጉ አሜን ብሎ መታዘዝም ሲሆን፤

15-በአላህና በእገሌ ፈቃድ ወይም አላህና እገሌ ባይኖሩ ኖሮ ወይም በአላህና በእገሌ ተመካሁ ማለት፤ ተገቢ የሚሆነው ካለፉትና መሰል አባባሎች ላይ "እና" ከሚለው ቃል ይልቅ "ከአላህ በታች" የሚል አገላለጽ መጠቀም ነው፡፡

16- ጊዜን፣ ቀናትንና ወራትን መስደብ፤

17-በዲን፣ በመልዕክተኞች፣ በቁርኣን ወይም በሱና ማፌዝ፣ እንዲሁም ዲን በያዙ ደጋግ ሰዎች እና ዐሊሞች፣ ቁርኣንና ሱናን በመተግበራቸው እና አጥብቀው በመያዛቸው ለምሳሌ ፂማቸውን በማስረዘማቸው፣ መፋቂያ በማዘውተራቸው ወይም ልብሳቸውን እስከ ቁርጭምጭሚት በማ

ሳጠራቸውና በመሰል ተግባራቶቻቸው መሳለቅ፤ ተውሒድን ይቃረናል፡፡

18-“አብዱነቢ” (የነቢዩ ባሪያ)፣“ዓብዱል ካዕባ” (የካእባያ) ወይም “አብዱል ሁሰይን” (የሁሰይን ባሪያ) ተብሎ መሰየምም አይፈቀድም፡፡ የሚፈቀደው ለአላህ ተገዠዥነትንና ባሪያነትን የሚያመለክት ስያሜ ብቻ ነው፡፡ ለምሳሌ አብዱላህ እና አብዱረህማን፡፡

19-ነፍስ ያላቸውን ነገሮች መሳልና ማላቅ፣ ከግድግዳ ላይና መሰል ቦታዎች በክብር ማንጠልጠልምተውሒድንያጎድፋል፡፡

20-መስቀልን ማኖር፣ መሳል ወይም ከልብስ ላይ ወዶና ፈቅዶ መተው ተውሒድን ይቃረናል፡፡ ግዴታ የሚሆነው መስበርና መደምሰስ ነው፡፡

21-ሙናፊቆችንና ካፊሮችን መውዳጀት፣ ማላቅና “ሰይድ” (አለቃ) በሚል የክብር ስም መጥራት፣ ለነርሱ ሸብ ረብ ማለት ፤

22- አላህ ባላወረደው ሕግና ሥርዓት መፍረድና መምራት፣ ሰው ሰራሽ ሕግጋትን ከሸሪዓው ድንጋጌዎች ጋር እኩል መፍረድ ይቻላል የሚል እምነት ይዞ ይህን መፈፀም ወይም ደግሞ ሰው ሰራሽ ስርዓቶችና ሕግጋት የሸሪዓውን ያህል ወይም ከሱ የበለጠ ደረጃ ያላቸው፣ ከሸሪዓው ይልቅ ለዚህ ዘመን ተስማሚ ናቸው ብሎ ማመን ተውሒድን ይቃረናል፡፡ ይንዳል፡፡ ሰዎች ይህንን እምነትና አስተሳሰብ ወደውና ፈቅደው በሰው ሰራሽ ሕግ መተዳደራቸው፤

23- ከአላህ ውጭ በሌላ አካል መማል ነው፡፡ ለምሳሌ በነብዩ (ﷺ)ወይም በአማና ወይም በሌላ ነገር መማል ነው፡፡ ነብዩ ሙሐመድ(ﷺ) ይህን በማስመልከት ሲናገሩ እንዲህ ብለዋል፡-“ከአላህ ውጭ በሌላ አካል የማለ ከፈረ ወይም አሻረከ” (ቲርሚዝይ)፤

24-በነብያትና በደጎ ሰዎች መወሰል በዚህ ዘመን ብዙ ሙስሊሞች ከአምላካቸው በመውጣታቸው እና ዲናቸውን ባለ ማወቃቸው በርካታ የሽርክ፣ የቢድዓና የመሐይምነት ተግባራትን ሲፈጽሙ ይስተዋላሉ፡፡ በሰፋት ከተሰራጩት ከነዚህ ሽርክያት መካከል እንዳንድ ሙስሊሞች ወልይና ደጋግ ሰዎች ለሚሏቸው ግለሰቦች በሚያሳዩት ከወሰን ያለፈ ክብርና እነርሱን ከአላህ ውጭ መማፀናቸው፣ ይጠቅ ማሉ ወይም ይጎዳሉ ብለው ማሰባቸው ይገኝበታል ከልክ በላይ አላቋቸው፡፡ ቀብሮቻቸውን ጎበኙ፡፡ ይህን የሚያደር ጉት አላህ ጉዳዩቻቸውን ይፈጽምላቸው፣ ችግሮቻቸውን ያሰወግድላቸው ዘንድ እነርሱን እንደ አማካይ ለመያዝ በማሰብ ነው፡፡

25-የሸዕባንን አጋማሽ ሌሊት በዒባዳ እንኳን ቢሆን ለይቶ ማክበር፤

26-የኢስራእ እና የሚእራጅ ሌሊትን በዒባዳም እንኳን በተለየ መልክ ማክበር፤

27-አስራ አምስተኛ- የነቢዩ ሙሐመድ መውሊድን ማክበር፤

28-የእምነት ነክ ትምህረቶችን ችላ ማለት ማናናቅ፤

29-ላኢላህ ኢለሏህ ማለት ብቻ በቂ ነው ብሎ መሳነፍ፤

30-ዒባዳን በሶላት በዘካ ... በመወሰን የዒባዳን መልዕክት ማጥበብ፤

31-በሁሉ ነገር ከካፊሮች ጋር መመሳሰል፤

32-ነቢዩን ኑር ናቸው ብሎ ማመን፤

33-ኢማን፤ ሙህሲንህ፤ ኩብራ፤ ሳዲቅ፤ መህሙድ፤ ራማ፤ ላራ፤ ሪና፤ ሪማስ፤ ሊማር፤ መይ፤ ሚላክ፤ አብራር፤ በረህ፤ ጌታ፤...ብሎ መሰየም እና መሰሎችን ተግባራት መፈፀም ነው፡፡ ሰለፎች ድንገተኛ የእምነት ስህተቶች ዉስጥ የወደቀን ተከታትሎ ማስተማርና እንዳይደግመው ከመምከር አልፈው ሆን ብሎ ለሚፈፅም ደግሞ እንደ ሁኔታው ቅጣት ይበይኑበት ነበር፡፡ ለምሳሌ ዑመር ኢብኑል ኸጣብ ሰቢግ ብን ዐሰል የተባለን ሰው ሆን ብሎ ተመሳሳይነት አላቸው ብሎ ያሰባቸዉን የቁርኣን አናቅፅ ወደ መዲና በመምጣት ማደናገር ሲጀምር አስጠርተው ሲመጣ ማንህ አሉት እኔ ዐብዱላህ ሶቢግ ነኝ ሲላቸው፡፡ እኔም ዐብዱላህ ዑመር ነኝ ብለው እስኪደማ ድረስ ደበድበው በቃኝ በዉስጤ የነበረው ችግር ለቆኛል እሰኪላቸው ድረስ እንደመቱት ይነገራል፡፡ ዳሪሚ.የቢድዓ ሰዎችንም እንዲሁ ከማስጠንቀቃቸው አልፈው ያገሏቸው ነበር፡፡



# ሱሃቦች የሰማይ ከዋክብት

ማንኛውም ሙስሊም የታላቁ ነብይ ሙሐመድ በባልደረቦች ከነብያት ቀጥለው ምርጦች ናቸው ብሎ ሊያምን ይገባዋል፡፡ የሱና እና የህብረት ባለቤቶች ካስቀመጧቸው መሰረታዊ የምነት መርሆዎች መካከል የነቢዩ ሶሃባዎችን መውደድ አንዱ ነው፡፡ ይህን መሰረታዊ ጉዳይ ካስገነዘቡ ታላላቅ ዐሊሞች መካከል ኢማሙ አጡሃዊ ይገኛሉ፡፡ አላህ በቁርኣን የእነርሱ ትልቅነት ብዙ ቦታዎች ላይ ዘግቦታል፡፡ ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ በታች ባሉት ዋናዋና ረዕሶች ስር እንመልከታቸው፡፡

ሀ-የነቢዩ ባልደረቦች ለዲናቸው ሲሉ የከፈሏቸዉን ወደር የለሽ ምስወአት በተመለከተም ከዚህ በታች ባሉት ነጥቦች አብረን እንመልከት፡፡

1-ቀደም ሲል የነበሩበትን እምነት መተዋቸውና የኢስላምን ጥሪ ተቀብለው፤ ትክክለኛ አማኞች ማለት እነሱ እንደነበሩ እስከሚመሰከርላቸው ድረስ መድ2ረሳቸው፤ ይህን አስመልክቶ ቁርኣን እንዲህ አለ፡-(ከአላህ ሌላ ከሰማያትና ከምድር ምንንም ሲሳይ የማይሰጧቸውንናምንንምየማይችሉትንያመልካሉን፡፡ መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! ለአላህ አምሳያዎችን አታድርጉ፡፡ አላህ መሳይ እንደሌለው ያውቃል፡፡ እናንተ ግን አታውቁም።) አን-ፋል 73-74.

2-አላህ ተግባራቸውን የተቀበላቸው ለመሆናቸው፡-(ከስደተኞቹም ሆነ ከረዳቶቹ የመጀመሪያዎቹ ቀዳሚዎችና እነዚያም በበጎ ሥራ የተከተሏቸው ሰዎች አላህ የእነሱን ተግባር ወዶላቸዋል፡፡ እና እነርሱም ወደውለታል፡፡ በሥሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸውን ገነቶች በውስጣቸውም ዘለዓለም ነዋሪዎች ሲሆኑ አዘጋጅቶላቸዋል፡፡ ይህ ታላቅ እድለኛነት ነው) አት-ተውበህ 100.

3-ዘመዶቻቸዉን፤ ሀገራቸዉንና ንብረታቸዉን ለዲን ሲሉ እርግፍ አድርገው መተዋቸዉን አስመልክቶም አላህ እንዲህ ይላል፡፡

4-መተዛዘናቸዉን በተመለከተ ቁርኣን እንዲህ አለ፡-(የአላህ መልዕክተኛ ነብዩ ሙሐመድ እና እነዚያ የእርሱ ጓደኞች በከሐዲያን ላይ ብርቱዎች፤ በመካከላቸው ተዛዛኞች ናቸው፡፡ አጎንባሾች፤ ሰጋጆች፤ ሆነው ታያቸዋለህ፡፡ ሁልጊዜም ከአላህ ችሮታንና ውዴታን ይፈልጋሉ፡፡ ምልክ

ታቸው ከስግደታቸው ፈለግ ስትሆን በፊታቸው ላይ ናት፡ ፡ ይህ በተውራት የተነገረላቸው ፀባያቸው ነው፡፡ በኢን ጅል ውስጥ የተጠቀሰው ምሳሌያቸው ደግሞ ቀንዘሉን እንደ አወጣ አዝመራና (ቀንዘሉን) እንዳበረታታው እንደ ወፍራምና ገበሬዎቹን የሚያስደነቅ ሆኖ አገዳዎቹ ላይ ተስ ተካሎ እንደቆመ አዝመራ ነው፡፡ ያበረታታቸውና ከሐዲ ያን በእርሱ ሊያሰቆጭ ነው፡፡ አላህ እነዚያን በእሱ ያመኑ ትን ና ከእነርሱ በጎዎችን ተግባራት የሰሩትን ሁሉ ምህረት ንና ታላቅ ምንዳን ቃል ገበቶላቸዋል። አል-ፈትህ 29.

5-እስቲ ቁርአንን ከነቢዩ ጋር እንዴት አብሮ እንደመደባ ቸው አብረን እንመልከት (ግን መልዕክተኛውና ከእርሱ ጋር ያመኑት ሰዎች በገንዘቦቻቸውም በነፍሶቻቸውም ታገሉ፡፡ እነዚያም መልካሞች ሁሉ ለእነሱ ብቻ የተዘጋጁ ናቸው፡፡ እነዚያም እነሱምኞታቸውን ያገኙናቸው፡፡ .አት ተውበህ 88

6- የዚች ዐለምን ፈተናዎችን የኑሮ ዉጣ ዉረድን ሳይበ ገሩ ማለፋቸው፤ ኢስላምንና ሙስሊሞችን ከምድረገፅ ለማ ጥፋት የተነሳዉን ሃይል ለመቋቋም የከፈሉት ሁለንተናዊ ምስወዐትነት፤ ኢስላምን ለማስፋፋት፤ ሙስሊሞችን ለመ ደገፍ የከፈሉት ሀብትና ዉድ ሕይወት እና ሌሎችንም በተ መለከተ በቁርአን እንዲህ ይላል፡፡ (እነዚያ በአላህ ያመኑት ከየአገሮቻቸውም የተሰደዱት በገንዘቦቻቸውና በነፍሶቻቸ ውም በአላህ መንገድ ላይ የታገሉት አላህ ዘንድ በደረጃ በጣም የላቁ ናቸው፡፡ ፍላጎታቸውን ያገኙ ማለትም እነሱ ብቻ ናቸው፡፡) አትተውበህ 20. እንኳንስ ተዋግተው ከጂሃድ ቀርተውም እንዲህ ተብለዋል፡፡ (እነዚያ በአላህ ያመኑና ለእሱ ሲሉ የተሰደዱ በአላህ መንገድ ላይ የታገሉ እነዚያም ያስጠጉና የረዱ እውነተኛ አማኞች እነሱ ናቸው፡ ፡ ለእነሱም ምሕረትና የከበረ ሲሳይ አለላቸው፡፡ እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ ፣እነዚያ በኋላ ያመኑና ከሀ ገራቸው የተሰደዱ ከእናንተም ጋር ሆነው የታገሉ ከእናን ተው ናቸው፡፡ የዝምድናዎች ባለቤቶች በአላህ መጽሐፍ ከፊሎቻቸው ከከፊሉ ለመውረስ የተገቡ ናቸው፡፡"አላህ ሁሉን ነገር ዐዋቂ ነው፡፡) አን-ፋል 75.

7-ከነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ጓዶች መካከል አንደኛ ደረጃ የሚሰጣቸው እኒያ በአላህ አምነው ለኢስላም ሲሉ ከመካ ወደ መዲና ተሰደው የነበሩና በጂሃድ ተሳታፊ የነበሩ ሙሃ ጂሮችና እነዚህን ስደተኞች የተቀበሉና በጂሃድም የተሳተፉ አንሷሮች ናቸው፡፡


8- በመቀጠልም ከሁደይቢያው ስምምነት በኋላ እምነትን ተቀብለው የተሰደዱና የተዋጉ ሶሃባዎች ናቸው፡፡

9- ከዚያሞ እምነትን የተቀበሉ ሆኖም ስደት ያልወጡ ሶሃ ባዎች ናቸው፡፡

ሶሃቦች በደረጃ ቢበላለጡም ባጠቃላይ የአላህ ቀን አገ ልጋይ ባሪያዎች እንደነበሩ አያሌ ምስክሮችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ አላህ እንዲህ አለ (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ ! እነዚያ በኋላ ያመኑና ከሀገራቸው የተሰደዱ ከእናንተም ጋር ሆነው የታገሉ ከእናንተው ናቸው) አን-ፋል75. አላህ እነሱን አንድ በማድረግ ከፍተኛ ዉለታ ዋለ ላቸው፡፡ ቁርአን እንዲህ አለ፡-(መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! በምድር ያለውን ሁሉ ሀብት በትለገሰ ኖሮ እንኳን በልቦቻቸው መካከል ባላስማማህ ነበር፡፡ ግን አላህ በመ ካከላቸው አስማማ፡፡ እርሱ አሸናፊና ጥበበኛ ነውና፡፡ ከጠላቶቻቸው የጠበቃቸው መሆኑን፤ አንተ ነብይ ሆይ ! ለሁሉ ነገር በቂህ አላህ ነው፡፡ ለተከተሉህም ምዕምናን በቂያቸው አላህ ነው፡፡ (አን-ፋል64.) ለነቢዩ ልዩ ድጋፎ ችና ምርጥ ሥጦታዎች መሆነቸውን መግከፁ፤ የቱን ያክል ምረኛ እንደነበሩ ይፋ አዋጅ ነው፡፡ አላህ እንዲህ አለ(ከ አማኞች መካከል በእርሱ ላይ ለአላህ ቃልኪዳን የገቡበ ትን በእውነት የፈጸሙ ወንዶች አሉ) አህ-ዛብ.23. የነቢ ሱሃቦች ማለት አላህ ተግባራቸዉን እንደተቀበላቸው በቁ ርአን ያወጀላቸው መሆኑን እንመልከት፡፡(መልዕክተኛ ችን ሙሐመድ ሆይ! አላህያችን ከዚህበፊትበእርግጥያለ ፈችውንልምድደነገገ፡፡ ለአላህ ልምድላይመቸምለውጥንአ ታገኝም፡፡)አል- ፈትህ-23.ቁርአን የሙሃጂርንንና የአንሷ ርን ቡድን እንዲህ ይላቸዋል፡፡ (መልዕክተኛው በእነዚህም በችግሩ ጊዜ (በተቡክ ዘመቻ) ከእነሱ የከፊሎቹ ልቦች ለመ

ቅረት ሊዘነበሉ ከተቃረቡ በኋላ በተከተሉት ስደተኞችና ረዳቶች ላይ አላህ በእርግጥ ፀፀታቸውን ተቀበለ፡፡ ከዚያም ከእነሱ ንሰሃ መግባታቸውን ተቀበለ፡፡ አላህ ለእነሱ ሩህ ሩህና አዛኝ ነውና ) አት-ተውበህ 117.

እንዲህም ይላቸዋል፡፡(ሰዎች ሆይ ! በአይነስውር ላይ ከዘመቻ በመቅረቱ ኃጢአት የለበትም፡፡ በበሽተኛው ላይ ኃጢአት የለበትም፡፡ አላህንና መልዕክተኛውን የሚታዘዝ ሰው ሁሉ ከስሮቻቸው ወንዞች የሚፈሱባቸው ገነቶች ያስ ገባዋል፡፡ የሚፈልገውንም ሰው አሳማሚ ቅጣት ይቀጣ ዋል፡፡) 48:17.



እንዲህ ብሉዋል፤- (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! ከም ዕመናኖቹ በዛፊቱ ስር ቃል ኪዳን በሚጋቡህ ጊዜ አላህ በእ ርግጥ ስራቸዉን ወደደላቸው፡፡ በልቦቻቸውም ውስጥ ያለውን ዐወቀ፡፡ በነሱም ላይ እርጋታን አወረደ፡፡ ቅርብ የሆነንም መክፈት መነዳው፡፡ ብዙዎች ዘረፋዎችንም የሚ ወስዷቸው የሆኑን መነዳቸው፡፡ አላህም አሸናፊ፤ ጥበበኛ ነው) 48:18-19.

ሙሃጂሮችን በተለይ በተመለከተ ቁርአን እንዲህ ይላል፡፡ እናም ጌታቸው እኔ ከእናንተ ውስጥ የወንድም ሆነ የሴትን መልካም ስራ ወሮታ አላጠፋም፡፡ ከፊላችሁ የከፊሉ አካል ነው በማለት ልመናቸውን ተቀበላቸው፡፡ እዚያ ለዲን ሲሉ የተሰደዱ ከአገሮቻቸውም በግፍ የተባረሩ በመንገ ድም (ሁከት የደረሰባቸው) የተጠቁ፤የተጋደሉ እና የተገደ ሉም ከፉ ስራዎቻቸውን አብስላቸዋለሁ፡፡ በስሮቻቸውም ወንዞች የሚፈስባቸውን ገነቶች አስገባቸዋለሁ ፡፡ እነሱም ከአላህ ዘንድ የሆነን ከፍተኛ ምንዳ ይመነዳሉ፡፡ አላህ እርሱ ዘንድ መልካም (ጀነት) ምንዳ አለና፡፡3፡ 195.

እንዲህ ብሉዋል፤- (ኢብራሂም አይሁድም ሆነ ክርስቲ ያን አልነበረም፡፡ ግን ወደ ቀጥተኛው ሃይማኖት የተዘነ በለ ቀጥ ያለ ሙስሊም ነበር፡፡ ከአጋሪዎችም አልነበረም፡ ፡ ከሰው ሁሉ ኢብራሂምን በመከተል ተገቢዎች እነዚያ በዘመኑ የተከተሉት ሰዎች ፤ ይህ ነብይ ነብዩ ሙሐመድ እና እነዚያ በሙሐመድ ያመኑት ሰዎች ብቻ ናቸው፡ ፡ አላህ የትክክለኛ አማኞች ሁሉ ወዳጅ ነው) 3፡ 67-68. እንዲህ ብሉዋል፤- (የሰማያትና የምድር ውርስ ለአላህ ብቻ ሲሆን በአላህ መንገድ የማትለግሱበት ምን ምክን ያት አላችሁ ? ከእናንተ መካከል ከመካ መከፈት በፊት የለገሰና የተጋደለ ሰው ከተከፈተ በኋላ ከለገሰና ከተጋደለ ጋር አይስተከከልም፡፡ ከእነዚያ በኋላ ከለገሱትና ከተጋደ ሉት እነዚህ በደረጃ በጣም የላቁ ናቸውና፡፡ ሁሉንም አላህ መልካሚቱን ተስፋ ቃል ገብቶላቸዋል፡፡ አላህ በምትሰሩት ሁሉ ውስጠ አዋቂ ነው) 57:10.

ሀገራቸዉን ለምንእንደተዉት(ለእነዚያ የአላህን ችሮታና ውዴታውን የሚፈልጉና አላህንና መልዕክተኛውን የሚረዱ ሆነው ከአገሮቻቸውና ከገንዘቦቻቸው ለተወጡ /ለተባረሩ/ስደተኞችድሆችይሰጣል፡፡ እነዚያ እነርሱ እው ነተኞችናቸው፡፡ አል ሐሽር-8

አንሷሮችን ብቻ በሚመለከተ(እነዚያ ከበፊታቸው ሀገሪ ቱን መዲና መኖሪያ ያደረጓትና እምነት በልባቸው የሰረ ፀባቸው ወደ እነርሱ የተሰደዱትን ሰዎች ይወዳሉ፡፡ ስደ ተኞችም ከተሰጡት ነገር ላይ በልቦቻቸው ውስጥ እንኳን ምንምቅሬታን አያሳድሩም፡፡ በእነሱ ላይ ችግር ቢኖርባ ቸቸውም እንኳ በነፍሶቻቸው ላይ ሌላውን ያስቀድማሉ፡ ፡ ከነፍሶቻቸው ንፍገት (ንፉግነት) የሚጠብቁ ሰዎች ሁሉ እነዚያ የተሳካለቸውና ምኞታቸውን አግኚዎች ማለት እነሱ ብቻ ናቸው፡፡ አል ሐሽር-9›

አላህ በእሱ የነቢዩ ሱሓባዎች ከነብያቸው ጋር ምንም

እፍረት የሌለባቸዉን መሆኑን ሲየወሳልን እንዲህ አለ፡፡ (አላህ ነብዩን እነዚያንም ከእርሱ ጋር ያመኑትን በማያሳፍር በትቀን ብርሃናቸው በፊቶቻቸውና በቀኞቻቸው የሚሮጥ ሲሆን ፡- ጌታችንሆይ ! ብርሃናችንን ሙላልን፤ ለእኛ ምህረ ትንም አድርግልን፤ አንተበነገሩ ሁሉ ላይ ቻይነህና ይላሉ፡ ፡) አተ-ተህሪም -8›

የነሱን ትልቅነት የሚያወሱ የነቢዩ ሃዲሶችም እንዲሁ ብዙ ናቸው፡፡ ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ በታች የሚከተሉት ናቸው፤ (ሶሃቦችን አትስደቡ፡፡ ህይወቴ በእጁ በሆነው በአላህ ይሁ ንብኝ ከመሀላችሁ አንዱ የኡሁድን ጋራ የሚሃል ወርቅ ቢሠጥ የእነሱን የአንድ እፍኝ አያሃልም፡፡ እረ ግማሹ ንም፡፡»



ሁለት አቡ ቡርደህ (መግሪብን ሰግደን ዒሻን ለመስገድ እየተጠባበቅን ሳለን ነቢዩ መጡና እስካሁን እዚህ ናችሁ አሉን አዎ ዒሻን ከእርሰዎ ጋር እንስገድ ብለን እየጠበቅነ ነው አልናቸው፡፡ ጥሩ አደረጋችሁ አሉና ራሰቸዉን ወደ ሰማይ በማቃናት ከዋክብት የሰማይ ሰለሞች ናቸው፡፡ ከዋ ክበት ከጠፉ የአላህ ቃል ይፈፀማል፡፡ እኔም የሱኃቦቼ ሰላም ነኝ እኔ ከሄድኩ በሱኃባዎቼ ላይ የአላህ ቃል ይፈፀ ማል፡፡ ሱኃቦቼም ለኡመቴ ሰላም ናቸው እነሱ ሲሄዱ በህ ዝቦቼ ላይ የአላህ ቃል ይፈፀማል) ሙስሊም.

(ሱሃቦቼን አትስደቡ፡፡ ነፍሴ በእጁ በሆነችው ጌታ ይሁንብኝ ከናንተ አነዳችሁ የኡሁድን ጋራ የሚያ ክል ገንዘብ ምጽዋት ቢሰጥ እንኳ እነርሱ የመጸወቱትን እፍኝ ወይም ግማሽ አያሃልም፡፡) ቡኻሪና ሙስሊም. ከተከታዩቹ ሁሉ ምርጡ ትውልድ እኔ ያለሁበት ነው፡ ፡ ከዚያም ቀጥሎ የሚመጣው ትውልድ ነው፡፡ ከዚያም ቀጥሎ የሚመጣው ትውልድ ነው፡፡ ዒምራን ይህን አባባል አንድ ጊዜ ይበሉ ወይም ሁለት በደንብ አላስታዉስም) ብሏል፡፡

....ጋር ቃል የተጋባ ሁሉ እሳት አይገባም፡፡ (ከዛፏ ስር ከኔ በአጠቃላይ የነቢ ሱሓቦች የኡመቱ ሳማይ ዉበት ከዋከ ብት ናቸው፡፡ እናም የእና ክብር እኑሱነን በመከተል ነው፡ ፡ እኛ ሙስሊሞች ለረሱል ሰሓቦች ሊኖረን የሚገባው ክብር ቁርኣንና ሐዲስ የቸራቸዉን ያክል መሆን አለበት፡ ፡ በነሱ ላይ የሚወሩትን የሐሰት ወሪዎች በመከላከል ክብ ራቸዉን ማስጠበቅ ግዴታችን ነው፡፡ ከአላህ ምስክርነትና ከነቢዩ ምስክርነት በኋላ ማንም እነሱን ሊተች አይችልም፡ ፡ በመሀከላቸው ተከስቶ በነበረው ጉዳይም ላይ የማንነንመ ዳኝነት አያስፈልግም፡፡

ቁርኣን ሶሃቦችን በጅምላ ብቻ ሳይሆን በተናጠልም እንዲህ በማለት ያሞካሻቸው አሉ፡፡

1-አቡ በክር ሲዲቅን በተመለከተ፡

አቡ በክር ሲዲቅ፡-የመጀመሪያው ሙስሊምና የመጀመ ሪያው ኸሊፋ፡፡ ከነቢያት ቀጥሎ በመሬት ላይ ከተጓዙ ሁሉ በላጭ ታላቅ ሰው፡፡ የስደት ባል ደረባ እንደነበሩ ሲገልፅ እንዲህ ብሏል፡- ሙስሊሞች ሆይ ! ነብዩ ሙሐ መድን ባትረዱት እነዚያ በአላህ የካዱት ህዝቦች የሁለት ሰዎች ሁለተኛ ሆኖ ከመካ ባስወጡት ጊዜ አላህ ረድቶ ታል፡፡ ሁለቱም በዋሻው ሳሉ ለጓደኛው አትዘን አላህ ከእኛ ጋር ነውና ባለ ጊዜ አላህ እርካታውን በእርሱ ላይ አወረደ፡፡ ባላያችኋቸውም ሰራዊት አበረታው፡፡ የእነዚያን በአላህ የካዱትን ሰዎች ቃል የበታች አደረገ፡፡ የአላህ ቃል ግን የበላይ ነው፡፡ አላህ ሁሉን አሸናፊና ጥበበኛ ነውና)

አት-ተውበህ 40. በመካ ዉስጥ የነበሩ ሙስሊም ድሃዎችን በመርዳት ፤ ባሮችን ነፃ በማውጣት ከፍተኛ ተጋድሎ አድ ርገዋል፡፡ ያ ! ገንዘቡን የሰጠ ሰው ጌታውን የፈራና፤ በመ ልካሚቱ እምነት ያረጋገጠ ሰው ለመልካም ነገር ሁሉ እና ዘጋጀዋለን፡፡ ያ የሚጥራራ ሆኖ ገንዘቡን ለሰዎች የሚሰጥና ፤ አላህን በጣም ፈሪ የሆነ በእርግጥ ይርቃታል፡፡ ለአንድ ሰው በእርሱ ዘንድ የሚመለስ ውለታ ሳይኖር፡፡ የታላቁን ጌታውን የአላህን ውዴታ ለመፈለግ ይህንን የሰራ ሲቀር፡፡ እርሱማ ወደ ፊት የፈለገው ተስጥቶት በእርግጥ ይደሰታል፡ ፡ (አል-ለይል) 5-6.

ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዐሊይ ኢብኑ አቡጣሊብ ከአላህ መልዕክተኛ (r) ጋር አንድ ቀን ቁጭ ብለን ሳለን እንዲህ አሉ፡- «ከመካከላችሁ ውስጥ አንዱ መቀመጫው ከጀነት ይሁን ወይም ከእሳት ሳይፃፍለት የቀረ የለም » አሉ እኛም «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ! ታዲያ ስራዎቻችንን አቁመን በዚሁ እንመካ እንዴ ? » አልናቸው ፡፡ እሳቸው «በፍፁም ስራችሁንማ ተግታችሁ ስሩ ሁሉም ሰው ለሚሰሪው ቀላል ነው» ካሉን በኋላ «የሰጠ ሰውማ ጌታውን የፈራም ፤ በመ ልካሚቱም እምነት ያረጋገጠ፤ ለገሪቱም ስራ እናሽጋግረዋ ለን፡፡ የሰሰተ ሰውማ የተብቃቃም በራሱ የተመካ በመ ልካሚቱ እምነት ያስተባበለም፤ለከፋይቱ ስራ እናዘጋጀዋ ለን» (አል-ለይል 5-10) የሚለውን የቁርአን አንቀፅ አነበቡ፡ ፡ (አል-ለይል)17-21.



ከብረት ምዕራፍ 10ኛው አንቀፅ የወረደበት ምክንያት ንም ስንመለከት አቡበክርን አላህ በግል ስማቸዉን ጠርቶ ሰላምታ መላኩን እንመለከታለን፡፡

ነብዩ ሙሐመድ (r) አቡበክር አጠገባቸው በነበሩበት ወቅት መላዕኩ ጅብሪል መጥቶ አቡበክር ለምንድ ነው በደረቱ ላይ የተንጠለጠለች ኮት የለበሰው ሲላቸው ከፊት ለፊትህ ካፖርቱን ለእኔ ሲል አውጥቶ ስለነበረ ነው አሉት፡ ፡ ጅብሪልም መለስ አድርጎ በአላህ ሰላምታም አድርሰውና ጌታህ ይህን ድህነት ተቀበለህዋል ወይንስ ጠልተኸዋል በማለት ጠይቀው ነብዩ ሙሐመድ (r) ወደ አቡበክር ዞር ብለው ጅብሪል የአላህን ሰላም አድርሰህ ጌታህን እንዲህ ብሎሀል ሲሏቸው አቡበክር አልቅሰው በጌታዬ ላይ እቆ ጣለሁኝ? እኔ ከጌታዬ ጋር ተስማቻለሁ በማለታቸው ይህ አንቀፅ የወረደው፡፡ (ዋሂዲ እና ሱዩጢ)

2-እንደዚሁም ዑመርን በተመለከተ

1-ነቢዩ ሙሐመድ (ከኔ በኋላ የሚመጡትን በአቡበክርንና ዑመርን ተከተሉ)ብለዋል፡፡ ቲርሚዚ.በማለታቸው፤

2-ከተበሰሩት አንዱ በመሆናቸው፤

3-ሁለተኛ ኸሊፋ በመሆናቸው፤

4-በብዙ ቦታዎች ላይ ሐሳባቸዉን በመደገፍ ቁርአን የወረ ደላቸው ናቸው፤

5-በኡሁድ ጋራ ላየ ሁነው በተነገረው ተዐምራዊ ሐዲስ ሁለት ሸሂድ ከተባሉት አንዱ በመሆናቸው፤

ሐ-እንደዚሁም ዑስማንን በተመለከተ

1-ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ)ስለ እሳቸው ብዙ የሙገሳ ቃላቶ ችን በማለታቸው፤

2-በምድር እያሉ በጀነት ከተበሰሩት አንዱ በመሆናቸው፤
3-ሶስተኛው ኸሊፋ በመሆን ከነቢዩ ሶስተኛ ሰው በመሆ ናቸው፤

4-በብዙ ቦታዎች ላይ ሐሳባቸዉን በመደገፍ ቁርኣን የወረ ደላቸው ናቸው፤

5-በኡሁድ ጋራ ላየ ሁነው በተነገረው ተዐምራዊ ሐዲስ ሁለት ሸሂድ ከተባሉት አንዱ በመሆናቸው፤

መ -እንደዚሁም ዐሊይን በተመለከተ

1-ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ) ስለ እሳቸው ብዙ የሙገሳ ቃላቶ ችን በማለታቸው፤

2-በምድር እያሉ በጀነት ከተበሰሩት አንዱ በመሆናቸው፤

3-አራተኛው ኸሊፋ በመሆን ከነቢዩ አምስተኛ ሰው በመ ሆናቸው፤ 4-መሰሎችን መመልከት የሶሃቦችን ትልቅነት በቂ ማስረጃ ነው፡፡

ሺዓና ሶሃቦች

1-ከሶስቱ ሰዎች በስተቀር ማለትም ከአቡ ዘር፤ ሚቅዳድ፤ ሰልማን አልፋሪሲ በስተቀር ሁሉንም ሱሓቦች ማከፈር፤

2-በተለይ ሶስቱን ኸሊፋዎች ማለትም አቡ በክርን፤ ዑመርን፤ ዑስማንን ከማከፈር አልፈው ጧት ማታ መራ ጋማቸው፤

3-ዑመር የተገደሉበትን ቀን ማክበር፤

4-ለዑመር ኢብኑ ልኸጣብ ገዳይ ለ አቡ ሉእሉአተ አል መጁሲ ልዩ ዶሪህ መገንባትና ማክበር፤

5-የነቢዩን ቤተሰቦች በተለይ ዓኢሻንና ሐፍሷን ነጥሎ ስማ ቸዉን ማጉደፍ፤ ታሪካቸዉን ማንቋሸሽ፤

6-ቁርኣንን ተቀንሷል፤ ተበርዟል፤ ፍቹን የሚያውቁት ኢማ ሞቻችን ብቻ ናቸው፤ በማለት የህዝበ ሙስሊሙን እምነት መሸረሸር፤

7-የነቢዩን (ﷺ) ሐዲስ በጠቅላለወ ማውገዝ፤

8-ኢማሞቻቸው ወህይ ይወረድላቸዋል ብሎ ማሰብ፤

9-እንኳንስ የአምልኮ አንድነት ይቅርና በሩቡቢያው ላይ በደንብ አለማመናቸው፤

10- ዐሊን እንደ አማላክ አድርገው መመለከታቸው፤

11-ጊዚያዊ ጋብቻን መፍቀዳቸው፤

12-አያሌ የሐሰት ሐዲሶችን መቅጠፍና ማስፋፋትንና መሰ ሎችን በመፈላሰፍ ኡማዉን ከሱሃባዎች ገለግ ለማስወ ጣት የማያደርጉት ሙከራ የለም፡፡ ኢብኑ ዐባስ (አላህ ለነቢዩ ምርጥ ሶሃቦችን መረጠላቸው..) በለዋል፡፡ ኢብኑ ዑምር (የነቢዩን (ﷺ) ሱሃቦች አትስደቡ፡፡ የእነሱ የአንድ ሰዐት ተግባር የእናንተን የእድሜ ልክ ተግባር ይበልጣል፤) ኢማሙ ማሊክ (...በሶሃቦች የሚበሳጭ ሰው ከሃዲ ነው) ብለዋል፡፡ አቡ ዙርዐህ (ከነቢዩ (ﷺ) ሱሓቦች የአንዱን ስም ሲያጎድፍ ካየህ ዚንዲቅ መሆኑን እወቅ፡፡ ..) ብለዋል፡፡

ከላይ እስካሁን ያየናቸው አራቱም ሶሃቦችና ከዋክብቶች አቡበክር አሲዲቅ፣ ዑመር አልፋሩቅ፣ ዑስማን ኢብኑ ዐፋን እና ዐሊይ ኢብኑ አቡ ጣሊብ ናቸው፡፡

4ቱ ኹላፋኡ ራሺዲን በመባል ይታወቃሉ፡፡





# መካ የቅዱሳን ቦታዎች ሁሉ ቅዱስ

አላህ በጥበቡ በህዝቦች፤ በወቅቶችና በቦታዎች መካከል አበላልጧል፡የኢስላም መፍለቂያ ማዕከል የሆነው ታላቁ ቤት ከዕባ አንዱ ነው፡፡ አላህ እንዲህ አለ ‹‹ለሰዎች ማምለኪያ ይሆን ዘንድ መሬት ላይ በመጀመሪያ ጊዜ የተ ሰራው ቤት ብሩክና ለዓለማት ሁሉ መመሪያ ሲሆን ያ በመካህ (በመካ) ያለው ቤት ካዕባ ነው›› 96 ኣሊ ዒምራን. በዚህ አንቀፅ ላይ ብሩክ ያለው እሱኑ ነው፡፡ ለአላህ ምስጋና ይገባዉና ከሙስሊሞች ዉስጥ የዚህን ቤት ክብር የማያ ውቅ አንድም የለም ቢባል ዉሼት አይደለም፡፡

## ከዕባ በምድር ከተሰሩት መስጊዶች ሁሉ የመጀመሪያው መሰጊድ ነው፡፡

ነቢዩ ኢብራሂም ሃጀር የተባሉትን ሚስታቸዉንና ኢስማ ዒል የተባለዉን ልጃቸዉን በዚያ ምንም አዝርእት በሌለ በት ዋሻ አስቀምጠው በሄዱበት እና ወደ እነሱ ሲመላለሱ በነበሩበት ጊዜ፤ በአንደኛው ጉብኝታቸው ለልጃቸው ለኢ ስማዒል ‹‹ልጄ ሆይ ! አላህ በዚህ ቦታ የዒባዳ ቤት እንድ ሰራ አዞኛል እናእርዳኝአሉት›› ከዚያም ኢስማዒል ድንጋይ እያቀበሉ፤ ኢብራሂም ገነቡት፡፡ ግንባታው በሰላም አለቀ፡ ፡በዚህም አይነት የመጀመሪያ ቤት የሆነው አልመስጂዱል ሐራም በአዲስ ተመሰረተ፡፡ይህን እውነታ በተመለከተ አቡ ዘር ከነቢዩ ጋር የሚከተለዉን ያማረ ዉይይት አድርገዋልና በጥሞና እንከታተለው፡፡አቡ ዘር፡-‹‹የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ! በምድር ላይ በመጀመሪያ ጊዜ የተሰራው መስጊድ የትኛው መስጊድ ነው፡፡ ነቢዩ ‹‹የመካው መስጂድ ነው››፡፡ አቡ ዘር ‹ከዚያስ›፡፡ ነቢዩ የአቅሷ መስጂድ ነው፡፡ አቡ ዘር ‹በመሀከ ላቸው ስንት አመት ነበር›› ነቢዩ ‹አርባ አመት፡፡ ከዚያም የትም ቦታ ላይ ሶላት ከደረሰብህ ቦታላይ ስገድ፡፡ ምክኒ ያቱም ቱሩፋት ያለው እዚህ ላይ ብቻ ነዉና ›ብለዋል፡፡ (ቡኻሪ በ 3366 እና ሙስሊምም በ520)

## መካ የሁሉም ነቢያት የሐጅ ቦታ ነው፡፡

ነቢዩ ኢብራሂም ቤቱን ገንብተው በጨረሱበት ወቅት ‹ሰዎች ሆይ ! ኑ ! ይህን ቤት ጎብኙ› የሚል ጥሪ በአላህ ትዛዝ አስተላለፉ፡፡ በዚህ ሰዐትም ብዙ ህዝብ ጥሪዉን ተቀበለ፡ ፡ ከነዚህ መካከል በዋነኝነት የሚጠቀሱት ነቢያት ነበሩ፡፡ እናም፡- 1-ነቢዩ ኢብራሂም ራሳቸው፤ 2-ነቢዩ ኢስማዒል ፤ -፫ነቢዩ ሙሳ፤ 4-ነቢዩ ዩኑስ፤ 5-ነቢዩ ሙሐመድ (ﷺ)

እና ሌሎችም ነቢያት ወደ እዚሁ ቤት በመጓዝ የሐጅ ሥርዓቶችን ፈፅመዋል:: ለዚህም ብዙ የጣሪክ መዛግብት ማገ ላበጥ አየሻም:: ኢብኑ ዐባስ በዘገቡት ሐዲስ ነቢዩ ዋዲል አዝረቅ በተባለ ቦታ ሲያልፉ ከሙስሊሞች ጋር የሚከተለ ውን ዉይይት አደረጉ::

ነቢዩ (ﷺ) «ይህ ወንዝ ምን ይባላል» ሙስሊሞች«ዋዲል አዝረቅ ይባላል:: ነቢዩ «ልክ ሙሳ ከአቀበቱ ወደ አላህ ለበይክ በማለት እያለቀሰ በቁልቁለቱ ሲወርድ የማየው ይመስለኛል » ኢብኑ ዐባስ «ከዚያም ሐርሻ የተባለ ቦታ ደረስን:: ከዚያም» ነቢዩ (ﷺ) «ይህ ቁልቁለት ማን ይባላል» አሉ ሙስሊሞች «ሐርሻ የተባለ ቁልቁለት ነው»:: ነቢዩ «ልክ ዩኑስ ኢብኑ መታን የሱፍ ካቦርት ለብሶ በደለበች ቀይ ግመል ላይ ሁኖ ለበይክ እያለ በቁልቁለቱ ሲወረድ የማየው ይመስለኛል:: ብለዋል:: (ሙስሊም 241.) ወደ ዐለም ፍፃሜ አካባቢ ነቢዩ ዒሳ የሚያደርጉ ትን ሐጅም አቡ ሁረይራ ነቢዩ (ﷺ) «ሕይወቴ በእጁ በሆነው ጌታ በአላህ ይሁንብኝ ኢብኑ መርየም ለሐጅ ወይም ለዑምራ ከፈጅ ረውሐእ ኢህራም ያደርጋል» ብለዋል:: (ሙስሊም 1252.)

በመካ የሚሰገድ አንድ ሶላት ከሌላው በመቶ ሺህ ሶላት የሚቆጠርበት ቦታ ነው::

## በሐረም ዉስጥ ወንጀልን መፈፀም ቀርቶ ማሰብ እንኳን ያስቀጣል::

ነቢዩ (ﷺ) ኢብኑ ዐባስ በዘገቡት ሐዲስ «ከሰዎች ሁሉ በአላህ ዘንደ የተጠሉ ሶስት ሰዎች ናቸው:: በሀረም ዉስጥ ወንወጀልን ያሰበ፤ በኢስላም ዉስት የጃሂሊያን ተግባር የሚመኝ፤ ያለ አግባብ የሰዎችን ደም ለማፍሰስ ግድ ብሎ የሚጠይቅ ነው»ብለዋል::(ቡኻሪ 6882.)

## ሁለቱ ቅዱሳን ከተሞች ከደጃል ወረራ እንኳን የተጠበቁ ;

ነቢዩ (ﷺ) አነስ ብን ማሊክ በዘገቡት ሐዲስ«ከመካና ከመዲና በስተቀር ደጃል የማይወረው ሀገር የለም:: እነሱማ በየኬላዎቻቸው ላይ የመላይካ ዘበኞች አሉ:: ከዚያም መዲና ሶስት ጊዜ ትርገፈገፋለች:: ከዚያም በአላህ ሀይል ከሃዲያንና ምናፍቃን ከመዲና ጥርግ ብለው ይወጣሉ»ብለዋል:: (ቡኻሪና ሙስሊም)

## ሁለቱም ሀገሮች ከደጃል ስለተጠበቁ ብዙ ሰዎች በመኗሪያነት በጣም ይፈልጓቸዋል::

## መካ ሁል ጊዜ የአስተማማኝ ሰላም ሀገር ነው

አል-ሓሪስ ብን ማሊክ በዘገቡት ሐዲስ ነቢዩ «ይህ ሀገር ከዛሬ በኋላ እስከ ዐለም ፍፃሜ ድረስ አይዘመትበትም» ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ ብሏል:: (አህመድናቲርሚዚ)

በመካ መኖር የሚያስገኘው ልዩ ዒባዳ; በመካ የሚኖርም ሆነ ጎብኚዎች ሁሉ ከሌሎች የሚለዩት ቀንም ሆነ ማታ በፈለጉበት ሰዐት ጦዋፍ ማድረግ መቻሉ ነው::

## ለቂብላችን ሊሰጠው የሚገባው ክብር

ነቢዩ (ﷺ) አቡ አዩብ አል አንሷሪ በዘገቡት ሐዲስ «ማንም ሊፀዳዳ ሲፈልግ ቂብላን በመቀመጫው አይቅጣጫት:: ጀርባዉንም እንዳይሰጣት:: ይልቁንም ወደ ምስራቅ ወይም ወደ ምዕራብ ይዞር »ብለዋል:: (ቡኻሪናሙስሊም)

ነቢዩ (ﷺ) ኡሳመት ብን ዘይድ በዘገቡት ሐዲስ «ከነቢዩ ጋር ወደ ከዕባ ገብቸ ነበር እናም እንደገቡተቀመጡ አላህን አመሰገኑ አወደሱት አላህ አክበር ላኢላሃ ኢለሏህ አሉ ከዚያም ወደ ቤቱ ልባቸዉን አስጠግተው እጃቸዉንና ጉንጫቸዉን እሱ ላይ አስቀምጠው አላህ አክበር ላኢላሃ ለሏህ አሉ:: ዱዓም አደረጉ፤ ይህን አይነት ተግባር በአራቱም አቅጣጫ ካደረጉ በኋላ ወጥተው እበሩ ላይ ወደ ቂብላ ዞረው ቆሙና ይህ ነው ቂብላ :: ይህ ነው ቂብላ አሉ:: » ብለዋል:: አህመድ፤ ነሳኢየዘገቡትሲሆንአልባኒት ከክልነውብለዋል::

## በጦዋፍ ዉስጥ መነጋገር

ሙስሊሞች በጦዋፍ ዉስጥ ሊናገሩት የሚገባው ዱዓና ዚክር ነው:: ሻፊዒ «በጦዋፍ ዉስጥ ደስ የሚለኝ ቁርአን መቅራት ነው:: ይህ ደግሞ ሰዎች ከተናገሩት ሁሉ የተመረ

ጠው ተግባር ነው »ብለዋል:: ዑምደቱልቃሪ9/263. ነቢዩ (ﷺ) ኢብኑ ዐባስ በዘገቡት ሐዲስ «በከዕባ ዙሪያ መጠወፍ ልክ እንደ ሶላት ነው:: ባይሆን በጠወፍ ልትነጋገሩ ትችላላችሁ እንጂ :: እናም በጠወፍ ወቅት የተናገረ ሰው መልካም ንግግርን እንጂ ሌላ እንዳይናገር » ብለዋል:: ቲርሚዚ፤ ነሳኢ.ኢብኑኹዘይማህና ሓኪም ዘግበዉታል:: አልባኒም ኢርዋእ ላይ ዘግቦታል::

በሐጀረል አስወድ ላይ የታየው ልዩ ተአምር

ቤቱ እየተገነባ ሲያድግ ቁመቱና ሐጀረልአስወድ ያለበት ቦታላይ ሲደርስ ኢብራሂም ለልጃቸው ለኢስማዒል እንዲህ አሉት ‹አንድ ዲንጋይ ፈልግልኝ ለሰዎች በጠዋፍ ጊዜ ለመጀመሪያ ምልክት እንዲሆናቸው:: ኢስማዒል በመፈለግ ላይ እያለ በቤቱ ዙሪያ ካሉት ከአላህ ተዐምራት አንዱ ይሆን ዘንድ መላኩ ጂብሪል ከጀነት ይዞት ዱብ አለ:: ዋናዉን ሐዲስሓኪም 2/293 ላይዘግቦታል:: ዘሀቢም እንዲሁ::

ነቢዩ (ﷺ) ኢብኑ ዐባስ በዘገቡት ሐዲስ «ሀጀረል አስወድ ከጀነት ሲወርድ- የሰዎች ወንጀል አጠቆረው እንጂ -ከወተት የነፃ ነበር» ብለዋል:: አህመድ. የአደም ልጆች ወንጀል አጠቆረው ማለት የአደም ወንጀል ለመጥቆሩ ምክኒያት ሆነ ማለት ነው:: ይህም ማለት እውነታ ነው:: አህወዚ 3/525.

አነስ ብን ማሊክ « ድንጋዩ ከጀነት ድንጋዮች አንዱ ነው:: ብለዋል:: -ሙሰነፍ ኢብኑ አቢ ሸይበህ3/706.

ዐብዱላህ ብን ዐምር «ድንጋዩ ከጀነት ነው የወረደው ሲወርድ ከበረዶ የነጣ ነበር:: ያጠቆረው የሰዎች ወንጀል ነው:: » ብለዋል:: ሙሰነፍ ኢብኑ አቢ ሸይበህ3/706.

ዲንጋዩ የሚመሰክርበት ቀን አለ:: በዚያ የጭንቅ ቀን ይህን ታላቅ የምስክርነት ቃል ለማገኘት ሲባል ሰለፎች ዲንጋዩን በእጃቸው ለመንካት ከተቻለም በአፋቸው ለመሳም ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል:: ይህም የነቢዩን (ﷺ)ሱና ለመከተል የሚያድረጉት ጥረት ነው:: ነቢዩ (ﷺ)ኢብኑ ዐባስ በዘገቡት ሐዲስ «ይህ ዲንጋይ የተሳለሙትን የሚያይባቸው ሁለት አይኖች፤ የሚናገርበት ምላስ አሉት:: በትክክል ለተሳለመው ሰው ሁሉ ይመሰክራል»ብለዋል:: አህመድ.

ይህ ዲንጋይ በዚህች ዐለም ዉስጥ ሳለ በትክክል ከጀነት የመጣ ነው፤ እሱን መንካትም ሆነ መሳሙ ለአላህ ከሚደረጉት ዒባዳዎች አንዱ ነው ብሎ አምኖ ለተፈፀመው ሰው ሁሉ የቂያማ ዕለት ይመሰክራል:: ዑመር ኢብኑልኸጣብ ይህን ዲንጋይ ሳሙትና «ምንም የማትጠቅም ና የማትጎዳ ዲንጋይ መሆንክን አውቃለሁ:: ነቢዩ ሲስሙህ ባላየሁኝ ኖሮ አልስምህም ነበር»አሉ:: ቡኻሪ 1597. ዐሊይ ዲንጋዩን ሲስሙ «ጌታየ በአንተ አምኜ በኪታብህ ሲድቅ ብየ፤ የነቢዩን ሱና ተከትየ» ይሉ ነበር:: ኢትሃፉልኺብረቲ 3/189

ዲንጋዩን በእጅ መንካትና በአፍ መሳም ተገቢ ነው ::

ነቢዩ (ﷺ) ዲንጋዩን ለመሳም በጣም ጉጉት ነበራቸው:: ወደ እሱ መድረስ ካልቻሉ በእንጨትም ቢሆን ይነኩት ነበር:: አቡ ጡፈይል «ነቢዩ (ﷺ) በከዕባ ሲዞሩ ዲጋዩን በዘንጋቸው ነክተው ያን የነኩበትን ዘንግ ሲስሙት አይቻለሁ» ብሏል:: ሙስሊም፣1275. ነቢዩ (ﷺ) ዙበይር ብን ዐረቢ በዘገቡት ሐዲስ «አንድ ሰው ዐብዱላህ ብን ዑመርን ዲንጋዩን መሳም እንዴት ነው ብሎ ጠየቀ ነቢዩ ሲሰሉሙትና ሲስሙተ አይቻለሁ አሉ:: ግፊ ቢኖርስ ተብለው ሲጠየቁ ቢሆንስ የሚለዉን የመን ላይ ተወው እኔ የምልህ ነቢዩ ሲሰልሙትና ሲስሙት አይቻለሁ ነው የምልህ አሉ» ብለዋል:: ቡኻሪና ሙስሊም. ዐብዱላህ ኢብኑ ዑመር ሱናን ለመከተል የተለያዩ ተልካሻ ምክኒያቶችን እየደረደሩ ማመካኜት እንደማይቻል ግልፅ ትምህርት ሰጥተዋል:: ሆኖም ከአቅም በላይ የሆነ ግፊ ካለ መተዉ አማራጭ እንደሌለው ጥያቄ የለዉም::

ዲንጋዩን በመሳም ላይ ከፍተኛ ጉጉት ማሳደር:: ነቢዩ (ﷺ) ናፊዕ በዘገቡት ሐዲስ «ኢብኑ ዑመር ዲንጋዩን በእጃቸው ሰላም ብለዉት እጃቸዉን ሲስሙት አየሁ:: ከዚያም ይህን ተግባር ነቢዩን ካየሁኝ በኋላ ሁልጊዜም ትተው አላውቅም» ብለዋል:: ሙስሊም1268. ሐዲሱ ድንጋዩን በተ

መለከተ በጣም ክብር እንዲስጠው ማግባባት ዋናው መል ዕክት ሲሆን ኢብኑ ዑመር ነቢዩ በጣም እሱን በመሳለም ከፍተኛ ጉጉት ስላየሁባቸው እኔም ከዚያን ቀን ጀምሬ አል ተውኩም፡፡

ዲንጋዩን በመንከባከብ ላይ ሊጠበቅ የሚገባው ጉዳይ ነው፡፡ ዲንጋዩን መሳለምና በየጦዋፉ ጊዜ ማስታውስ ከመ ልካም ስራዎች አንዱ ነው፡፡ ሙጃሂድና ጣዉስ ሁለቱንም ማዕዘናት በየ ነጠላ ቁጥሩ ሰላም ማለትን ይወዱ ነበር፡ ፡ ዐሊሞችም ዘንድ የሚተገበረው በዚሁ አይነት ነው፡፡ ማለትም በየጦዋፉ ከቻሉ ዲንጋዩን መሳም፤ ካልቻለ በእጁ መንካትና እጁን መሳም፤ በየጦዋፉ ካልቻለ በየነጠላ ቁጥሩ ላይ እጁ መድረስ ካልቻለ እንኳን በአቅጣጫው ላይ ሁኖ አላሁ አክበር በማለት ሰላም ማለት ተገቢ ነው፡፡ ነቢዩ (ﷺ) ሱወይድ ብን ገፈለህ በዘገቡት ሐዲስ «ኢብኑ ዑመር ዲንጋዩን ሰላም ብለው ሲያቅፉትና ነቢዩ በጣም ስለ አንተ ሲጨነቁ አይቻለሁ አሉ» ብለዋል፡፡ ተምሂድ.

ይህ ሁሉ የሚያመለክተው ሱሃቦች ምንንም ነገር የሚያከብ ሩት ነቢዩን ብቻ ተከትለው መሆኑን ነው፡፡

ከተቻለ በሒጅር ኢስማዒል ዉስጥ መስገድ ተገቢ ነው፡ ፡ በከዕባ ዉስጥ መስገድ የብዙ ሰዎች ወደ መካ ሲሄዱ የሚመኙት ህልም ነው፡፡ ከህዝብ ብዛት አኳያ ይህ ህልም ለሁሉም በተግባር የመዋሉ ጉዳይ አይታሰብም፡፡ በተለ ይም እኒያ በሐጀረል አስወድ ላይ እንኳን እግሬ ዉስጥ መግባት እንደሌለባቸው ልዩ ምክር የተቸራቸው ሴት ልጆች፡፡ ነቢዩ (ﷺ) እናታችን ዓኢሻ በዘገቡት ሐዲስ «በከዕባ ዉስጥ ገብቶ መስገድ በጣም እመኝ ነበር፡፡ አን ድቀን ነቢዩ እጀን ያዙና ሒጅር ኢስማዒል የተባለው ቦታ ወሰዱኝና በከዕባ ዉስጥ ገብቶ መስገድካማረሽ እዚህ ስገጂ ምክኒያቱም ይህ ስፍራ የቤቱ አካል ነዉና፡፡ ዘመ ዶችሽ ቤቱን ሲያድሱ በጀት ስላነሳቸው ቀንሰዉት ነው፡ ፡ አሉኝ...» ብለዋል፡፡ አህመድና አቡዳዉድ....አልባኒምት ክክል ነው ብለዉታል፡፡ ይህ ሐዲስ በከዕባ ዉስጥ ገብቶ መስገድ ለሚፈልግ ሰው ሁሉ ምኞቶችን በአጭሩ የሚያ ሳካ መልዕክት ይዟል፡፡ ምክኒያቱም ታሪኩ ከሴት ጋር ስለ ተያያዘ ለወንዶች አይሆንም አይባልምና፡፡

ከተቻለ በዲንጋዩ ላይ መደፋት ተገቢ ነው፡፡ በዲንጋዩ ላይ መደፋት ነቢዩ (ﷺ)የመሰናበቻው ሐጅ ዕለት ወደ መካ ገብተው ለመጀመሪያ ጊዜ የሰሩት ነገር ዲንጋዩን ሰላም ማለትና ከዚያ ጦዋፍ ማድረግ ነው፡፡ ይህ የዲንጋዩ ሰላምታ በመካ ብቻ ከሚደረጉ የአምልኮ ተግባራት አንዱ ነው፡፡ ነቢዩ (ﷺ) ጀዕፈር ብን ዐብዱላህ በዘገቡት ሐዲስ «ሙሐመድ ብን ዐባድ ብን ጀዕፈር ዲንጋዩን ስመው በእሱ ላይ በፊታቸው ተደፉ፡፡ ከዚያም አጎቴን ኢብኑ ዐባስን ስመው በፊታቸው ተደፉ አይቻለሁ ኢብኑ ዐባስም ዑመር ኢብኑልኸጣብንም እንደዚሁ ስመው በፊታቸው ተደፉ አይቻለሁ ከዚያም ነቢዩ እንዲህ ሲያደርጉ ስላየሁ እኔም ይህንኑ አድርጊያለሁ»ብለዋል፡፡ ሙስሊም.





በሶፋና በመርዋ ላይ የሚደረጉት ተክቢራዎች ተገቢ ናቸው:: በመካ ውስጥ ሁለት ታላላቅ ጋራዎች አሉ:: ትልቅነታቸው በአካል ግዝፈት ሳይሆን በሙስሊሞች ዘንድ ባላቸው ክብር ነው:: እነኚህ ሁለት ጋራዎች ከኢብራሂም ወደ ዚህ ቦታ መምጣት ጀምሮ ከከዕባ ታሪክ ጋር ብዙ ሁኔታዎችን አሳልፈዋል:: አላህም ስለ እነሱ ጉዳይ በቁርኣን እንዲህ ሲል «የሶፋና የመርዋ ጋራዎች የአላህን ትዕዛዝ ከመፈፀሚያ ጉልህ ቦታዎች ናቸው»አል በቀራህ 158 አዉስቷል:: ነቢዩ (ﷺ) ጃቢር ብን ዐብዱላህ በዘገቡት ሐዲስ «ነቢዩ ከዲንጋይ እስከ ዲንጋይ ድረስ በሶስቱ ዙር ብቻ ፈጠን፤ ፈጠን እያሉ ይሄዱ ነበር:: ጦዋፍ ሲጨርሱም ሁለት ረከዓ ይሰግዱና ዱዓ ያደርጉ ነበር:: ከዚያም ወደ ዲንጋዩ ይሄዱና ከሳሙት በኋላ ወደ ዘምዘም ዉሃ በመሄድ ከሱ ጠጥተው በራሳቸዉም ላይ ያፈሱ ነበር:: ከዚያም እንደገና ወደ ዲንጋዩ በመሄድ ሰላም ካሉት በኋላ ወደ ሶፋ ጋራ ይሄዳሉ:: ሶፋ ላይ እንደደረሱም «አላህ በጀመረበት እጀምራለሁ» በማለት ሰዕዩን በሶፋ ይጀምራሉ» ብለዋል:: (አህመድ፤ ቲርሚዚና ነሳኢ አልባኒም ትክክለኛ ሐዲስ ነው ብለዉታል) ሐዲሱ ነቢዩ (ﷺ) በመሰናበቻው የሐጅ ተግባር ዘርዘር አድርጎ ይዘግባል::ለዝንተ ዐለሙ ጉዞ መዘጋጀት:: የሰው ልጅ ለትልቅ ስብሰባ ሲዘጋጅ ባማረና በተሸለ ሁኔታ ለመሆን ይዘጋጃል:: እናም ነቢዩ (ﷺ) ወደ እሱ ሊወስዳቸው በፈለገ ጊዜ በዘምዘም ዉሃ አጥቦ ነው:: ነቢዩ አቡ ዘር በዘገቡት ሐዲስ «በመካ ሳለሁ ጣራዩ ተከፈተና ጂብሪል ወርዶ ልቢን ከፈተው ና በዘመዘም ዉሃ አጠበው:: ከዚያም በእምነትና በጥበብ የተሞላ የወርቅ ሰሀን አምጥቶ በልቤ ዉስጥ አፈሰሰው:: ከዚያም ዘጋው ከዚያም እጀን ይዞኝ ወደ ሰማይ ወሰደኝ»ቡኻሪናሙስሊም:: ብለዋል::ይህ ሐዲስ የዘምዘም ትልቅነት ከተነገረባቸው ሐዲሶች አንዱ ነው::

ቤተሰብ አጥጋቢው የዘምዘም ዉሃ:: ነቢዩ (ﷺ)አቡ ዘር በዘገቡት ሐዲስ ወደ ኢስላም የገቡበትን ታሪክ ሲያወሱ፡ -ነቢዩ ከመቼ ጀምረህ እዚህ ቦታ ነበርክ አቡ ዘር፡ ከሰላሳ ቀን ጀምሬ፤ነቢዩ ማን እየቀለበህ፤ አቡ ዘር:- ከዘምዘም በስተቀር ምንም ምግብ አልነበረኝም፤ ቦርጬ እስከሚሰበር ድረስ ወፈርኩ፤ በአንጀቴ ዉስጥ ምንም የረሀብ ስሜት የለኝም:: ነቢዩ የተባረከ እኮነው ለምግብነትም የሚያገለግልነው .....»(ሙስሊም) ቁረይሾች ወደ ነቢዩ የሚመጣን ሁሉ እያሰቃዩ በነበሩበት ዘመንአቡ ዘር ነቢዩን ለማግኘት ወደ ነቢዩ መጥቶ ሰላሳ ቀን ሲያፈላልግ ሰነበተ:: በዚያ ጊዜም ከዘምዘም ዉሃ በስተቀር ምንም ምግብ አልነበረዉም:: ኢብኑ ልቀይም ብዛት ያለቸው ሰዎች ዘምዘመን ቀለብ አድረገው ከግማሽ ወር በላይ የሆኑ ቀናት ሲያሳልፉና እንደማንም ጦዋፍ እያደረጉ አይቻለሁ እንዲዉም አንዳዶቹ እስከ አርባቀን ድረስ ይቆዩ ነበር ብለዋል::

ልዩ የመካ ስጦታ:: ሰዎች ወደ ሆነ ሀገር ደርሰው ሲመጡ ከዚያሀገር ምርጥ ነገሮች ለቤተሰቦቻቸው ይዘው መምጣት የተለመደ ነው:: በመካ ደግሞ ከዘምዘም ዉሃ የተሻለ ምርጥ ነገር የለም:: ነቢዩ እናታችን ዓኢሻ ‹የዘምዘም ዉሃ ይዘው ይሄዱነበር ለምንድነው ተብለው ሲጠየቁ ነቢዩም ይህን ያደርጉ ነበርብለዋል»(አህመድ አልባኒምትክክልነው ብለዋል)የመካ ሰዎች ለሌሎች ከሚያበረክቱት ስጦታ ሁሉ የዘምዘም ዉሃ መሆኑንነው:: ኢብኑ ዐባስ እንግዳ ሲመጣ የሚያበረክቱለት የዘምዘም ዉሃ ነበር:: ዐጣእ ኢብኑ አቢ ረባህ ከዕብ ሀጅ ባደረገ ጊዜ አስራሁለት ወይም አስራስድስት የዘምዘም ዉሃ ይዘው ወደ ሻም ሂደዋል» ብለዋል:: አንዳደንድ የኢንዱኑሲያ ሀጀኞች ለመካ ወጣቶች እንደተናገሩት የዘምዘም ዉሃ ወደ ሀገራቸው ወስደው በቡና ሲኒ እንደሚያቀምሷቸው ነግረዋቸዋል:: ይህንም ተግባር በጣም እንደሚደነቅ ነግረዋቸዋል::


የተውሳኮች ሁሉ ፍቱን መድሐኒት የሆነው የዘምዘም ዉሃ:: ከአመት እስከ አመት ብዙ ቁጥር ያለቸው ሰዎች

ለሐጅ ወይም ለዑምራ ወይም ለጉብኝት ወደ መካ በገፍ ይጓዛሉ፡፡ በተለይም በሐጅ ወራትና በረመዷን ወር ላይ፡፡ ይህ አይነቱ ስብስብ ደግሞ የተለያዩ በሺተዎችን ሊያስከትል እንሚችል ያሰጋል፡፡ ግን በአላህ ቤት አጠገብና በዚያ ለሁሉም በሺታ መድህን የሆነው ተዐምረኛው የዘምዘም ዉሃ አጠገብ በመሆናቸው በአላህ ጥበቃ ስር ስላሉ በምንም በሺታ ሲጠቁ አይታዩም፡፡

ነቢዩ ኢብኑ ዐባስ በዘገቡት ሐዲስ «በምድርዉስጥ ካሉ ዉሃዎች ሁሉ ምርጡ የዘምዘም ዉሃ ነው፡፡ ለምግብነት ለሚፈልጉት ሁሉ ምግብ ነው፡፡ ለመድሃኒትነት ለሚፈልጉ ትም እንዲሁ መድህኒት ነው»ብለዋል፡፡ (ቡኻሪ በታሪ መፅሐፉና ሙስሊም)

ዘምዘምን በመስጠት ምግብና ዉሃ እንዲሆን ከማድረጉም በተጨማሪጤናም ለሚፈልግ ሰው ሁሉ ፍቱን መድሀኒት አደረገው፡፡ የመካ ኗሪዎች ይህን እውነታ በገሃድ ያስዉሉታል፡፡ ይህ ረድኤት የመጀመሪየው «ያመሰግኑህም ዘንድ ከፍሬዎች ስጣቸው » ኢብራሂም 37 ያለው ነው፡፡ ኢብኑ ዐባስ ሲጠጡት «አንተን ብቻ እገዛለሁ ከአንተ ብቻ እርዳታ እጠይቃለሁ...»አልፋቲሐሕ. በማለት ይጠጡት ነበር፡(ዳረ ቁጥኒ2/288.) ኢብኑልቀይም የዘምዘምን መድሃኒትነት በራሴ ሞክሪዋለሁ፡፡ ብዙ ተዐምራት አይቸበታለሁ፡፡ ከብዙ በሺታዎችም በአላህ ድንኜበታለሁ) ብለዋል፡፡ (ዛዱልመዓድ 4/178.) እንደዚሁም በመካ ሳለሁ ታም ሜነበር ሐኪምም መደሀኒትም አጥቼ «... ባለው እያታከምኩኝ ነበር፡፡ ሙስሊሞች ሁሉ ይህን ቤት ለመጎብኘት ሲያስቡ ሁሉን ነገር ወደ ኋላ ትተው ይህ ጉዳይ ብቻ ነው ምኞታቸው፡፡ ነቢዩ አቡ ሁረይራ በዘገቡት ሐዲስ «ይህን ቤት ለሐጅ የጎበኜና ስለ ስሜት ያላወራ ወንጀልም ያልፈፀመ ሰው እናቱ ስትወልደው እንደነበረ ሁኖ ይመለሳል» ብለዋል፡፡ (ቡኻሪና ሙስሊም)

<u>ልቦች ሁሉ ወደ መካ ይናፍቃሉ፡፡</u> ሱፍያን ብን ዑየይነህ በሙዝደሊፋ ላይ ተኟተው ለአንድ ጓደኛቸው እዚህ ቦታ ሰባ ጊዜ መጥቻለሁ በየአመቱ መጨረሻ አታድርግብኝ እላለሁ፡፡ አሁን በየ ጊዜው ይህኑ ጉዳይ መጠየቁ አሳፈረኝ አሉ፡፡ ከዚያም ተመልሰው በዚያው አመት ሞቱ፡፡



ነቢዩ ዐብዱላህ ብን መስዑድ በዘገቡት ሐዲስ «ሐጅንና ዑምራን አከታትሉ፡፡ ምክኒያቱም እሳት በብረት፤ በወርቅና በብር ላይ ያለን ቆሻሻ እንደሚያስወግድ ሁሉ ሁለቱም ዒባዳዎች ድህነትንና ወንጀሎችን ያስወግዳሉና ትክክለኛ ሐጅ ክፍያው ጀነት ብቻ ነው» ብለዋል፡፡ (አህመድ፤ ቲርሚዚ፤ ነሳኢ ኢብኑ ሒባን አልባኒም ትክክለኛ ነው ብለዋል)

<u>ሓጅ የተከበረው እንግዳ/ልዑክ/ ነው፡፡</u> ነቢዩ (ﷺ) ዐብዱላህ ብን ዑመር በዘገቡት ሐዲስ «ለአላህ ሲል የዘመተ፤ ለሀጅ የወጣ፤ ለዑምራ የወጣ ሰው የአላህ ልዑክ ነው፡፡ ጠርቷቸው አቤት ያሉ፤ ለምነዉት የሰጣቸው ናቸው» ብለዋል፡፡ (ኢብኑ ማጀህ ጦበራኒ ኢብኑ ሒባን አልባኒም ትክክለኛ ሐዲስ ነው)

<u>መካየትየክክለኛው እምነት/መደበቂያ/ መሰበሰቢያ ቦታ ነው፡፡</u>

ነቢዩ (ﷺ) ዐብዱላህ ብን ዑመር በዘገቡት ሐዲስ «ኢስላም ሲጀምርም እንግዳ ነበር በመጨረሻው ዘመንም ልክ እንዲሁ እንግዳ ይሆናል፡፡ እባብ በዋሻዋ እንደምትሰበሰብ ሁሉ ኢስላምም በሁለቱ መስጂዶች መካከል ብቻ ይወሰናል›ብለዋል፡፡



# የልጆች አስተዳደግ በኢስላም

ልጆች የአላህ አማና ናቸው፡፡ ልጆች የሕይወት ተስፋም ናቸው፡፡ ያአይን ማረፊያዎች ፤ የነገ ገንቢዎች፤ የወደፊት አደራ ተረካቢዎች ናቸው፡፡ የአባቶች አማና ጠባቂዎች ናቸው፤ ዲናቸውን በጥንቃቄ በመጠበቅ ጌታቸውን ይታዘዛሉ፤ ለዚህም ብሎ ኢስላም አባቶችን እንዲንከባከቧቸው እና በትኩረት እንዲያሳድጓቸው አደራ ጥሎባቸዋል፡ ፡ ይሄውም ከራሳቸው አልፈው ማህበረሰባቸውን እንዲጠቅሙ በሚል ነው፡፡ እኛ ሙስሊሞች ወደ ዋናው ዲናችን በመመለስ የወደፊት ተስፋ ወጣቶችን በትክክል ማሳደግ ይጠበቅብናል፡፡ የመልካም አስተዳደግ ዋናው ምሰሶው በትክክል እምነት ኮትኩቶ እና በመልካም ስነ ምግባር አንጾ ማሳደግ ነው፡፡ የትውልዶች ግዴታ ምድርን በአላህ ፍራቻ ላይ በተመሰረተ ልማት ማልማት ነው፡፡

አላህ በቁርኣን እንዲህ አለ (ገንዘብና ወንዶች ልጆች የቅርቢቱ ህይወት ጌጦች ብቻ ናቸው፡፡ መልካም ቀሪ ሥራዎች ግን በጌታህ ዘንድ በምንዳ በላጭ ናቸው፡፡ በተስፋም በላጭ ናቸው›› አል ከህፍ 46”፡፡

ለዚህም ነው ነብዩ ኢብራሂም መልካም ዙርያ እንዲሰጣቸው አላህን በድንብ ተናንሰዉና ዝቅ ብለው የለመኑት)

ቁርኣን እንደህ አለ (ገንዘብና ወንዶች ልጆች የቅርቢቱ ህይወት ጌጦች ብቻ ናቸው፡፡ መልካም ቀሪ ሥራዎች ግን በጌታህ ዘንድ በምንዳ በላጭ ናቸው ፡፡ በተስፋም በላጭ ናቸው )18፡ 46. እንዲህም አለ ‹‹ጌታየ ሆይ ! ከመልካሞቹ የሆነን ልጅ ስጠኝ፡፡ ታጋሽም በሆነ ወጣት ልጅም አበሰርነው›› አሷፋት 100-101.ነብዩ ዘከርያም እንደዚሁ ዝቅ ብለው የለመኑ መሆናቸውን ቁርአን እንዲህ ይላል፤ ( ይህ ምዕራፍ ጌታህ ባርያውን ዘከሪያን በችሮታው ያወሳበት ምዕራፍ ነው፡፡ ጌታው የሚስጢርን ጥሪ በተጣራ ጊዜ የሆነውን አስታውስ፡፡ ጌታዬ ሆይ ! እኔ አጥንቴ ደከመ፡፡ ራሴም በሽበት ተጥለቀለቀ፡፡ ጌታዬ ሆይ! አንተንም በመለመኔ ! ምንጊዜም ዕድለ ቢስ አልሆንኩም አለ፡፡ እኔም ከበኋላዬ ከሞትኩ በኋላ ዘመዶቼን ከእምነት እንዳይወጡ ፈራሁ፡፡ ሚስቴም መካን ነበረች፡፡ ስለዚህ ከአንተ ዘንድ ለእኔ ልጅን ስጠኝ፡፡ የሚወርሰኝ ከየዕቁብ ቤተሰቦች የእምነትን ሃላፊ

ነት የሚወርስን ልጅ ስጠኝ:: ጌታዬ ሆይ ! ተወዳጅም አድርገው አለ›› “መርየም 5-6”

ልጆች የአባቶች እና የእናቶች ብቻ ሀብቶች ሳይሆኑ የማህበረሰብም ሀብቶች ናቸው:: በመሆኑም አባቶች መልካም ተግባር ሁሉ በነሱ ይደሰታሉ:: በጥፋታቸዉም በአላህ ዘንድ ይጠየቃሉ:: በማህበረሰቡም ልጆችን በቅድሚያ እንድናሳድግበት የታዘዝነው ትክክለኛው እምነት ነው፤

በዚህ ጉዳይ ነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) ተርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ ለዐብደላህ ኢብን ዐባስ እንዲህ ብለዋል፡- (አንድ ቀን ከነቢዩ ኋላ ነበርኩ:: እንዲህም አሉኝ:: “አንተ ልጅ እኔ ጥቂት ቃላትን ላስተምርህ፡- የአላህን ተዕዛዝ ጠብቅ፤ እርሱም ይጠብቅሃልና:: አላህን ጠብቀው፤ ከፊት ለፊትህ ታገኘዋለህና:: ስትጠየቅ አላህን ጠይቅ፤ እርዳታ ከፈለግህ በአላህ ተረዳ:: ህዝቦች ሁሉ ሊጠቅሙህ ቢሰበሰቡ ሊጎዱህ አይችሉም፤ አላህ በእርግጥ ባንተ ላይ የወሰነብህ ነገር ቢሆን እንጂ:: ብዕሮች ተነስተዋል፤ ገጾቹም ደርቀዋል::” (ቲርሚዚይ ዘግበውታል) ሌሎች ዘጋቢዎች ደግሞ፡- “አላህን ጠብቀው ከፊትህ ታገኘዋለህ:: ከአላህ ጋር በሰላም ጊዜ ተዋወቅ፤ በችግር ጊዜ ዕውቅና ይሰጥሃልና:: ያላጋጠመህ ነገር ሊደርስብህ ያልነበረና፤ የደረሰብህም ነገር ደግሞ የሚያልፍህ እንዳልነበረ እወቅ:: ድል ከትዕግስት ጋር፤ እርካታ ከጭንቅ ጋር፤ ችግርም ከምቾት ጋር መኖሩን እወቅ::” እንዲህም አለ፡- ነቢዩ ‹አላህን ጠብቅ› ማለታቸው ሕግጋቱን እና ሸሪዓውን ማለታቸው ነው:: ባዘዘው በመገኘት ከከለከለው በመራቅ:: አላህም ይጠብቅሃል በሃይማኖትህ፤ በቤተሰብህ፣ በገንዘብህ:: መልካም በመሥራትህ በመልካም ነገር ይመነዳሃል:: ከክህደትና ከመንሸራተት ይጠብቅሃል:: ‹ከፊትህ ታገኘዋለህ› ማለት ቅርብህ ይሆናል፣ ይረዳሃል፣ ይመራሃል፣ ማለት ነው:: በአጠቃላይ መላ ሕይወትህን ከአላህ ጋር አድርግ:: እሱን ብቻ ለምን፤ ተማፀን:: ከሱ ብቻ ፈልግ:: ሰዎች ሊጠቅሙህም ሆነ ሊጎዱህ የሚችሉት አላህ ሲፈቅድ ብቻ ነው) ብለዋል::

በኢስላም ልጆችን ማስተማር ግዴታ ነው:: አላህም እንዲህ ብሏል ( (ሰውንም በወላጆች በጎ እንዲያደርግ በጥብቅ አዘዝነው:: እናት ከድካም በላይ በሆነ ድካም አረገዘችው:: ጡት መጣያውም በሁለት ዓመት ውስጥ ነው:: ለእኔም ለወላጆችህም አመስግን:: በማለት አዘዝነው መመለሻው ወደ እኔ ብቻ ነው:: ለአንተ በእርሱ እውቀት የሌለህን ነገር በእኔ እንድታጋራ ቢታገሉህም አትታዘዛቸው:: በቅርቢቱም ዓለም በመልካም ስራ ተወዳጃቸው:: ወደ እኔም የተመለሰን ሰው መንገድ ተከተል:: ከእዚያ መመለሻችሁ ወደ እኔ ነው:: ትሰሩት የነበራችሁትንም ሁሉ እነግራችኋለሁ አልነው:: ሉቅማንም አለ ልጄ ሆይ ! እርሷ መልካም ተግባር ወይም መጥፎ ተግባር የሰናፍጭ ቅንጣት ክብደት ያህል እንኳን ብትሆንና በቋጥኝ ውስጥ ወይም በሰማያት ውስጥ ወይም በምድር ውስጥ ብትሆን አላህ ያመጣታል:: አላህ ሩህሩህ፤ ውስጠ አዋቂ ነውና:: ልጄ ሆይ ! ሶላትን አስተካክለህ ስገድ በበጎ ነገርም እዘዝ ከሚጠላም ሁሉ ከልክል በሚያገኝህም መከራ ላይ ታገስ ይህ በምር ከሚያዙ ነገሮች ነው:: ጉንጭህን በኩራት ከሰዎች አታዙር:: በምድርም ላይ ተንበጥርረህ አትሂድ:: አላህ ተንበጥራሪ ን ጉረኛን ሁሉ አይወድምና:: በአካሄድህም መካከለኛ ሁን:: ከድምጽህም ዝቅ አድርግ:: ከድምጾች ሁሉ አስከፊው የአህዮች ድምጽ ነውና ››31፡14-19 )

እንዲህም አለ (እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ! እነዚያ እጆቻችሁ የጨበጧቸው ባሮች እነዚያም ከእናንተ መካከል ለአካለ መጠን ያልደረሱት ህፃናት ከጎህ ስግደት በፊት፤በቀትር ልብሶቻችሁን በምታወልቁበት ጊዜና ከምሽት ስግደትም በኋላ በሶስት ጊዜያት ወደ እናንተ ለመግባት ሲፈልጉ ያስፈቅዷችሁ:: እነዚህ የእናንተ ሶስት የሐፍረት ገላ መገለጫ ጊዜያቶች ናቸውና:: ከእነዚህ ግን በእናንተም ሆነ በነሱ ላይ ያለፈቃድ በመግባት ኃጢአት የለም:: እናንተን ለማገልገል በዙሪያችሁ ዟሪዎች ናቸውና:: ከፊላችሁ በከፊሉ ላይ ዟሪ ነውና፤ ልክ እንደዚሁ አላህ ለእናንተ ህግጋትን ይገልጽላችኋል:: አላህ ሁሉን ዐዋቂና ጥበበኛ ነውና:: ከእናንተም መካከል ለአቅመ አዳም በደረሱ ጊዜ

እነዚያ ከእነርሱ በፊት የነበሩት ታላላቆች እንዳስፈቀዷችሁ ያስፈቅዱ:: ልክ እንደዚሁ አላህ ለእናንተ እንቀጾችን ያብራራል:: አላህ ዐዋቂና ጥበበኛ ነው» አል ኑር. 58. ዑመር ኢብኑ ሰለማህ (ከነብዩ ጋር የሚያድግ ህፃን ነበርና እንዲህ የአላህን ስም አውሳ፤ በቀኝህ ብላ፤ ከፊት ለፊትህ ብላ ብለው ስለ አስተማሩኝ ከዚያ ጊዜ ጀምሬ በዚሁ መልኩ ነው የምበላው:: ብሏል::....) ቡኻሪና ሙስሊም.

ኢስላም በልጆች መካከል የሚደርጉ ስጦታዎች ማበላለጥ ክልክል ነው፤ በሴትና በውንድም መካከል ቢሆንም እንኳን፤ በዚህ መልኩ ያደጉ ልጆች ወላጆቻቸውን ብቻ ሳይሆኑ የሚኖሩበት ማህበረሰብም ይታደላል::

<u>የልጆች ለአባቶች ተተኪነት ሂደት እንዴት መምጣት እንዳለበት</u>

የልጆችን ተተኪነት ለመግለፅ አባቶቻችን እንዲህ ይላሉ ነበር «የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች» :: ይህ አባባል በጣም ሰፊና ጥልቅ መልዕክት አለው:: ከአባባሉ እንደ ምንረዳው አበባው በደንብ ካልተኮተኮተ በዙሪያው ያሉት አረሞች ካልተወገዱለት የምንፈልገውን ፍሬ ያህል ማግኘት አይቻልም :: ቢገኝ እንኳ ምን አልባትም የቀጨጨው በድጋሚም ዘር ሆኖ ሌሎች አበቦችን መተካት ላይችል ይችላል:: ዛሬ ልክ እንደ አበባው ዙሪያ እንደሚበቅሉት አረሞች እስልልምናችንን ለማቆሸሽ እና ልጆቻችንን ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ የሚወስዱ በርካታ ነገሮችን አለም እያስተናገደችበት ያለችበት ሁኔታ ላይ እንገኛለን:: ስለዚህ ሙስሊሙ ማህበረሰብ ለነገው ብቁ ተተኪ እንዴት ማፍራት እንዳለበት ማሰብና መጨነቅ ይገባዋል::

ልጆች ለምድራዊው አለም ደስታ ከአላህ የተሰጡን ፀጋዎች ናቸው:: ለእነዚህ ፀጋዎች አካላዊ እድገት እንደም ንጠነቀቀው ሁሉ ለውስጣዊ ስሜታቸውና አስተሳሰባቸው መዳበር የምንጠነቀቅ ከሆነ በአግባቡ የአላህንና የመልዕክተኛውን የነብዩ ሙሀመድን ፍቅር በውስጣቸው ቀርፀን ካሳደግናቸው ጥረታችን እና ድካማችን ፍሬያማ ይሆናል::

<u>አላህም በቁርአኑ ላይ እንዲህ ይላል</u> «እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ ! ነፍሶቻችሁና ቤተሰቦቻችሁን መቀጣጠያዋ ሰዎችና ደንጊያዎች ከሆነች እሳት ጠብቁ፤በእርሷ ላይ ጨካኝና ኃይለኛ የሆኑ መላዕክት አሉ:: አላህን ያዘዛቸውን ነገር በመጣስ አያምፁም፤ የሚታዘዙትን ሁሉ ይሰራሉ" አትተህሪም 6"_በተጨማሪም አንተ ልጅ አሳዳጊ ሆይ ከምንም በፊት መጀመሪያ ራስህን ማስተካከል አለብህ:: ምክንያቱም ልጆች ዘንድ የምትሰራውን በሙሉ መልካም ነው ከልጆች ዘንድ ደግሞ አንተ ያልፈፀምከው ባጠቃላይ መጥፎ ነውና የሚሉት ይገኙበታል::

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የቁርአን አንቀፆችና ሐዲሶች እነደምንረዳው እናት፤ አባት አስተማሪና ማህበረሰቡ በሙሉ ስለ ልጆች አስተዳደግ አላህ ፊት ተጠያቂዎች ናቸው:: ልጆችን በጥሩ ሁኔታ ብታሳድጓቸው ልጆችም ሆኑ አሳዳጊዎች በዚህችም አለም ሆነ በመጪው አለም እድለኞች ይሆናሉ የሚሉት መልእክቶች ዙሪያ ያጠነጥናሉ :: ስለዚህ እኛ ወላጆች ይህን ያክል ሀላፊነት እንዳለብን ካወቅን እንዴት ልጆቻችንን አላህ በሚፈልገው መንገድ አሳድገን ለእኛና ለልጆቻችን አልፎም ለኢስላም ተቆርቋሪና ተተኪ እሚሆኑት እንዴት አድርገን ስናሳድጋቸው ነው ? የሚሉ

የላኢላህ ኢለላህ ሙሀመድ ረሱሉላህን ትርጉም ስንነግራቸው በቃላቸው እንዲይዙ ስናደርጋቸው፤ እኛን የፈጠረን ፤ ሲሳይ የሚለግሰን ፤ በኛላይ ለሚከሰት መከራ ሊረዳንና ሊያስወግድልን የሚችለው አጋሪ የሌለው ብቸኛ የሆነው አምላካችን ሀያሉ አላህ ብቻ መሆኑን በመንገር፤ ስለ ጀነት እና ጀሀነም ምንነት በማስረዳት ጀነትን የሚወርሱት ሰላትን የሚሰግዱ፤ ፆምን የሚፆሙ፤ ወላጆቹን ለሚታዘዙና ለሚያከብሩ፤ አላህ የሚወደውን የሚሰሩ መሆናቸውን እና የዚህን ተቃራኒ የሰሩ ጀሀነም እንደሚሆኑ በመግለፅ፤ ስለ ሰላት ምንነት አስፈላጊነት በማስረዳት፤

የተከበረ የሆነውን ቁርአንን በማስተማር የአላህን ቃል እንዲረዱ በማድረግ፤ ልጆች ከክህደት ፤ሰዎችን ከመሳደብና

ፀያፍና ወራዳ ንግግርን እንዳይናገሩ በማስጠንቀቅ፤ የሀራ ምና ሀላል (የመጥፎና በጎ) ስራዎችን መግለጫ ዝርዝር አድርጎ በማስረዳት ሀራም ስራዎችን እንዳይሰሩና ሀላል (በጎ) ሥራዎችን አብዝተው መስራት እንዳለባቸው በመ ንገር፤ቁማር ፤ሱስ አምጪ መጠጦችና ጭሶችን ለሂወታ ቸው አደገኛና በአላህም ዘንድ የተጠሉ መሆናቸውን በማ ስረዳት፤ ሐሰትን ባለመናገር እውነትን መናገርን እንዲለማ መዱ በማድረግ ይህንን ነገር እናደርግላቹኃለን ብለን ቃል ከገባንላቸው ቃላችንን በማክበር ማሳየት፤ ከአላህ ውጪ የሆነን አካል መማፀን ሽርክ መሆኑን መንገርና ሽርክ ከእስ ልምና እንደሚያስወጣ በማስረዳት፤ ወንድም ይሁን ሴት ልጅን የአለባበስ አደብን በማስተማር በተለይ ሴት ልጅ ለአቅመሄዋን በምትደርስበት ጊዜ መሸፈን እንዳለባት፤ እን ዲሁም ከሁለቱ ፆታ ለእያንዳንዳቸው የተመደበላቸውን የልብስ አይነት መልበስ እንዳለባቸው ፤በአድ የሆኑ የውጪ ህዝቦችን ሞዴል እንዳይለብሱ በመምከር፤

ኢስላማዊ የሆነ አመጋገብ ስርዐትን በማስተማር ሲመገቡ ፤ሲጠጡ፤ ሲተኙም ይሁን ስራ ሲሰራ በቀኝ እጅ እንደሆነ በመንገር እናቢስሚላህ ብለው እንዲጀምሩ ሲጨርሱም አልህምዱሊላህ ማለት እንዳለባቸው በማስተማር፤

ንፁህናቸውን እንዲጠብቁ፤ ጥፍራቸውን እንዲቆርጡ፤ከም ግብ በፊትም ሆነ በኃላ እጃቸውን መታጠብ እንዳለባቸው ፤ ልብሶቻቸው እዳይቆሸሽ እዲጠብቁ በማስረዳት፤ የአከባ ቢያቸውን ንፅህና እንዲጠብቁ በማሳየት ቆሻሻ በየቦታው እንዳይጥሉ በመምከር፤ መጥፎ ጓደኛ እንዳይዙ በማስጠን ቀቅ፤ ሰዎችን በተለያዩ ቦታዎች ሲያገኙ አሰላሙ አለይኩም ወራህመቱላሂ ወበረካቱሁ በማለት ሰላም እንዲሉ በማስት ማር ማሳየት፤ ጎረቤት ለሆኑ ሰዎች በጎ ነገር መስራት እንዳ ለባቸው፣ ጎረቤቶችን ማስቸገር ክልክል እንደሆነ በመንገር ልጆች ለወላጆችም ማድረግ ያለባቸውን እንክብካቤ እንዲ ሁም ወላጆቻቸውን በመንከባከባቸው በአላህ ዘንድም ምን ያክል ምንዳ እንደሚያገኙ በማስተማር፤ ከመግቢያው ላይ ለመግለፅ እንደተሞከረው ልጆች ማለት የዛሬ አባባዎች የነገ ፍሬዎች ማለት የዛሬ ልጆች የነገ ወላጆች፤ የዛሬ ተማ ሪዎች የነገ አስተማሪዎች፤ የነገ ማህበረሰብ /የኡማው/ ተተ ኪዎች ወይም የሀገር ተረካቢዎች ስለሆኑ ልጆቻችንን በት ክክለኛ መንገድ ላይ ማስተማርና መቅረፅ ወደር የማይገኝ ለት አማራጭ መሆኑን አውቀን የተሰጠንን አደራ ጠብቀን ተተኪ እናደርጋቸው ዘንድ እስልምና ያስተምረናል፡፡

የሚከተሉት ጉዳዮች ኢስላም ለቤተሰብ ልዩ እንክብካቤና እገዛ ማድረጉን በግልጽ ያሳያሉ፡-

ኢስላም በጋብቻ ጅማሬና በቤተሰብ ምስረታ ላይ ልዩ እይታ አለው፡፡ በመሆኑም ከስራዎች ሁሉ የላቀ ተግባር ከመሆኑም ባሻገር፣ የመልከተኞች ፈለግ እንዲሆንም አድር ጎታል፡፡ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ነገር ግን እኔ እጾማ ለሁ እፈታለሁም፤ እሰግዳለሁ አሸልባለሁም፤ ሴትም አገባ ለሁ፡፡ ከኔ ፈለግ የወጣ ከኔ አይደለም፡፡» (ቡኻሪ 4776 / ሙስሊም 1401) ቁርኣን ከታላላቅ ተዓምራትና ጸጋዎች ጎራ ከቆጠራቸው ነገሮች አንዱ አላህ በባልና ሚስት መሐከል ፍቅርን እዝነትንና እርካታን ማድረጉን ነው፡፡ አላህ እንዲህ ይላል፡- «ለናንተም ከነፍሶቻችሁ ሚስቶችን ወደነርሱ ትረኩ ዘንድ መፍጠሩ፣ በመካከላችሁም ፍቅርንና እዝነትን ማድረጉ ከአስደናቂ ምልክቶቹ ነው፡፡ በዚህ ውስጥ ለሚ ያስተውሉ ሕዝቦች ታምራቶች አልሉ፡፡» (አል- ሩም 21)

ጋብቻን ገር ማድረግ፣ ለማግባት የሚፈልግም ሰው ነፍሱን ከዝሙት እንዲጠብቅ መረዳትና መታገዝ እንዳ ለበት ትዕዛዝ ተላልፏል፡፡ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «አላህ ሦስት ዓይነት ሰዎችን ለመርዳትና ለማገዝ በራሱ ላይ ግዴታ አድርጓል፡፡» አሉና ከነሱ መካከል፣ «ጥብቅነ ትን ፈልጎ ጋብቻን የፈፀመን ሰው» ጠቅሰዋል፡፡ (ቲርሚዚ 1655)

ወጣቶችን ገና በአፍላ ዕድሜያቸውና ባልተነካ ጉልበታ ቸው ላይ ሳሉ ጋብቻን እንዲፈፅሙ አዟል፡፡ ምክንያቱም ጋብቻ ለነሱ መርጊያቸውና መርኪያቸው ስለሆነ ነው፡፡ ለፍቶት ስሜታቸውና ፍላጎታቸው ትክክለኛ መፍትሄም ነው፡፡

ኢስላም ለእያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ወንድም ሆነ ሴት ልዩ ክብር ሰጥቷል፡፡

ኢስላም ልጆችን የመንከባከብና በማሳዳግ ጉዳይ በእና ትና በአባት ላይ ከባድ ኃላፊነት ጥሏል፡፡ ዐብዱላህ ኢብኑ ዑመር፣ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ሲሉ ሰምቻቸዋለሁ ማለታ ቸው ተላልፏል፡- «ሁላችሁም እረኞች ናችሁ፤ ማናችሁም ከሚጠብቀው ይጠየቃል፡፡ አንድ መሪ እረኛ ነው፤ በጥበ ቃው ስር ስላሉት ሁሉ ተጠያቂ ነው፡፡ አባወራ በቤተሰቡ ላይ እረኛ ነው፤ በርሱ ስር ስላሉት ሁሉ ተጠያቂ ነው፡፡ ሴትም በባሏ ቤት ውስጥ እረኛ ነች፤ በርሷ ስር ስላሉት ሁሉ ተጠያቂ ነች፡፡ ባሪያ በአሳዳሪው ንብረት ላይ እረኛ ነው፡፡ በርሱ ስር ስላሉት ሁሉ ተጠያቂ ነው» (አል ቡኻሪ 853 /ሙስሊም 1829)

ኢስላም ለአባቶችና ለእናቶች ክብር በመስጠትና ደረጃቸ ውን በመጠበቅ፣ እንዲሁም እስከ ህልፈተ ሕይወታቸው ድረስ እነርሱን መንከባከብና ትዕዛዛቸውን መፈፀምን አስ መልክቶ ልዩ ትኩረት ቸሯል፡፡

## ኢስላም ለእናትና ለአባት ክብር የመስጠትን መሰረት ጥሏል፡፡ .

ወንድ ወይም ሴት ልጅ፣ ምንም ያህል ትልቅ ሰው ቢሆኑም ለወላጆቻቸው ታዛዥ የመሆንና ለነሱ በጎ የመዋል ግዴታ አለባቸው፡፡ አላህ ይህንን ጉዳይ ከርሱ አምልኮ ጋር አቆራ ኝቶ ጠቅሶታል፡፡ እነርሱ ላይ በንግግርና በተግባር ድንበር ማለፍን ከልክሏል፡፡ በነሱ መናደዱን የሚመለክትን ቃል ወይም ድምፅ ማሰማትንም ሳይቀር ከልክሏል፡፡ «ጌታህም (እንዲህ ሲል) አዘዘ፤ እርሱን እንጂ ሌላን አትገዙ፤ በወ ላጆቻችሁም መልካምን ስሩ፤ በአንተ ዘንድ ኾነው አንዳ ቸው ወይም ሁለታቸው እርጅናን ቢደርሱ ፎህ አትበላ ቸው፤ አትገላምጣቸውም፤ ለነርሱም መልካምን ቃል ተናገ ራቸው፡፡» (አል- ኢስራእ 23)

ኢስላም የወንድም ሆነ የሴት ልጆችን መብት እንድንጠ ብቅ አዟል፡፡ በመካከላቸው በወጪም ሆነ በይፋ በሚታዩ ጉዳዮች ላይ ፍትሃዊ መሆንም ግዴታ ነው፡፡ ኢስላም በአንድ ሙስሊም ላይ ዝምድናን የመቀጠል ግዴታ ጥሎ በታል፡፡ ይህ ማለት በእናቱም ሆነ በአባቱ በኩል ያሉትን ዘመዶቹን ዝምድና በመቀጠልና ለነርሱ በጎ በመዋል ይገ ለፃል፡፡

ወንድሞቹ፣ እህቶቹ፣ አጎቶቹ፣ አክስቶቹና ልጆቻቸው እዚህ ውስጥ የሚገቡ ሲሆን ለነርሱ መልካም መስራት፣ ከታላላቅ ወደ አላህ መቃረቢያዎችና ታዛዥነትን መግለጫ መንገዶች መካከል ቆጥሮታል፡፡ ዝምድናቸውን ከመቁረጥ፣ ወይም ክፉ ነገር በነርሱ ላይ ከመፈፀም እንድንርቅ አስጠን ቅቋል፡፡ ይህን ማድረግን ከከባባድ ወንጀሎች ፈርጇታል፡፡ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ዝምድናን ቆራጭ ጀነት አይ ገባም፡፡» ( ቡኻሪ 5638 /ሙስሊም 2556)

## ሴት በኢስላም ውስጥ ያላት ስፍራ

ኢስላም ሴት ልጅን እጅግ በጣም አክብሯታል፡፡ ለወንዶች ባሪያ ከመሆንም ነፃ አውጥቷል፡፡ ክብርና ደረጃ የሌላት ውዳቂና ርካሽ ከመሆንም አድኗታል፡፡ ከሴት ልጅ ክብር ጋር ተያያዥነት ካላቸው ኢስላማዊ ድንጋጌዎች መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

ኢስላም ለሴት ልጅ ፍትሃዊ በሆነ ክፍፍሎሽ የውርስ ድር ሻዋን ሰጥቷል፡፡ በአንዳንድ ስፍራ ከወንድ ጋር እኩል ታገ ኛለች፡፡ በአንዳንድ ስፍራ ደግሞ ድርሻዋ ከወንዱ ይለያል፡ ፡ ይኸውም ለሟች ባላት ቅርበት፣ እንዲሁም ካለባት ኃላ ፊነትና ወጪ አንጻር የሚወሰን ነው፡፡

በሌሎች በርካታ ጉዳዮች ላይ ወንድና ሴትን እኩል አድር ጓቸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል ማንኛውም ገንዘብ ነክ እንቅ ስቃሴ አንዱ ነው፡፡ ነብዩ እንዲህ ብለዋል፡- «ሴቶች የወን ዶች ክፋይ ናቸው» (አቡ ዳውድ 236)

ኢስላም ለሴት ልጅ ባሏን የመምረጥ ነፃነት ሰጥቷል፡ ፡ ልጆችን የማሳደግ ትልቅ ኃላፊነት ደግሞ ጥሎባታል፡፡ ነብዩ እንዲህ ብለዋል፡- «ሴት ልጅ በባሏ ቤት ውስጥ ጠባቂ ነች፤ ከምትጠብቀው ነገር ተጠያቂ ነች፡፡» (አል ቡኻሪ 853 / ሙስሊም 1829)

ስሟና በአባት የመጠራት ክብሯ እንዲቆይ አድርጓላታል፡፡ ከጋብቻ በኋላም በአባት መጠራቷ ይቀጥላል፡፡ ምን ጊዜም በአባቷና በቤተሰቦቿ መጠራቷም ይዘልቃል፡፡

ወጪያቸውን መሸፈን ከሚኖርበት ሴቶች መካከል ከሆነች ማለትም ሚስቱ እናቱ ወይም ሴት ልጁ ከሆነች፣ ኢስላም በወንዱ ላይ እሷን የመጠበቅና ወጪዋን የመሸፈን ግዴታ ጥሎበታል፡፡

የቅርብ ዘመድ ባትሆንም፣ ረዳት የሌላትን ደካማ ሴት መርዳትና ማገዝ ልዩ ክብርና ደረጃ የሚሰጠው መሆኑን አጽንኦት ሰጥቶታል፡፡ እሷን ለመርዳትና ለማገዝ መሯሯጥ አላህ ዘንድ ትልቅ ክብር ያለው ተግባር መሆኑን በመግለጽ አነሳስቷል፡፡ ነብዩ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል፡- «ባሎቻቸው የሞቱባቸውን ሴቶችና የችግረኞችን ጉዳይ ለመፈፀም የሚሯሯጥ ሰው፣ ልክ በአላህ መንገድ ላይ ትግል እንደሚያደርግ፣ ሌሊት ተነስቶ ሳይ ታክት እንደሚሰግድና፤ ጾሞ እንደማያፈጥር ሰው ነው» (አልቡኻሪ 5661 / ሙስሊም 2982)

በኢስላም ልዩ ልዩ ክብርከተሰጣቸው ሴቶችመካከል እናት ዋናው ናት፡፡ ቡኻሪ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ <<አንድ ሰው ወደ ነቢዩ ዘንድ መጣና፣ አንተ የአላህ መልክተኛ ሆይ ከሰዎች ሁሉ በበለጠ ጓደኝነቱን ወይም ግንኙነቱን ልጠብቅለት የሚገባ ማን ነው? አላቸው፡፡ እሳቸውም፡ «እናትህ» አሉት፤ ከዚያስ? አላቸው፤ «ከዚያም እናትህ» አሉት፤ ከዚያስ? አላቸው፤ «አሁንም እናትህ» አሉት፡፡ ለአራተኛ ጊዜ፡ ከዚያስ? አላቸው፣ «ከዚያማ አባትህ ነው» አሉት፡፡» ብለዋል፡፡

ሴት ልጅ፡ ዑቅበቱ ኢብኑ ዓሚር ነቢዩ << እንዲህ ሲሉ ሰምቻለሁ ብለዋል፡ «ሦስት ሴት ልጆች ኖረውት፤ ስለ ነርሱ ትዕግስት አድርጎ፣ ጥሮ ግሮ ከላቡ ውጤት ያበላቸው፣ ያጠጣቸውና፣ ያለበሳቸው ሰው፣ የትንሳኤ ቀን ከእሳት ግርዶሽ ይሆኑለታል፡፡» (ኢብኑ ማጃህ 3669)

ሚስት፡ እመት ዓኢሻ ፣ ነቢዩ እንዲህ ማለታቸውን አስተላልፈዋል፡- «በላጫችሁ ለቤተሰቦቹ መልካም የሆነው ነው፡፡ እኔ ለቤተሰቦቼ መልካማችሁ ነኝ» (ቲርሚዚ 3895)

በኢስላም የወንድና የሴት ግንኙነት የመደጋገፊያ ግንኙነት ነው፡፡ እያንዳንዳቸው ሙስሊም ማህበረሰብን በመገንባት ላይ የሚዘጉት ክፍተት ወይም ቀዳዳ አላቸው፡፡

በሁለቱ ፆታዎች መካከል ሽኩቻ የሚፈጥር ነገር የለም፡፡

በአንዳንድ ያልሰለጠኑ ማህበረሰቡች ውስጥ እንደታየው፣ በወንድና በሴት መካከል የተደረጉት ሽኩቻዎች፣ በወንዱ በሴት ላይ ፈላጭ ቆራጭ መሆን፣ አለያም ደግሞ በሴቷ ከተፈጥሯዊ ባህሪ ማፈንገጥና ከአላህ ሕግጋት ውጭ መሆን ይጠናቀቃል፡፡

ይህ ደግሞ ከአላህ ሕግጋት ፍፁም በመራቅ እንጂ ሊከሰት አይችልም፡፡ አላህ እንዲህ ብሏል፡- «አላህም ከፊላችሁን በከፊላችሁ ላይ በርሱ ያበለጠበትን ጸጋ አትመኙ፤ ለወንዶች ከሰሩት ስራ ዕድል አላቸው፤ ለሴቶችም ከሰሩት ስራ ዕድል አላቸው፤ አላህንም ከችሮታው ለምኑት አላህ በነገሩ ሁሉ ዐዋቂ ነውና፡፡» (አልኒሳእ 32) በኢስላም ሁለቱም ፆታዎች እራሱን የቻለ ልዩ ተሰጥኦ፣ ኃላፊነትና ክብር አላቸው፡፡ ሁሉም የአላህን ችሮታና ውዴታ ለማግኘት ይጥራል፡፡ ኢስላማዊው ድንጋጌ፣ ለሙስሊም ማህበረሰብ ብሎም ለሰው ዘር በሙሉ እንጂ ለወንዶች ወይም ለሴቶች ሲባል የተደነገገ አይደለም፡፡ በኢስላም እይታ መሰረት፣ በሁለቱ ፆታዎች መሐከል ለሽኩቻ ቦታ የለውም፡፡ በዓለማዊ ጥቅም መፎካከር ትርጉም አልባ ነው፡፡ በሴቶች ላይ ማሴር ወይም በወንዶች ላይ ማመጽ የሚባል ነገር ጣዕም ወይም ስሜት አይኖረውም፡፡ አንዱ ሌላኛውን በቁጥጥሩ ስር ለማድረግ፣ ድክመቱን ችግሩንና ጉድለቱን ለማጋለጥ የሚካሄድ ሙከራ በኢስላም ቦታ የለውም፡፡ ይህ ሁሉ በአንድ በኩል ስንመለከተው ጫወታ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ኢስላምንና የሁለቱን ፆታዎች ትክክለኛ የስራ ዘርፍ አላግባብ ከመረዳት የመነጨም ነው፡፡ ሁላቸውም አላህን ከችሮታው ሊለምኑት ይገባል፡፡




# ወደ አላህ መጣራት

ያለው ቱሩፋት

ወደ አላህ መጣራት:-ማለት ሰዎችን ወደ ኢስላም እንዲ
ገቡ ጥሪ ማድረግ ነው፡፡ ስለ ዚህ ጉዳይ አላህ በተከበረው
ቁርኣኑ እንዲህ አለ፡-(መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ !
ይህ መንገዴ ነው፡፡ ወደ አላህ እጠራለሁ፡፡ እኔም የተከተለ
ኝም ሰው በግልጽ ማስረጃ ላይ ነን፡፡ ጥራትም ለአላህ ብቻ
ይገባው፡፡ እኔም ከአጋሪዎች አይደለሁም በል) ዩሱፍ 108.

ወደ አላህ መጣራት በይኑ

ወደ አላህ መጣራት ብይኑን በሙስሊሞች ላይ የተጣለ
ግዴታ ነው፡፡ ሁሉም እንዳቅሙ በሚችለው ወደ አላህ
በሚደረገው ጥረት ላይ ተሳትፎ ግድ ነው፡፡ ደዕዋ ሰዎችን
ወደ ኸይር መጥራት ከመጥፎ ነገር መከለከል ማለት ነው፡
፡ እነዚህ ሁለት ጉዳዮች ከመከበዳቸው የተነሳ አንዳንድ
ዐሊሞች ዘንድ ስደስተኛው የኢስላም ማዕዘን እስከመ
ባል ደርሰዋል፡፡ አላህም ማህብረሰቡ ሊተገብረው የሚገባ
ጉዳይ እንደሆነ እንዲህ በማለት አዞናል፡፡ (አማኞች ሆይ !
ከእናንተ መካከል ወደ በጎ ነገር  የሚጠሩና በመልካም ስራ
የሚያዙ ከከፉ ነገር የሚከለክሉ ከፊሎች ቡድኖች ይኑሩ፡፡
እነዚያ ከእሳት የሚድኑ እነሱ ብቻ ናቸው፡፡ አማኞች ሆይ
! እንደነዚያ ግልፅ ተዐምራት ከመጣላቸው በኋላ እንደ ተለ
ያዩትና እንደተጨቃጨቁት የመፅሐፍ  ሰዎች አትሁኑ፡፡እነ
ዚያም ለነርሱ ታላቅ ቅጣት አለባቸው)ኣሊ-ኢምራን 104፣
ወደ አላህ መጣራት በኢስላም ትልቅ አጅር የሚያስገኝ ከተ
ተዎም በከፍተኛ ጥፋት የሚያስጠይቅ ሃይማኖታዊ ተግባር
ነው፡፡ ቁርኣን ስለ መፅሐፍት ሰዎች ሲናገር እንዲህ ብሏል፡
፡ (የመጽሐፍ ባለቤቶች ሁሉ በእምነት እኩል አይደሉም፡፡
ከመፅሐፍ ባለቤቶች መካከል ቀጥ ያሉና በሌሊት ሰዓቶች
እየሰገዱ የአላህን አንቀፆች የሚያነቡ ሕዝቦች አሉና፡፡ በአላ
ህና በመጨረሻውም ቀን ያምናሉ፡፡ በፅድቅም ነገር ያዛሉ፡
፡ ከመጥፎ ነገርም ይከለክላሉ፡፡ ለበጎ ስራዎችም ይጣደ
ፋሉ፡፡ እነርሱ ከደጋግ ሰዎች ናቸው፡፡ ከበጎ ስራ ሰሪዎች

መካከል ማንኛውንም በጎ ስራ ቢሰሩ አይካዱትም ውድቅ አይደረግባቸውም፡፡ አላህ ጥንቁቆቹን ሁሉ አዋቂ ነውና፡፡ ) ኣሊ-ኢምራን 113-115›

## ወደ አላህ መጣራት የሚጀምረው

ወደ አላህ መጣራት የሚጀምረው ወደ አላህ መጣራት የሚ ጀምረው ነቢዩ (ﷺ) ከጀመሩበት ከተውሒድ ነው፡፡ ነቢዩ ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ እንዲህ አሉ፡-(ዑመር እንዲህ አሉ፡-‹‹ከዕለታት አንድ ቀን ከመልዕክተኛው ጋር በተቀመ ጥንበት ወቅት አንድ በጣም ነጭ የሆነ ልብስ የለበሰ፣ ፀጉሩ በጣም የጠቆረ፣ የጉዞ ምልክት የማይታይበት፣ ከእኛም ውስጥ ማንም የማያውቀው ሰው ብቅአለ፡፡ ጉልበቱንም (ከነብዩ) ጉልበት ጋር አሳክቶ ተቀመጠ፡፡ መዳፎቹን ደግሞ ታፋዎቹ ላይ አደረገ፡፡ ‹‹ሙሐመድ ሆይ ! ስለ ኢስላም ንገረኝ›› አለ፡፡የአላህመልዕክተኛም ‹‹ኢስላም ከአላህ ሌላ አምላክ እንደሌለና ሙሀመድም የአላህ መልዕክተኛ መሆ ናቸውን መመስከር፣ስላትን አስተካክሎ መስገድ፣ የግዴታ ምፅዋት (ዘካ) መስጠት፣ የረመዷንን ወር መጾም፣ ከተቻለ የአላህን ቤት፣ መጎብኘት ነው›› በማለት መለሱለት፡፡ (ጠያ ቂውም) ‹‹እውነትህን ነው›› አለ፡፡ እኛም በሰውዬው ድር ጊትተገረምን፡፡ ራሱይጠይቃል፤እንደገና በትክክል ነው የተ ናገርከው ይላል፡፡በመቀጠልም ‹‹ስለኢማንንገረኝ›› አለ፡ ፡ ‹‹በአላህ፣ በመላዕከቱ፣በቅዱሳን መጻሕፍቱ፣ በመልዕክ ተኞቹ በመጨረሻውቀንና በቀደር ጥሩም ቢሆን መጥፎ ማመን ነው›› አሉት ‹‹እውነትህን ነው›› አለናደግ ‹‹ስለኢ ሕሳንንገረኝ›› አላቸው ‹‹አላህን እንደምታየው አድርገህ ልትገዛ ነው፡፡ አንተ ባታየው እርሱ ያይሀልና›› አሉት ‹‹ስለ ጊዜዋ (የፍርዷቀን) ንገረኝ›› አላቸው ‹‹ተጠያቂው ከጠያ ቂው የበለጠ ዕውቀት የለውም›› አሉት፡፡እሺ ስለምልክቶቿ ንገረኝ›› አለ፡፡ ‹‹ባሪያ ሴት ጌታዋን (እመቤቷን) ትወልዳ ለች፤ ጫማ የሌላቸው፣ የታረዙ፣ ድሆችና እረኞች (የነበሩ) ታላላቅ ህንፃዎችን ለመገንባት ሲፎካከሩ ታያለህ›› አሉት፡ ፡ ከዚያ (ጠያቂው) ሄደ፡፡ እኔ ጥቂት ጊዜ ከቆየሁ በኋላ ‹‹አንተ ዑመር ጠያቂው ማን እንደሆነ አውቀሀልን ? ሲሉኝ ‹‹አላህና መልዕክተኛው ያውቃሉ›› አልኳቸው፡፡ ‹‹እርሱ ጅብሪል ነው፤ የመጣውም ሃይማኖታችሁን ሊያስተምራ ችሁ ነው›› በማለት መለሱልኝ)) ብለዋል፡፡

## ወደ አላህ መጣራት አላማው

ወደ አላህ መጣራት ብዙ አላማዎች ያሉት ሲሆን ከብዙ በጥቂቱ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትበዋነኝነት ይገኙበታል፡፡

1-የአላህን ዉዴታ ማግኜት ነው፡፡ አላህ እንዲህ አለ (የም ናበላችሁ ለአላህ ውዴታ ብቻ ብለን ነው፡፡ከእናንተ ክፍያ ንም ሆነ ማመስገንን አንፈልግም) አል-ኢንሳን 9.

2-ኢስላምን በምድር ላይ ለማሰራጨት ነው፡፡ አላህ እንዲህ አለ፡- (ከሃዲያን የአላህን ብርሃን በአፎቻቸው ለማ ጥፋት ይፈልጋሉ፡፡ አላህ ከሓዲያን ቢጠሉም እንኳ ብርሃ ኑን መሙላትን እንጂ ሌላን አይሻም ፡፡ አላህ ያ ! ኢጋሪዎቹ ቢጠሉም መልዕክተኛውን ሙሐመድን በቅን መንገድና በእ ውነተኛ ሃይማኖት ላይ ከሃይማኖት ሁሉ በላይ ይፋ ያደ ርገው ዘንድ የላከ ብቸኛ አምላክ ነው>> አት-ተውበህ ፡ 32-33.

3-የሰዎችን እምነት በማስተካከል ላይ የሚያተኩር በመሆኑ ነው፡፡ አላህ እንዲህ አለ፡-<<መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ! ከአንተ በፊትም፤ እነሆ ከእኔ ሌላ አምላክ የለምና ተገዙኝ በማለት ወደ እርሱ የምና ወርድለት ቢሆን እንጅ ከመልዕክተኛ አንድንም አላክንም>> አል አንቢያእ 25.

ነቢዩም ሙሐመድ (ﷺ) ለሙዓዝ (በመፅሐፍ ወደሚያ ምኑ ህዝቦች ነው የምትሄደው እነሱ ጋር ስትደርስ በመጀ መሪያ ወደ ሸኃደትይን ጥሪ አድርግላቸው፡፡ እሱን ከተቀበ ሉህ የአምስቱን ሶላቶች ግዴታነት ንገራቸው፡፡ እሱን ከተ ቀበሉህ ከባለሀብቶቻቸው ተወስዶ ለድሆቻቸው የሚሰጥ የዘካን ግዴታ ንገራቸው፡፡...) በማለት የደነገገውን ቅደም ተከተል አስተምራዋል፡፡

## ወደ አላህ መጣራት ያለው ትሩፋት

በኢስላም ዉስጥ ዋና ዋና ጉዳዮች ከሚባሉት መካከል ሰዎችን ወደ ኸይር መጥራት ለእሱ ማግባባት ከመጥፎ

ነገሮች ደግሞ መከልከል ማስፋራራት ማስጠንቀቅ ነው:: እናም የነቢ ኡመቶች ዋና ስስራቸው ይህ እንደሆነ ቁርኣን በይፋ አዉጇል:: አላህ እንዲህ አለ:-(ሙስሊሞች ሆይ ! ለሰው ልጆች ጥቅም (አገልግሎት) ከተገለጹት ሕዝቦች ሁሉ በላጭ ሆናችሁ :: ይኸውም መልካም ነገር ታዛላችሁ :: ከመጥፎም ነገር ትከለክላላችሁ :: በአላህም አንድነት ታምናላችሁና ነው :: የመጽሐፍ ሰዎችም ልክ እንደናንተ ባመኑ ኑሮ ለእነርሱ የተሻለ በሆነ ነበር:: ጥቂትም ቢሆኑ ትክክለኛ ከእነርሱ መካከል አማኞች አሉ :: አብዛሀኞቻቸው ግን አመፀኞች ናቸው::ኣሊ-ኢምራን110፣ ይህን እውነታ የሚያመለክቱ ብዙ መረጃዎች አሉ:: ቁርኣን ስለ መፅሐፍት ሰዎች ሲናገር እንዲህ ከብዙ በጥቂቱ:-

1-የታላቁ ነቢይ የነቢዩ ሙሐመድ ተግባርና ዉርስ በመሆኑ፤ አላህ እንዲህ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! ከጌታህ ወደ አንተ የተወረደውን ቁርኣን አድርስ::ይህን ባትሰራ ግን የጌታህን መልዕክቱን አላደርስክም:: አላህ ከሰዎች ተንኮል ሁሉ ይጠብቅሃልና:: አላህ ከሐዲያን ሕዝቦችን አያቀናምና ) አል ማኢህ 67.

2-አላህ በዚህ ስራ ላይ የተሰማሩትን እንዲህ ሲል በማሞገሱ:: (ወደ አላህ ከጠራና መልካምን ከሰራና እኔ ከሙስሊሞች ነኝ ካለ ሰው ይበልጥ ቃሉ ያማረ ማን ነው ?) ፉሲለት 33.

3-ይህን የሚተገብር ሁሉ የነቢዩ ጓደኛና ኣጋር መሆኑ በቁርኣን በመመስከሩ፤ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! ይህ መንገዴ ነው:: ወደ አላህ እጠራለሁ:: እኔም የተከተለኝም ሰው በግልጽ ማስረጃ ላይ ነን:: ጥራትም ለአላህ ይገባው:: እኔም ከአጋሪዎች አይደለሁም በል) ዩሱፍ 108.

4- ነቢዩም (r) እንዲህ ብለዋል:: (ወደ ቀና መንገድ የጠራ ሰው ሁሉ በቀናው መንገድ የተከተሉት ሰዎች ምንዳ ያክል አለው::ከእነሱም ምንም አይቀነስም) በማለት ከሰደቃዎች ሁሉ ትልቁ መሆኑን ስለመሰከሩ ይህ ተግባር ከፍ ያለ ምንዳ ካላቸው ስራዎችና ወደ አላህ ከሚያቃርቡ ቅዱስ ተግባሮች ላቅ ያለው ነው::

## የትክክለኛው ኢስላማዊ ጥሪ መገለጫ ባህሪያት

1-መረጃና ዕውቀት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ (መልዕክተኛችን ሙሐመድሆይ ! ይህ መንገዴ ነው:: ወደ አላህ እጠራለሁ:: እኔም የተከተለኝም ሰው በግልጽ ማስረጃ ላይ ነን:: ጥራትም ለአላህ ይገባው:: እኔም ከአጋሪዎች አይደለሁም በል)ዩሱፍ108

2-በብልሃትና በጥበብ የተሞላ በመሆኑ አላህ እንዲህ አለ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! ወደ ጌታህ መንገድ በብልሃትና በመልካም ግሳጼ በለዘብተኛ ቃል ሰዎችን ጥራ:: በዚያችም እርሷ በመልካም በሆነችው ዘዴ ተከራከራቸው:: ጌታህ ከመንገዱ የተሳሳተውን ሰው ዐዋቂ ነው:: እንደዚሁም እርሱ ቅን የሆኑትን ሰዎች ዐዋቂ ነው) አል-ነህል125.

እንዲህም አለ <<መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! በአላህ ችሮታ ለዘብክላቸው::አመለመጥፎና ልበደረቅ በሆንክ ኖሮ ከአጠገብህ በተበተኑ ነበር:: ከእነርሱም ጥፋትን ይቅር በል:: ለእነርሱም ከአላህ ምህረትን ለምንላቸው:: በሁሉም ነገር ላይ አማክራቸው:: ከዚያም ቁርጥ ሀሳብ ባደረገ ጊዜ በአላህ ላይ ብቻ ተመካ:: አላህ በእርሱ ላይ ብቻ ተመኪዎችን ይወዳልና::ኣሊዒምራን159.





እንዲህም አለ <<መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! ቤተሰብህን በሶላት ላይ እዘዝ፡፡ አንተም በእርሷ ላይ ዘውትር፡፡ ሲሳይን አንጠይቅህም፡፡ እኛ እንሰጥሃለን፡፡ መልካሚቱ መጨረሻ ለጥንቁቆች ሁሉ ናት) ጡሃ132 .

እንዲህም አለ (አንተ የወደድከውን ሰው ፈጽሞ አታቀናም፤ ግን አላህ የሚሻውን ሰው ያቀናል እርሱም ቅኖዎችን ዐዋቂ ነው፡፡ ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሙሰይብ እንዳስተላለፉት፤ የአላህ መልዕክተኛ (r) «አቡጣሊብ ለሞት እየተቃረቡ ባለበትና አቡጀህል ከሳቸው ጋር እያለ ነብዩ ወደ እርሳቸው ገብተው «አጎቴ ሆይ! ከአላህ በስተቀር አምልኮ የሚገባው ጌታ የለም የምትለውንና አላህ ዘንድ የምከራከርበትን ቃል በልልኝ» አሉ፡፡ አቡጀህልና ዐብደላህ ኢብኑ አቡ ኡመይያህ በተደጋጋሚ «አቡ ጧሊብ ሆይ ! የዐብዱልሙጧሊብን ሃይማኖት ለመተው ትፈልጋለህን ?» ይሏቸው ነበር፡፡ ከመሞታቸው በፊት ያሏቸው ነገር ቢኖር «በዐብዱልሙጠሊብ ሃይማኖት ላይ ነኝ» የሚል ነበር፡፡ ነብዩም «ምንም የተከለከልኩ ቢሆንም ላንተ ምህረትን እጠይቅልሃለሁ» አሉ፡፡ በዚህም ሳቢያ «ለነብዩና ለነዚያ ላመኑት ለአጋሪዎቹ የዝምድና ባለቤቶች ቢሆኑም እንኳ እነሱ ከሓዲያን የእሳት ጓዶች መሆናቸው ከተገለፀላቸው በኋላ ምህረትን ሊለምኑ የሚገባ አልነበረም» አት-ተውባህ፡፡ አንተ የወደድከውን ሰው ፈፅሞ አታቀናም፤ ግን አላህ ...» (አል-ቀሰስ 56) የሚለውን አንቀፅ አወረደ፡፡ ወደ አላህ የሚጠራ ሰው የሚጠራበትን ነገር በራሱም ላይ ሆነ በቤተሰቡ ላይ የተገበረው መሆን አለበት፡፡ በአጠቃላይ ወደ አላህ መጣራት የሙስሊሞች ዋነ ባህሪ እንዲሆን ይፈለጋል፡፡

አላህ እንዲህም አለ (....አላህ ሰዎችን ከፊላቸውን በከፊሉ መገፍተሩ ባልነበረ ኖሮ ገዳማት ቤተክርስቲያኖች ምኩራቦችና በውስጣቸው የአላህ ስም በብዛት የሚወሳባቸው መስጊዶች በተፈረሱ ነበር ፡፡ አላህ ሃይማኖቱን የሚረዳውን ሰው ሁሉ በእርግጥ ይረዳዋል ፡፡ አላህ ብርቱና አሸናፊ ነውና ፡፡ እነርሱ ማለት እነዚያ በምድር ላይ ብናስመቻቸው (የበላይነትን ሰጥተን ባጎናፀፍናቸው ኖሮ) ሶላትን እንደሚገባ የሚያስተካክሉ፤ ዘካንም የሚሰጡ፤ በደግ ነገርም የሚያዝዙ፤ ከመጥፎ ነገር የሚከለከሉ ናቸው ፡፡ የነገሮች ሁሉ መጨረሻ ወደ አላህ ብቻ ነው ፡፡ ስለ ዚህ ወደ አላህ ጥሪ የሚያደርግ ሁሉ፡-

1-ለሚጠራበት በቂ እውቀት ሊኖረው ግድ ይላል፤

2-የማስተማር ዘዴዎችን መላበስ ያስፈልገዋል፤

3-በዋና በዋና ጉዳዮች መጀመር ተገቢ ነው፤

4-.ከቤተሰቡ መጀመር ይኖርበታል፤

5-የሚጠራበትን ነገር በራሱም ሆነ በቤተሰቡ መተግበር ነው፤

6-እንደሌሎች የአምልኮ ተግባራት ሁሉ ኢኽላስ ሊኖረው ነው፡፡




# ነቢዩ ሙሐመድን ﷺ መውደድ ግዴታነት



ነቢዩ ሙሐመድ ﷺ እ.ደ ኢ.አ.በ570 ላይ በመካ ተወልደው በየቲምነት አደጉ፡፡ በመጀመሪያ ከእናታቸው ከአሚና ጋር፤ ከዚያም ኩጡት እናታቸው ከሐሊማ ጋር፤ ከዚያም ለሁለተኛ ጊዜ ከእናታቸው ከአሚና ጋር፤ ከዚያም ከአያታቸው ከዐብዱል ሙጦሊብ ጋር፤ ከዚያም ከአጎታቸው ከአቡ ፃሊብ ጋር አደጉ፡፡ እያደጉ ሲሔዱ በመልካም ስነ ምግባሮች በተለይም በታማኝነት በማህበረሰቡ ዘንድ እውቅናን አገኙ፡፡ ከእነ ስያሚያቸው ሙሐመድ አል አሚን በመባል ይታወቁ ነበር፡፡ በዚህ ላይ እያሉ አርባ አመታቸው ሲደርስ ነቢይ ሆኑ፡፡ ከዚያም ኢስላምን ማስተማር ሲጀምሩ እርሳቸዉም ሆኑ ተከታዮቸቻቸው ለስቃይና ለእርዛት ተዳረጉ፡፡ እ.ደ ኢ.አ. በ615 አካባቢ በጣም ስቃዩ የበዛባቸው አማኞች ወደ ሐገራችን ሐበሻ ተሰደዱ፡፡ መከራው ከቀን ወደ ቀን እየተባባሰ በመሄዱ እ.ኢ.አ.በ622 በአላህ ትእዛዝ ወደ መዲና ተሰደዱ፡፡ በሃያ ሶስት አመት ዉስጥ አብዛኛው የዐረቢያ ግዛቶች ኢስላምን ተቀበሉ፡፡ ቁርአንም በእነዚሁ አመታት ዉስጥ እንደሁኔታው ወርዶ አበቃ፡፡ ስልሳ ሶስት አመታቸው ላይም ከዘህች ዐለም በሞት ተለዩ፡፡ በዚህ አጭር ፁሑፍም ስለ እሳቸው ብዙ ለማውራት ታስቦ ሳይሆን እሳቸዉን መውደድ በኢስላም የጠሰጠው ቦታና የመውደዳችን ምልክቶችን መጠቆም ነው፡፡

፩-ነቢዩ ሙሐመድን ከራሳችን፤ ከልጆቻችን፤ ከወላጆቻችን፤ ከቤተሰቦቻችን፤ ከንብረቶቻችንና ከሁሉ ነገር በላይ አብልጦ መውደድ ግዴታ ነው፡፡ ምክኒያቱም በቁርአን ከተደነገጉት ዋናዋና ጉዳች መካከል ነቢዩን መውደድ ነው፡፡ የዚህም ፁሑፍ ዋና አላማው ይህንኑ ጉዳይ ማስተማር ነው፡፡ ስለዚህ ጉዳይ አላህ እንዲህ አለ፡-(ከሰዎች መካከል ከአላህ ሌላ ባላንጣዎችን/ ጣዖታትን/ አላህን እንደሚወዱ የሚወዷቸው ሆነው የሚይዙ አሉ፡፡ እነዚያ ያመኑትም አላህን ከምንም በላይ ይወዳሉ፡፡ እነዚያም የበደሉት ሰዎች ቅጣትን በትንሳኤ ቀን ባዩ ጊዜ ሀይል ሁሉ በአላህ ብቻ

መሆኑንና አላህም ቅጣቱ ብርቱ እንደሆነ ይገነዘባሉ» አል በቀራህ 165.

እንዲህም አለ፡-( መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! አባቶቻችሁ፣ ወንዶች ልጆቻችሁ፣ ወንድሞቻችሁ፣ ሚስቶቻችሁ ዘመዶቻችሁ፣ የሰበሰባችኋቸው ሀብቶች፣ መክሰሯን የምትፈሯት ንግድና የምትወዷቸው መኖሪያዎች በእናንተ ዘንድ ከአላህ፤ ከመልዕክተኛውና በእርሱ መንገድ ከመታገል ይበልጥ የተወደዱ ከሆኑ አላህ ቅጣቱን እስከሚያመጣ ድረስ ተጠባበቁ በላቸው፡፡ አላህ አመፀኞች ህዝቦችን አይመራም) አት ተውበህ 23-24. እራሳቸው ነቢዩም እንዲህ አሉ፡-(ሶስት ነገሮችን በዉስጡ ያገኜ ሰው የእምነትን ጠዐም በትክክል አገኚቷል፡፡ በእሱ ዘንድ አላህና መልዕክተኛው ከሁሉ ነገር የተወደዱ መሆን፤ሰዎን ሲወድ ለአላህ ብሎ መውደድ፤ ከኢስላም ወደ ክህደት መሄድን እሳት ላይ እንደመጣል አድርጎ መቁጠር ናቸው)ብለዋል፡፡ ቡኻሪና ሙስሊም.

በተመሳሳይም አንድ ቀን ዑመር ያአላህ መልዕክተኛ እርሰዎ እኮ እኔ ዘንድ ከራሴ በመቀጠል እውደዎታለሁ ሲሏቸው ይሆንም ሕይወቴ በእጁ በሆነቺው ጌታ አላህ ይሁንብኝ ከራስህም እስከምታበልጠኝ ድረስ አላቸው ዑመርም መልሰው አሁን ከራሴም የበለጠ እወደወታለሁ ሲሏቸው አሁን ነው ዑመር አሏቸው.»ቡኻሪ.

2-በፍቅርም ቢሆን ከልክ በላይ ማጋነን ክልክል ነው፡፡ ማጋነን ማለት ወሰንን ማለፍ፤ ከሚገባው በላይ ማዕረግ መስጠት ማለት ነው፡፡ ነብዩ ሙሐመድ ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ «ክርስቲያኖች የመርየምን ልጅ ዒሳን ከተገቢው በላይ እንዳጋነኑት ሁሉ እኔንም ከተገቢው በላይ አታጋኑኝ፡፡ እኔ የአላህ አገልጋይ ብቻ ነኝ፡፡ እናም «የአላህ አገልጋዩና መልዕክተኛው በሉኝ» ብለዋል፡፡ እንደዚሁም አህመድበዘገቡት ሐዲስ (ማጋነንን ተጠንቀቁ፡፡ ከእናንተ በፊት የነበሩ ህዝቦችን ለጥፋት የዳረጋቸው አጉል ማጋነን ነበርና» ብለዋል፡፡

3-ያለወደዳቸዉን ሁሉ አላህ ዝቶባቸዋል፡፡ ቁርኣን እንዲህ አለ፡-(መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ! አባቶቻችሁ፣ወንዶች ልጆቻችሁ፣ ወንድሞቻችሁ፣ ሚስቶቻችሁ ዘመዶቻችሁ፣ የሰበሰባችኋቸው ሀብቶች፣ መክሰሯን የምትፈሯት ንግድና....፡፡) አትተውበህ24.

4-የነብዩን ማእረግ በተገቢው መግለፅ ተገቢ ነው፡፡ አላህ እንዲህ አለ፡-(መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ! ከሌሊት ለአንተ ተጨማሪ የሆነችን ሶላት በቁርአን ስገድ፡፡ ጌታህ ምስጉን በሆነ ስፍራ በእርግጥ ያቆምሃል፡፡ መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! በልም ጌታዬ ሆይ ! የተወደደን መግባት አስገባኝ የተወደደንም መውጣት አስወጣኝ፡፡ ለእኔም ከአንተ ዘንድ የተረዳን ስልጣን አድርግልኝ፡፡ መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! በልም እውነት መጣ ውሸትም ተወገደ እነሆ ውሸት ተወጋጅ ነውና»አል ኢስራ 79.

እንዲህም አለ፡-(እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሆይ ! ድምፆቻችሁን ከነብዩ ድምፅ በላይ ከፍ አታድርጉ፡፡ ከፊላችሁ ለከፊሉ እንደሚጮህም ሁሉ በንግግር ለርሱ ስትናገሩ አትጩሁ፡፡ እናንተ የማታውቁ ስትሆኑ ስራዎቻችሁ እንዳይበላሹ ከዚህ ተከላከሉ፡፡ እነዚያ በአላህ መልዕክተኛ ዘንድ ድምፆቻቸውን ዝቅ የሚያደርጉ እነዚያ አላህ ልቦቻቸውን ለፍርሃት የፈተናቸው ናቸው፡፡ ለእነርሱም ምህረትና ታላቅ ምንዳ አለላቸው፡፡ መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! እነዚያ ከመኗሪያ ክፍሎቹህ ውጭ ሆነው የሚጠሩህ አብዛሀኞቻቸው አያውቁም፡፡ ወደ እነርሱም እስክትወጣ ድረስ ዝምብለው በታገሱ ኖሮ ለእነርሱ በላጭ በጎ ተግባር በሆነ ነበር፡፡ አላህም እጅግ መሀሪና አዛኝ ነውና»49-2-5

«አማኞች ሆይ ! በመካከላችሁ የመልዕክተኛውን ጥሪ ከፊላችሁ ከፊሉን እንደመጥራት አታድርጉት፡፡ ከእናንተ ውስጥ እነዚያን እየተከለሉ በመሽሎክሎክ የሚወጡትን አላህ በእርግጥ ያውቃቸዋል፡፡ እነዚያም ትእዛዙን የሚጥሱ ሁሉ መከራ እንዳትደርስባቸው ወይም አሳማሚ ቅጣት እንዳያገኛቸው ይጠንቀቁ »አልኑር 63.

እንዲህም አለ:-«አላህና መላዕክት በነብዩ ላይ የአክብሮት እዝነትን ያወርዳሉ፡፡ እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ ! በእርሱ ላይ የአክብሮት እዝነትን አውርዱ፡፡ የማክበርን ሰላምታንም ሰላም በሉ» አል-አህዛብ 56.

4-ለነብዩ ሶለዋት መለመን ከፍተኛ ምንዳ አለው፡፡ ከብዙ በጥቂቱ

4-1-ቁርኣን እንዲህ ብሏል፡፡ (አላህና መላዕክት በነብዩ ላይ የአክብሮት እዝነትን ያወርዳሉ፡፡ እናንተ በአላህ ያመናችሁ ሰዎች ሆይ ! በእርሱ ላይ የአክብሮት እዝነትን አውርዱ፡፡ የማክበርን ሰላምታንም ሰላም በሉ ፡፡) 33፡56.

4-2-ቡኻሪ በዘገቡት ሐዲስ ዐብዱረህማ ኢብኑ አቡ ለይላ እንዳስተላለፉት፣ ከዕብ ኢብኑ ዑጅራህ አገኘኝና «ከነብዩ ሙሐመድ (ﷺ) የሰማሁትን አንድ ስጦታ ልስጥህ ?» አለኝ፡፡ እኔም «እንዴታ!» አልኩት፡፡ እሱም «የአላህ መልዕክተኛ በእርሰዎ ላይ ሰላምታ እንዴት እንደምናቀርብ አላህ አስተምሮናል፡፡ ታዲያ በእርስዎ ቤተሰነብ ላይ እንዴት ነው ሰላምታ የምናቀርበው ? ስንል ጠየቅናቸው፡፡ እሳቸውም «ጌታችን ሆይ ! በኢብራሂምና በኢብራሂም ቤተሰቦች ላይ እዝነትን እንዳወረድከው በሙሐመድና በሙሐመድ ቤተሰቦች ላይ እዝነትን አውርድ፡፡ አንተ በእርግጥ እጅጉን የተመሰገንክና የላቅክ ነህ፡፡ አሉን፡፡»

4-3-ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ዐብደላህ ኢብኑ ዐምር ብን አልዓስ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) ተከታዩን ሲናሩ ሰምቻለሁ በማለት አስተላልፈዋል:-«በኔ ላይ አንድ ጊዜ ያወረደ አላህ በርሱ ላይ አስር ሶላቶችን ያወርድለታል፡፡»

4-4-ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ ኢብኑ መስዑድ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል:-«በዕለተ ቂያማ ለኔ ይበልጥ የተገባው ሰው በኔ ላይ አብዝቶ ሶላት ያወረደ ነው»

4-5-አቡዳውድ በዘገቡት ሐዲስ አውስ ኢብኑ አውስ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ «ከቀኖቻችሁ ሁሉ በላጩ የጁመዓ ቀን ነው፡፡ ጁመዓ ቀን በኔ ላይ ሶላት አብዙ፡፡ ሶላዋቶቻችሁ ይቀርቡናል» አሉ፡፡ ባልደረቦቻቸውም:-«የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! አካሎዎ በአፈር ተብልቶ እያለ እንዴት ነው የኛ ሶላዋት የሚቀርብዎ» በማለት ጠየቋቸው፡፡ እርሳቸውም:-«በምድር የነብያትን አካል እንዳትበላ አላህ ከልክሏል» አሉ፡፡

4-6-ቲርሚዚ በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:-«ከአጠገቡ ተወስቼ በኔ ላይ ሶለዋት ያላዋረደ ሰው ከሰረ»

4-7-ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሁረይራ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ ብለዋል:-«ለኔ ሰላምታ የሚያቀርብልኝ አንድም ሰው የለም አላህ ነፍሴን በመመለስ ለሰላምታው ምላሽ እንደሰጥ የሚያደርገኝ ቢሆን እንጂ»

4-8-ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ ዐሊይ እንዳስተላለፉት የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) እንዲህ ብለዋል:-«ስስታም ማለት ከአጠገቡ ተወስቼ በኔ ላይ ሶለዋት ያላወረደ ነው፡፡»

4-9-ቡኻሪና ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አቡ ሙሐመድ ከዕብ ኢብኑ ዑጀረህ እንዳስተላለፉት:-ነብዩ ወደኛ መጡ፡ ፡ «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ! ለርስዎ እንዴት ሰላምታ ማቅረብ እንዳለብን አወቅን፡፡ ሶለዋት የምናወርደውስ እንዴት ነው?» በማለት ጠየቅናቸውና እንዲህ እንድል አስተማሩን:-«አልላሁምመ ሶልሊ ዐላ ሙሐምመዲን ወዐላ አሊ ሙሐምመደን ከማ ሶልለይተ ዐላ አሊ ኢብራሂይመ ኢንነከ ሐሚይዱን መጂይድ፡፡ አልላሁምመ ባሪክ ዐላ ሙሐመዲን ወዐላ አሊ ሙሐመዲን ከማ ባረክተ ዐላ አሊ ኢብራሂመ ኢንነከ ሐሚይዱን መጂይድ፡፡

4-10--ሙስሊም በዘገቡት ሐዲስ አቡ መስዑድ አል-አድሪይ እንዲህ ሲሉ አስተላለፈዋል:-ከሰዕድ ኢብኑ ዐብደላህ ዘንድ ተቀምጠን እያለ የአላህ መልዕክተኛ (ﷺ) መጡ፡ ፡ «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ ! አላህ በርስዎ ላይ ሰለዋት እንድናወርድ አዞናል፡፡ እንዴት ነው የምናወርደው?» ሲል በሺር እብን ሰዕድ ጠየቃቸው፡፡ ባልጠየቃቸው ብለን እስከምንመኝ ድረስ ዝም አሉ፡፡ ከዚያም እንዲህ አሉ፡፡ «አልላሁምም ሶልሊ ዐላ ሙሐምመዲን ወዐላ አሊ ሙሐመ

ዲን ከማ ሶልለዬተ ዐላ አሊ ኢብራሂይመ እንነከ ሐሚይ ዱን መጂይድ፤ በሉ፡፡ ሰላምታ እንዴት እንደምታቀርቡልኝ ታውቃላችሁ»

4-11-አቡ ሑመይድ አስ-ሰዒዳይ እንዳስተላፉት «የአላህ መልዕክተኛ ሆይ! በርስዎ ላይ ሰለዋት የምናወርደው እንዴት ነው በማለት ሰዎች ጠየቋቸው፡፡ እርሳቸውም እንዲህ እንዲሉ አስተማሯቸው፡-«አልሏሁምም ሶልሊ ዐላ ሙሐምመዲን ወዐላ አዝዋጂሂ ወዙሪይየቲሂ ከማ ሶልለ ይተ ዐላ አሊ ኢብራሂይመ ወባረክ ዐላ ሙሐምመድን ወዐላ አዝዋጂሂ ወዙሪይየቲሂ ከማ ባረከተ በላ አሊ ኢብራ ሂይመ እንነከ ሐሚይዱን መጂይድ» በመሆኑም ሶለዋት መለመን ሁልዜም ተፈላጊ ቢሆንም ጁሙዓ ቀንና ሌሊቱ ላይ በጣም ይወደዳል፡፡ ስማቸው በተወሳ ቁጥርም እንዲሁ ይወደዳል፡፡ አነጦሓዊና ሌሎችም ስማቸው በተወሳ ቁጥር ግዴታ ነው) ብለዋል፡፡ በየሶላቱ በመጨ ረሳው ተሸሁድ ላይ፣ በጁሙዓና በዒድ ኹጥባ ዉስጥ ግዴታ ነው የሚሉት ብዙ ናቸው፡፡ ኢብኑል ቀይም ጂላኡል አፍሃም በተባለው መፅሐፍ ሶለዋት መለመን አርባ ቦታ ላይ ይገባል ብለው አርባዉን ሁሉ ዘርዝረው ታል፡፡ ከፋይዳዎችም አርባ ጥቅሞችን ዘርዝረዋል፡፡ አላህ እንዲህ አለ «መኮች ሆይ ! ባልደረባችሁ ሙሐመድ ሐቅን አልሳተም። ከእውነትም አላፈነገጠም። ኮከቡ በጠለቀ ጊዜ እምላለሁ፡፡ ከልብ ወለድ ስሜቱም አይናገርም፡፡ ቁርኣን ከአላህ የተወረደ እንጂ ሌላ አይደለም፡፡ ሀይለ ብርቱ የሆነው መልዐክ ጂብሪል አስተማረው፡፡ የእውቀት ባለቤት የሆነው፡፡ ከዚያም በላይኛው አድማስ ላይ ሆኖ ተመቻቸ፡፡ ከዚያም መልዐኩ ጂብሪል ነብዩን ቀረበው፡፡ ከዚያም በጣም ተጠጋው፡፡ ከዚያም የሁለት ደጋን ጫፎች ያህል ወይም ከዚያም ባነሰ ርቀት ላይ ሆነም፡፡ እናም አላህ ለአ ገልጋዩ ለሙሐመድ ማውረድ/መግለፅ/ የሻውን አወረደ/ ገለፀ/፡፡ ያየውን ነገር ሁሉ ልቦናው አላስተባበለውም፡፡ ታዲያ ባየው ጉዳይ ላይ ትከራከሩታላችሁን ?

እንዲህም አለ፡- (እናንተ ሰዎች ሆይ ! መልዕክተኛው እውነ ትን ከጌታችሁ አመጣላችሁ፡፡ እናም እመኑም፡፡ በሱ ማመ ናችሁ ለእናንተ የተሻለ ይሆናል፡፡ በአላህ ብትክዱም እሱን ቅንጣት ያክል አትጎዱትም፡፡ በሰማያትና በምድር ያለው ሁሉ የአላህ ነውና፡፡ አላህ አዋቂና ጥበበኛ ነው፡፡)አን-ኒሳእ :170 .

ነቢዩን መውደድ ትክክለኛ መሆኑን የሚያሳዩ ምልክቶች ከዚህ ቀጥሎ በአጭሩ ቀርበዋል፡፡

1-እሳቸዉን ለማየት መጓጓትና እሱን እድል ከማጣት ሌላን ምንንም ነገር ከማጣት ማስቀደም፤

2-ለሳቸው ሲል እስከ ሕይወት መሰዋት ድረስ ለመክፈል መዘጋጀት፤

3-ትዕዛዛቸዉን ማክበርና የአቅሙን ያክል መተግበር፤

4-የእሳቸዉን ሱና መደገፍና ከሱም ላይ መከላከል ናቸው፡

ነቢዩን መውደድ የሚያስከትለው ጥቅም ከዚህ ቀጥሎ በአጭሩ ቀርቧል፡፡

1-አላህ ይወደዋል ወንጀሉንም ይምረዋል፡፡ አላህ እንዲህ አለ፡-(መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! ፡- አላህን የምት ወዱ እንደሆናችሁ እኔን ተከተሉኝ፡፡ አላህ ይወዳችኋል፡ ፡ ኃጢአቶቻችሁንም ለእናንተ ይምራልና....)አሊ ዒምራን 31-32.

2-የቂያማ ዕለት ከሳቸው ጋር ይሆናል፡፡ ነቢዩ እንዲህ አሉ(ምን አዘጋጅተሀሰል፡፡ አላህንና መልዕክተኛዉን መውደድ አላቸው እሳቸዉም አንተ ከወደድካቸው ጋር ነህ) ሙስሊም.

በትክክል ነቢዩን የወደደና ሱናቸዉን ጠብቆ የኖረና በዚሁ ላይ ኺታሙ የሆነለት እኒህና የመሳሰሉት መልካም አድሎች ይጠብቁታል፡፡ ሁላችንም እንዳያመልጠን ነቢያች ንን በትክክል ልንወዳቸው ይገባል፡፡



# ሲሳይ እና ማግኛው ምክኒያቶች

ሲሳይን በተመለከተ መታወቅ ያለባቸው መሰረታዊ ጉዳዩች አሉ፡፡ እነሱም፡-

1-የሁሉም ሲሳይ ከአላህ የተወሰነለት መሆኑን፡፡ አላህ እንዲህ « .በምድርም ላይ ምንም ተንቀሳቃሽ የለችም ምግቧ በአላህ ላይ ያለና ማረፊያዋንም ሆነ መርጊያዋን የሚያውቅ ቢሆን እንጂ፡፡ ሁሉም ነገር ግልጽ በሆነው መጽሐፍ ውስጥ ነው» ሁድ፡6

2-መስራትና መንቀሳቀስ ሰበቦችእን ማድረስ ተገቢ ነው፡ ፡ አላህ እንዲህ አለ «.እርሱ ያ ምድርን ለእናንተ የተገራች ያደረገላችሁ ነው፡፡ በጋራዎቿና በመንገዶቿም ሂዱ፡፡ ከሲ ሳዮም ብሉ፡፡ » አል ሙልክ ፡ 15.

3-ሲሳይ የሚፈለገው ከአላህ ብቻ መሆኑን ማወቅ ወሳኝ ነው፡፡ አላህ እንዲህ አለ«-ሶላቷ በተፈፀመች ጊዜ በምድር ላይ ተበተኑና የአላህን ችሮታ ፈልጉ፡፡» አልጁሙዐህ 10.

4-ከአላህ ሌላ ማንም ሲሳይን የሚሰጥ የለም፡፡ አላህ እንዲህ አለ‹‹እነዚያ ከአላህ ሌላ የምትገዟቸው ለእናንተ ሲሳይን ሊሰጧችሁ አይችሉም፡፡ ስለዚህ ሲሳይን ከአላህ ዘንድ ብቻ ፈልጉ፡፡ ተገዙትም ለርሱም አመስግኑ ወደ እርሱም ትመለሳላችሁ›› አል ዐንከቡት፡17.

ሪዝቀን የሚያሰፋዉና የሚያጠበው አንድ አላህ ብቻ መሆኑ ሙስሊሞች ሁሉ የምንስማሙበት መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡

አላህ እንዲህ አለ‹‹መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ፤ጌታዬ ሲሳይን ለሚሻው ሰው ሁሉ ያሰፋል፡፡ ለሚሻው ሰውም ሁሉ ያጠባል፡፡ ግን አብዛኛዎች ሰዎች ይህን አያውቁም በላቸው፡፡ ገንዘቦቻችሁና ልጆቻችሁም ያች እኛ ዘንድ መቅ ረብን የምታቀርባችሁ አይደለችም፡፡ ያ! በትክክል ያመነና መልካምን የሰራ ብቻ ሲቀር...)ሰበእ፡36-38. ሆኖም ብዙ ሰዎች አብዛኛዉን ጊዘያቸዉን የሚያሳልፉት ሪዝቅን በማ ፈላለግ ላይ ነው፡፡ አንዳንዶችማ እንዴዉም ለዚሁ ሲሉ

አላህ በከከለከለዉ መስመር በኩልም የሚያሳድዱት አሉ፡ ፡ እናም በዚህ የተነሳ እንዲሰሩት ከተፈጠሩበት አላማም ይስታሉ፡፡ አላህ እንዲህ አለ «አጋንንትና ሰውም ሊገዙኝ እንጂ ለሌላ አልፈጠርኳቸውም፡፡ ከእነሱም ምንም ሲሳይ አልፈልግም፡፡ እንዲመግቡኝም አልፈልግም» አዝ-ዛሪያት 56

.ሲሳይን ማፈላለግና ለእሱም የተላያዩ አላህ የፈቀዳቸዉን ዘዴዎች በአቅም ልክ መጠቀም ይፈቀዳል ብቻ ሳይሆን እን ደሁኔታው ግዴታም ይሆናል፡፡ ይህን አስመልክቶ አላህ እንዲህ አለ «እርሱ ያ ምድርን ለእናንተ የተገራች ያደረገ ላችሁ ነው፡፡ በጋራዎቿና በመንገዶቿም ሂዱ፡፡ ከሲሳዮም ብሉ፡፡ ኋላ መመለሻችሁም ወደ እርሱ ብቻ ነው» አል-ሙልክ 15.

እንዲህም አለ «ሶላቷ በተፈፀመች ጊዜ በምድር ላይ ተበ ተኑና የአላህን ችሮታ ፈልጉ፡፡ ልትድኑ ይከጅላልና አላህ ንም በብዙው አውሱ» አል-ጁሙዐ 10. የአላህ መልዕክተ ኛም እንዲህ አሉ (...አላህ ሆይ! ለሰጠህው ከልካይ የለም ለከለከልከው ሠጪ የለዉም) ሙስሊም. አላህ የሰዉን ልጅ ሪዝቁን ዋስትና ሰጥቶታል፡፡ ምክኒያቶችንም ደንግ ጎለታል፡፡ ሰዎች የሚጠበቅባቸው ሰበቦችን ከማድረስ ባሻገር አለመጨነቅ ነው፡፡ ሪዝቁ በእሱ ጥረት ይመጣል ብሎ መገመት የለበትም፡፡ የእሱ ጥረት ምክኒያት እንጂ ሲሳዩ ያለው በአላህ እጅ ነው፡፡ እናም ሰበቦችን ካደረሰ በኋላ ራሱን ማጨናነቅ የለበትም፡፡ ምክኒያቱም የሪዝቁን አድራሻ የት እንደሆነ ፈፅሞ አያውቅምና፡፡ ሪዝቁ ግን የሰ ዉየዉን አድራሻ ጠንቅቆ ያውቀዋል፡፡ ከአላህ በተወሰነለት ጊዜና ቦታ በሩን ቆርቁሮ መምጣቱ እንደማይቀር ማረጋ ገጥ ይኖርበታል፡፡ ሀያሉ አላህ እንዲህ አለ «ሲሳያችሁንና የምትቀጠሩት ፋኢዳና ምንዳ ሰማይ ውስጥ ነው፡፡ በሰ ማይና በምድር ጌታም እምላለሁ፡፡ እርሱ እናንተ እንደም ትና ገሩት ብጤ እርግጠኛ ነው» ሐሰኑ ል በስሪ «ብዙ አኺራ ፈላጊዎች ዱንያ ስትመጣላቸው ያየን ሲሆን ዱንያን ለሚፈልግ ግን አኺራ ሲመጣላቸው አላየንም ብለዋል» የአላህ መልዕክተኛም እንዲህ አሉ« የሰው ልጅ ከሞት እነደሚሸሸ ያክል እንኳን ከሪዝቁ ቢሸሽ ሞት አሳዶ እን ደሚደርስበት ሁሉሪዝቁምይመጣለታል» አቡ ኑዐይም. እንዲህ በመሆኑም የሰው ልጅ ይህን እውነታ ቢቀበልና ከሰበቦች በኋላ ከመጣለት ተደስቶ ካልመጣም በትዕግስት ቢጠብቅ በማይረባ ጊዜያዊ ነገር ሲባከን እድሚው አያል ቅም ነበር፡፡ ለሪዝቅ ማግኛ ከሚሆኑም ከኒያቶች የተወሰኑ ትን መጠቆሙ ጠቀሜታ አለዉና ከዚህ የተወሱትን ተመ ልከቱ፡፡

1-ተውሒድን /እምነትን ማረጋጋጥ ነው፡፡ ስለ ዚህ ጉዳይ አላህ እንዲህ አለ «የየከተሞቹ ሰዎች በትክክል ባመኑና በተ ጠነቀቁ ኖሮ በእነሱ ላይ ከሰማይና ከምድር በረከቶችን በከ ፈትንላቸው ነበር፡፡ ግን አስተባበሉ፡፡ ይሠሩት በነበሩትም ኃጢአትቀጣናቸው» አል-አዕራፍ 96.

2-ሶላትን ለራሳችን በደንብ መስገድና ቤተሰቦቻችንንም ዲናቸውን ማዘዝ ነው፡፡ አላህ እንዲህ አለ (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ ! ቤተሰብህን በሶላት ላይ እዘዝ፡፡ አንተም በእርሷ ላይ ዘውትር ፡፡ ሲሳይን አንጠይቅህም፡፡ እኛ እን ሰጥሃለን፡፡ መልካሚቱ መጨረሻ ለጥንቁቆች ሁሉ ናት» ጣሃ 132. ሱፍያኑ ሰውሪ የተባሉ ዐሊም «ሲሳይን አንጠይ ቅህም» ማለት እንድ ታፈላልግ አናስገደድህም ማለት ነው» ካሉ በኋላ በዚህ አንቀፅ መሰረት ሂወቱን የመራ ሁሉ አይደ ኸይም ከሰዉም ምንንም አይፈልግም ብለዋል፡፡

3- አላህን በትክክል መፍራት ነው፡፡ አላህ እንዲህ አለ «አላህን የሚፈራ ሰው ሁሉ ለእርሱ መውጫን ያደርግ ለታል፡፡ ከማያስበውም በኩል ሲሳይን ይሰጠዋል፤...» አጦላቅ2-3 አላህን መፍራትና ጉዳይን ሁሉ ጠቅልሎ ለእሱ መስጠት ፍቱን መደሃኒት ነው፡፡ ከአቅም በላይ የሆኑ ነገ ሮችንም በአንድ አፍታ ያቃልላል፡፡ ከዚህ በታች ያለዉም ታሪክ የሚያመለክተው ይህንኑ ነው፡፡ አውፍ ቢን ማሊ

ክልጁ በጠላቶች ተማርካ ስለ ነበር እናቱ አዘነች:: ምን ይመክሩኛል ? በማለት ነብዩ ሙሐመድን (ﷺ) ስለ ጠየቀና:-እሳቸዉም ታገስ አላህን ፍራ:: አንተም ሆንክ እናቱ ላህውለ ወላ ቁወተ ኢላ ቢላህ የሚለውን አብዙ:: ብለውት ወደ ቤቱ ተመልሶ ለሚስቱ የተነገረውን ነገሯት:: እሷም በጣም ጥሩ ነው የተባል ነው አለች:: የተባሉትን ሲተገብሩ ሳለ ጠላቶች ተዘናግቶ እያለ ልጃቸው አራት ሺህ ፍየሎችን ነድቶ ይዞ ስለመጣ ነው ይህ አንቀፅ የወረደው:: (ዋሂዲ እና ሱዩጢ)

4-ከሀያሉ አላህ ምህረትንመፈለግነው:: አላህ እንዲህ አለ: -«ጌታችሁን ምህረትን ለምኑት:: እርሱም በጣም መህሪ ነውና:: በእናንተ ላይ ዝናምን ተከታታይ አድርጎ ይልካል:: ገንዘቦችንና ልጆችን ይለግሳችኋል:: ለእናንተ አትክልቶችን ያደርግላችኋል:: ለእናተም ወንዞችን ያደርግላችኋል አልኳቸው» ኑህ 10-12. የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉ «ምህረትን መለመን ያበዛ ሰው ለጭንቁ ሁሉ መፍቲሄ፤ ለጠበበው ሁሉ መውጫያደርግለታል:: ከማይገምተዉም በኩል ይረዘዝቀዋል» አህመድ.

5-በአላህ ላይ ብቻ መመካት ነው:: አላህ እንዲህ አለ «.....በአላህም ላይ የሚጠጋ ሰው እርሱ በቂው ነው.... .» አጦላቅ 3. ነቢዩ እንዲህ አሉ«.በአላህ በትክክል ብትመኩ ኖሮ ያችን ባዶ ሆዷ ወጥታ ሆዷን ሞልታ የምትመለሰዋን ወፍ እንደሚረዝቃት ሁሉ ይረዝቃችሁ ነበር»ቲርሚዚ.

6-ዝምድናን መቀጠል ነው:: ይህን በተመለከተ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉ:-«ሪዝቁ እንዲሰፋለትና እድሜው እንደረዝምለት የሚፈልግ ሰው ዝምድናዉን ይቀጥል»ቡኻሪ.

7-ሰደቃን ማብዛት ነው:: ስለዚህ አላህ እንዲህ አለ:: (መልዕክተኛችን ሙሐመድ ሆይ! ጌታዬ ሲሳይን ከባሮቹ ለሚሻውሰውያሰፋል:: ለእርሱም ያጠባል:: ከማንኛውም ነገር የምትለግሱትን እርሱ ይተካዋል:: እርሱም ከሲሳይ ሰጪዎች ሁሉ በላጭ ነው በላቸው» ሰበእ 39.

8-ሐጅንና ዑምራን መደጋገም ነው:: ስለዚህ ነቢዩ እንዲህ አሉ «.ሐጅና ዑምራን አከታትሉ የብረትን ቆሻሻ ወላፈን እንደሚያባርረው ሁሉ ድህነትንና ወንጀልን ስለሚያስወግዱ» ቲርሚዚ.

9-ማግባት ነው:: ይህን አስመልክቶ አላህ እንዲህ አለ (ሙስሊሞች ሆይ ! ከእናንተ መካከል ትዳር የሌላቸውን ሰዎች አጋቡ:: ከወንዶች ባሮቻችሁና ከሴቶች ባሮቻችሁም ለጋብቻ ብቁ የሆኑትን ክፍሎች አጋቡ:: ድሆች ከሆኑም አላህ ከችሮታው ያከብራቸዋል:: አላህ ስጦታው ሰፊና ሁሉን ዐዋቂ ነውና) አል-ኑር 32. ዑመር ‹ድሆች ከሆኑም አላህ ከችሮታው ያከብራቸዋል:: እያለ በማግባት ሀብት የማይፈልግ ይገርመኛል»ብለዋል»

10-ዱዓ ማድረግ ነው:: ይህን በተመለከተ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉ «አቡ ኡማማህ ምነው በመስጂድ ያለ ሶላት ወቅት ተክዞሃል አሉት :: እሱም ሀሳቦችና ብድሮች ይዘዉኝ ነው አላቸው:: እሳቸዉም ጭንቀትህን ለማስወገድ የምታነባቸው ቃላትን ላስተምርህን አሉት እሱም አዎ አላቸው:: የአላህ መለዕክተኛም በጧት በማታ እንዲህ በል «አላሁመ ኢኒ አዑዙ ቢከ ሚነልሀሚ ወል ሐዘኒ ወል ዐጅዚ ወል ከሰሊ ወልጁብኒ ወል ቡኽሊ በዲለዒደይኒ ወቀህሪ ሪጃል» የሚሉትን በል ሲሉት ይህን ፍፅሜ አላህ ጭንቀቴን ሁሉ አስ ወገደልኝ ብድሬንም ከፈለለኝ» አቡ ዳዉድ.

11-አላህን በፀጋዎቹ ላይ ማመስገን ነው:: አላህ እንዲህ አለ:-«ጌታችሁም ባለ ጊዜ የሆነውን አስታውስ ብታመሰግኑ በእርግጥ እጨምርላችኋለሁ:: ብትክዱም እቀጣችኋለሁ:: ቅጣቴ በእርግጥ ብርቱ ነውና በማለት ባስታወቀ ጊዜ አስታውሱ»ኢብራሂም 7.

ዑመር ኢብኑ ዐብዱል-ዐዚዝ እንዲህ ብለዋል:: «የአላህን ፀጋዎች በምስጋና እሰሯቸው:: ምስጋና የፀጋ ማሰሪያ ነውና»

12-ልጅ መውለድ ነው:: ቁርኣን እንዲህ አለ (ሰዎች ሆይ ! ልጆቻችሁን ድህነትን በመፍራት አትግደሉ:: እኛ እንመግባቸዋለን:: እናንተንም እንመግባለን:: እነሱን መግደል ታላቅ ኃጢአት ነውና) አል አስራእ31. እንዲሁም አለ (... ልጆቻችሁንም ድህነትን ፈርታችሁ አትግደሉ:: እኛ እናንተንም ሆነ እነርሱን እንመግባችኋለንና) አል-አንዓም 151.

ሲሳያችንን ሊያጠብብን የሚችሉ ነገሮች ብዙ ናቸው:: ሲሳያችንን ሊያጠብብን የሚችሉ ነገሮችም በጣም ብዙ ናቸው:: በዋነኝነት የሚጠቀሱት ግን ከዚህ በታች የተጠቆሙት ናቸው::

1-የወንጀል መብዛት ነው:: አላህ እንዲህ አለ (ሰዎች ሆይ! ማንኛውም መከራ ያገኛችሁ እጆቻችሁ በሰሩት ኃጢአት ምክንያት ብቻ ነው:: ብዙውንም ይቅር ይላል) 42:30.



የአላህ መልዕክተኛም እንዲህ አሉ (የሰው ልጅ በወንጀሉ ምክኒያት ሲሰሰይ ይከለላል )

2- ከወለድ ጋር መነካካት (አላህ የአራጣን ገንዘብ ያከስ ማል፡፡ መልካም ልገሳዎችን ያፋፋል፤ አላህም ኃጢአተኛ ንና ከሓዲን ሁሉ አይወድምና)2፡276.

3-ሰበቦችን አለማድረስና ስንፈት ከድህነት ምክኒያቶች በብዛት የሚጠቀስ ነው፡፡ ሙስሊም ሰነፍ አይደለም፡፡

4-የወላጆቹን ሐቅ አለመጠበቅና ሐቃቸዉን መርገጥ የድ ህነቱ ትልቅ በር፤

5-ዝምድናን መቁረጥ ዋናው ነው፡፡ የአላህ መልዕክተኛ እንዲህ አሉ (ሪዝቁ እንዲሰፋለት፤ እድሜው እንዲረዝም ለት የፈለገ ሰው ዝምድናን ይቀጠል)

6-ዝሙት፤ ሰዎችን መመቅኜት፤ ሰዎችን መናቅ፤ ዉሼት፤ ጋጠወጥነት እና ሌሎችም ወንጀሎች የድህነት በር መከፋቻ ናቸው፡፡ ማንም ሰው ከአላህ የተከተበለትን ብቻ ነው የሚ ያገኘው ምንም ቢሮጥና ቢለፋ ከልኩ አያልፍም፡፡ ምንም ቢዘገይ ደግሞ የተከተበለትን ሳያገኝ ከዚች አለም ፍንክች አይልም፡፡ ነቢዩ እንዲህ «ሲሳያችሁን አታጣድፉ፡፡ ማንም ሰው ለሱ የተባለለትን ሳያገኝ ማንም አይሞትም ፡፡ እናም አፈላለጉን አሳምሩ፡፡ ሐላልን ፈልጉ፡፡ ሐራምን ራቁ» ሲል ሰለቱ ሶሂሃ. የአላህን ፀጋ ማመስግን ግዴታ ነው፡፡ አነሰ ብሎ ማማረርና መናቅ ተገቢ አይደለም፡፡ ነቢዩ ሙሐመድ እንዲህ አሉ፡- «ወደ በታቻችሁ ተመልከቱ፡፡ ምክኒያቱም የአላህን ፀጋ እንዳትንቁ ያደርጋችኋልና»ሙስሊም. ሪዝቅን መፈለግ ፈፅሞ ነዉር አይደለም፡፡ ይልቁንም ተገቢና የተ ወደደ ከጂሃድ ጋር በመሳነት በቁርኣን የተወሳ ነው ፡፡ አላህ እንዲህ አለ «ሙስሊሞች ከእነዚያም አብረውህ ካሉ ከፊሎች የሚቆሙ መሆናቸውን ያወቃል፡፡ አላህ ሌሊትና ቀንን ይለካል፡፡ ሌሊቱን በሙሉ የማትቆሙት መሆናችሁን አወቀ፡፡ እናም በእናንተ ላይ ህጉን ወደ ማቃለል ተመለ ሰላችሁ፡፡ ስለዚህ ከቁርኣን በስግደት የተቻላችሁን ያህል አንብቡ፡፡ ከእናንተ ውስጥ በሽተኞች ከአላህ ችሮታ ለመፈ ለግ በምድር ላይ የሚጓዙ ሌሎችም፤ በአላህ መንገድ /ሃይማ ኖት ላይ የሚጋደሉ እንደሚኖሩ አወቀ» አል ሙዘሚል20. ነዉር የሚሆነው ሲሳዩን በሐራም መንገድ መፈለግ ና ባገኜ ነውም ንብረት መፈተን ነው፡፡ እንዲያዉም ቁርኣን « ከእ ነርሱ ውስጥ ጌታችን ሆይ ! በምድር ዓለም ደግን ነገር ፀጋን በመጨረሻይቱ ሀገርም ደግን ነገር ገነትን ስጠን፡፡ ከእሳትም ቅጣት ጠብቀን»201 የሚሉ ሰዎች አሉ፡፡እነዚያ ከሰሩት በጎ ስራ ድርሻ አላቸው፡፡ አላህ ምርመራው ፈጣን ነው፡፡ ከእሳትም ቅጣት ጠብቀን የሚሉ አሉ» ብሏል፡፡

በአጠቃላይ ራሳችንን በቁርኣንና በሱና ከተመራን የሁለቱ ንም ዐለም ደስታ እንደሚለግሰን ባለሙሉ ተስፋ ልንሆን ይገባናል፡፡

//////







ዘምዘም መጽሄት

እስላም ሀውስ ዌብሳይት

የሙስሊም
ህፃናት ሊስቱት የማይገባ

የመጨረሻው አስር አንደኛን
ተፍሲር



በነፃ የሚከፋፈል ነው ፡፡

ከደዕዋ ነክ ህትመቶች አንዱ ነው ፡፡

اللغة الأمهرية